# የሰባኪው ምሳሌ

2ኛመጽሐፍ



1. የምድር ጨው ወይስ የእንግሊዝ ጨው
2. መርፌ የራሱን ቀዳዳ አይሰፋም
3. ኢብራሂም ሰላም ብሎሃል
4. የእርግዝና መከላከያ ዘዴ
5. ጊወርጊስ ወይስ ዮሐንስ?
6. ሙሉ ወንጌልን እወዳለሁ
7. ድንግል ማርያም

በወንጌላዊ ደመወዝ አበበ

# ማውጫ

## ክፍል አንድ

### እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ትዳር


- በዛሬዋ ጀምበር....1
- በግ አራጁ በግ ለልጁ....2
- የጎዳና ልጆች....3
- ከራስ በላይ ራስ....5
- አሽሙርና ትዳር....6
- አንድ ሥጋ በሁለት አልጋ....7
- የባል ዘመድ በዓይኑ አመድ....8
- ጭድ የሌለው ጭቃ....10
- የእርግዝና መከላከያ ዘዴ....11


## ክፍል ሁለት

### እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ኅብረትና ፍቅር


- አንድ ብር ለአንድ ወገን....12
- አምስቱ ካልሲዎች....13
- ጉንዳን ከተባበረ ወንዝ ይሻገራል....14
- ፍቅር እውር ነው....15
- ከእኔ በላይ ለአሳር....16


## ክፍል ሦስት

### እግዚአብሔርን ስለ ማመስገን


- ወንደላጤውና ድመቷ....17
- ሠላሳ ሁለት ጥርስ....18


## ክፍል አራት

### ለእግዚአብሔር ስለ መኖር


- የጋለሞታ ልብስ....19
- አልማዝ ባለጭራ....20
- ሴትን ከጃለሁ....21


## ክፍል አምስት

### ስለ እግዚአብሔር አዳኝነት


- ሰይጣንን በቆመጥ....22
- መስተፋቅር በሎሚ....23
- አጋንንቱና ሥራ አስኪያጁ....24
- ጥቁር አባቡሌ....25
- ፊታኙን እምቢ በል....27
- ኑር ያልኩት ይኖራል....29
- በሕግ አምላክ....30
- የመቃብር አፈር....31
- ድንግል ማርያም....33

## ክፍል ስድስት

### እግዚአብሔርን የሚስደስት ሕይወትና አገልግሎት


- ምላጭ አበጠ በምን ይበጣ....34
- ገንፎ በቂቤ....36
- ጴንጤው በክሰኛ....37
- ሰላቢ የሰለበው ሀብት....38
- እግዚአብሔር አይዘበትበትም....39
- ጌታ ልቤን እንጂ እጄን አልሰበረውም....40
- የምድር ጨው ወይስ የእንግሊዝ ጨው....41
- ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ....43
- የአርባ ቀን ዕድሌ....44
- ደምህን አቁሜአለሁ....45
- ስኬት....47
- መገለጥ ወይስ ማጋለጥ....48
- ነብር በቤታችን አለ....50
- መንፈስ ቅዱስ የለም....51


## ክፍል ሰባት

### እግዚአብሔርን ስለ መጠበቅ


- በክሰኛ አፍንጫውን ይሰበራል....53
- የሩቅ ሣር ለምለም መስሎ ይታል....55
- ጠብቀነው ጠብቀነው....56
- እግዚአብሔር ጊዜ አለው....57
- ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም....58


## ክፍል ስምንት

### እግዚአብሔርን በሙሉ ኃይል ስለ ማገልገል


- የአሜሪካን ፕሬዚዳንት....60
- የቄሣርን ለቄሣር....61
- ኃይሌ ገብረ ሥላሴና ቀነኒሣ....62


## ክፍል ዘጠኝ

### እግዚአብሔርን አምኖ ከሞት ስለ መዳን


- ሙሉ ወንጌልን እወዳለሁ....63
- የአስቂዋ ልጆች....64
- ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት....65
- የተበላ እቁብ....66
- ዕዳ መቶ ሲሞላ አይከብድም....67
- ጊወርጊስ ወይስ ዮሐንስ....68
- የፋሲካው በግ....69
- ይሉኝታ ይገድላል....70

## ክፍል አሥር

### ለእግዚአብሔር ስለ መስጠትና መስጠት


- ኮርሽምሽምሽምሽምሽም ........ 72
- ኢንቨስተሩ........ 73
- የፈረንጅ ላም ........ 75
- ዲቪ ቢወጣልኝ........ 76
- ኑሮ ጨምሯል........ 77
- እንደ አንበጣዎች ነን ........ 78
- ችግሬ ክሶኝ ተከሰከሰ ........ 80
- እናቴ ጆሮዬን በላችው........ 82
- መርፌ የራሱን ቀዳዳ አይሰፋም ........ 84


## ክፍል አሥራ አንድ

### ስለ እግዚአብሔር ቃል


- የጨረቃ ቤት ........ 85
- የሌባ ዓይነ ደረቅ ........ 86
- እኔም ዜሮ ነኝ........ 87
- ኢየሱስ ሳሎን ቤት ነው ያለው........ 88
- በኤፌሶን ይገኛዎታለሁ........ 89
- በውሻ የተበላው ስብከት ........ 90
- ለካስ ለበጎ ነው ........ 92
- ሚስቴ ሞገሴ ናት ........ 94
- መሐይሙ እሥረኛ........ 95


## ክፍል አሥራ ሁለት

### ግብዝነት ስለሌለበት እውነት


- ገመድ ሰርቄአለሁ ........ 97
- በወገቡ የተጠመጠመው እባብ........ 98
- ኢብራሂም ሰላም ብሎሃል........ 99
- ጾም ጸሎት........ 101

# የሰባኪው ምሳሌ

## 2ኛ መጽሐፍ

በወንጌላዊ ደመወዝ አበበ

በ1998 ዓ.ም ታተመ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

ይህን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት ወይም
መልሶ ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

Copyright© Demewez Abebe
August 2005
All rights reserved.

አሳታሚና አከፋፋይ:-
የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ. ቁጥር 127
ስልክ 349 32 52 / 551 29 73
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ኢ-ሜይል:- SIMmedia@ethionet.et

**Printed by SIM Press**

# ማውጫ

## ክፍል አንድ

### እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ትዳር


- በዛሬዋ ጀምበር.......1
- በግ አራጁ በግ ለልጁ.......2
- የጎዳና ልጆች.......3
- ከራስ በላይ ራስ.......5
- አሽሙርና ትዳር.......6
- አንድ ሥጋ በሁለት አልጋ.......7
- የባል ዘመድ በዓይኑ አመድ.......8
- ጭድ የሌለው ጭቃ.......10
- የእርግዝና መከላከያ ዘዴ.......11


## ክፍል ሁለት

### እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ኅብረትና ፍቅር


- አንድ ብር ለአንድ ወገን.......12
- አምስቱ ካልሲዎች.......13
- ጉንዳን ከተባበረ ወንዝ ይሻገራል.......14
- ፍቅር እውር ነው.......15
- ከእኔ በላይ ለአሳር.......16


## ክፍል ሦስት

### እግዚአብሔርን ስለ ማመስገን


- ወንደላጤውና ድመቷ.......17
- ሠላሳ ሁለት ጥርስ.......18


## ክፍል አራት

### ለእግዚአብሔር ስለ መኖር


- የጋለሞታ ልብስ.......19
- አልማዝ ባለጭራ.......20
- ሴትን ከጃለሁ.......21


## ክፍል አምስት

### ስለ እግዚአብሔር አዳኝነት


- ሰይጣንን በቆመጥ.......22
- መስተፋቅር በሎሚ.......23
- አጋንንቱና ሥራ አስኪያጁ.......24
- ጥቁር አባቡሌ.......25
- ፊታችን እምቢ በል.......27
- ኑር ያልኩት ይኖራል.......29
- በሕግ አምላክ.......30
- የመቃብር አፈር.......31
- ድንግል ማርያም.......33

## ክፍል ስድስት

### እግዚአብሔርን የሚስደስት ሕይወትና አገልግሎት


- ምላጭ አበጠ በምን ይበጣ ........ 34
- ገንፎ በቂቤ ........ 36
- ጴንጤው በክሰኛ ........ 37
- ሰላቢ የሰለበው ሀብት ........ 38
- እግዚአብሔር አይዘበትበትም ........ 39
- ጌታ ልቤን እንጂ እጄን አልሰበረውም ........ 40
- የምድር ጨው ወይስ የእንግሊዝ ጨው ........ 41
- ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ........ 43
- የአርባ ቀን ዕድሌ ........ 44
- ደምህን አቁሜአለሁ ........ 45
- ስኬት ........ 47
- መገለጥ ወይስ ማጋለጥ ........ 48
- ነብር በቤታችን አለ ........ 50
- መንፈስ ቅዱስ የለም ........ 51


## ክፍል ሰባት

### እግዚአብሔርን ስለ መጠበቅ


- በክሰኛ አፍንጫውን ይሰበራል ........ 53
- የሩቅ ሣር ለምለም መስሎ ይታል ........ 55
- ጠብቀነው ጠብቀነው ........ 56
- እግዚአብሔር ጊዜ አለው ........ 57
- ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም ........ 58


## ክፍል ስምንት

### እግዚአብሔርን በሙሉ ኃይል ስለ ማገልገል


- የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ........ 60
- የቁማርን ለቁማር ........ 61
- ኃይሌ ገብረ ሥላሴና ቀነኒሣ ........ 62


## ክፍል ዘጠኝ

### እግዚአብሔርን አምኖ ከሞት ስለ መዳን


- ሙሉ ወንጌልን እወዳለሁ ........ 63
- የአስቂዋ ልጆች ........ 64
- ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ........ 65
- የተበላ እቁብ ........ 66
- ዕዳ መቶ ሲሞላ አይከብድም ........ 67
- ጊወርጊስ ወይስ ዮሐንስ ........ 68
- የፋሲካው በግ ........ 69
- ይሉኝታ ይገድላል ........ 70

## ክፍል አሥር

### ለእግዚአብሔር ስለ መስጠትና መስጠት


- ኮርሽምሽምሽምሽምሽም ........ 72
- ኢንቨስተሩ ........ 73
- የፈረንጅ ላም ........ 75
- ዲቪ ቢወጣልኝ ........ 76
- ኑሮ ጨምሯል ........ 77
- እንደ አንበጣዎች ነን ........ 78
- ችግሬ ክሶኝ ተከሰከሰ ........ 80
- እናቴ ጆሮዬን በላችው ........ 82
- መርፌ የራሱን ቀዳዳ አይሰፋም ........ 84


## ክፍል አሥራ አንድ

### ስለ እግዚአብሔር ቃል


- የጨረቃ ቤት ........ 85
- የሌባ ዓይነ ደረቅ ........ 86
- እኔም ዜሮ ነኝ ........ 87
- ኢየሱስ ሳሎን ቤት ነው ያለው ........ 88
- በኤፌሶን ይገፎታለሁ ........ 89
- በውሻ የተበላው ስብከት ........ 90
- ለካስ ለበጎ ነው ........ 92
- ሚስቴ ሞገሴ ናት ........ 94
- መሐይሙ እሥረኛ ........ 95


## ክፍል አሥራ ሁለት

### ግብዝነት ስለሌለበት እውነት


- ገመድ ሰርቄአለሁ ........ 97
- በወገቡ የተጠመጠመው እባብ ........ 98
- ኢብራሂም ሰላም ብሎሃል ........ 99
- ጾም ጸሎት ........ 101

# ማስታወሻ

ይህንን መጽሐፍ በአገልግሎቴ ሁሉ ከጎኔ በመቆም አብራኝ ለተሰለፈችው፣ ለምትጸልይልኝ፣ ለምትመክረኝ፣ እና ለምታበረታታኝ ለምወዳት ለውዷ ባለቤቴ ለወ/ሮ የሺወርቅ ሽመልስ፣ እንዲሁም በጣም ለምወዳቸው ልጆቼ ለቤተልሔም ደመወዝና ለሃሌሉያ ደመወዝ እንዲሆን አበረክታለሁ።

# ምስጋና

ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ጤንነትን፣ ሰላምንና ጸጋን ያበዛልኝን አምላኬን እግዚአብሔርን በፍጹም ልቤ አመሰግናለሁ። በመቀጠልም፣ ከጎኔ ቆመው ያበረታቱኝን፣ የጸለዩልኝን፣ የጽሑፉን ረቂቅ በማንበብ ከስሕተት ያረሙኝን፣ በመደጋገም የጻፉልኝን ሰዎች ሁሉ ለማመስገን እወዳለሁ። እንዲህም ሆኖ ሳለ፣ በዚህች መጽሐፍ ውስጥ ፈጽሞ ስሕተት የለም ማለት አይቻልም። ሆኖም፣ የተፈጠረ ስሕተት ቢገኝ በተገኘው ስሕተት ተወቃሹ እኔው እራሴው እንጂ እነዚህ ሰዎች አይደሉም። የአቃቂ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን፣ ወንጌላዊያንና ምእመናንን ሁሉ አመሰግናቸዋለሁ። እንዲሁም ባለቤቴን ወ/ሮ የሺወርቅ ሽመልስን፤ ወ/ም ዳንኤል ኃይሉን፣ ወ/ም ናይእግዚ ጎሩይን፣ ወ/ም ዘነበ ገ/ሐናን፣ እኅት አለምፀሐይ እውነቱን፣ እና እኅት የሺመቤት ደምሴን እግዚአብሔር አምላክ ያክብርልኝ፣ ሰላም፣ እድሜና ጤና ይስጥልኝ እላለሁ።

# መግቢያ

የሰውን አእምሮና ልብ በራሱ ፈቃድ እንዲከፍት አድርጎ በአእምሮው ውስጥና በልቡ ተቀምጦ ሳይረሳ ሁልጊዜ የሚኖር ቢኖር በምሳሌ የተላለፈ ትምህርት ነው፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በሥጋ በተመላለሰበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው ሕዝቡን በማስተማር ነበር፡፡ ታዲያ ትምህርቱ የሚያርፈው መሬት ሳይሆን የሰው ልብ ላይ ነበር፡፡ እርሱ በሚያስተምርበት ጉባኤ ያለ ሰው ሁሉ ለአፍታም አሳቡ ተሰርቆ ወይም ተሰላችቶ እንደ ነበረ አንድም ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ አናነብም፡፡ የዚህ ምሥጢሩ ምን ነበር? አንዱ ምሥጢር ተገቢና ልብን አንጠልጣይ ምሳሌ መጠቀሙ ነው፡፡

የዛሬ አሥራ ሁለት ዓመት አካባቢ ከሰማኋቸው ብዙ መልእክቶችና ትምህርቶች ውስጥ አብዛኛዎቹን አላስታውስም፣ ጥቂቶቹን ግን አስታውሳለሁ፤ ምክንያቱም በብዙ ምሳሌ ወደ ውስጤ ገብተው ነበርና ነው፡፡ እንዲሁ ዛሬም በሰዎች ልብ ውስጥ ቀርተው ፍሬ ሊያፈሩ የቻሉ ትምህርቶችን ስናጠና የምሳሌን ኃያልነት ሳንጠቅስ አናልፍም፡፡

እኔም ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ዋናው ቁም ነገር ይህ ነው፡፡ ሕይወት ሰጪ የሆነውን ወንጌል ስናስተምር ከትምህርቱ ጋር በትክክል የሚሄዱ ምሳሌዎችን ብንጠቀም በሰዎች ልብ ውስጥ ሠርፆ መቅረቱ አሌ የማይባል ሐቅ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን መጽሐፍ መጋቢዎች፣ ቄሶች፣ የወንጌል አስተማሪዎች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች፣ እንዲሁም ወንጌልን ለሌሎች ለማስተማር የሚፈልጉ ሁሉ እንዲጠቀሙበት እመክራለሁ፡፡

በመጨረሻም፣ ይህንን መጽሐፍ ሳዘጋጅ በተለያየ መንገድ ከጐኔ ተሰልፈው የረዱኝንና ያበረታቱኝን፣ እንዲሁም ከውድ ጊዜያቸው ላይ ቆርሰው ጽሑፉን አንብበው በማረም ያገዙኝንና ጠቃሚ ምክር እና አስተያየት የሰጡኝን ሁሉ አመሰግናለሁ፡፡ ይህንን መጽሐፍ ለሚያነቡ ሰዎች ሁሉ ጠቃሚና ሕይወት ለዋጭ የሆነ ትምህርትና አሳብ እንዲያገኙበት ምኞቴና ጸሎቴ ነው፡፡

ወ/ዊ ደመወዝ አበበ

# እርስዎም ይሞክሩት!

አብዛኛዎቹ በዚህ መጽሐፍም ሆነ በአንደኛው መጽሐፍ ላይ የሰፈሩት ምሳሌዎች ከእውነተኛ የሕይወት ታሪክ የተወሰዱና በሀገራችን ኢትዮጵያ የተፈጸሙ ናቸው። ይህ ማለት ደግሞ በዚህ መጽሐፍ ላይ ያሉት ምሳሌዎች ሁሉ የሀገር ሀብት ናቸው ማለት ነው።

ዛሬም ሁለተኛውን መጽሐፍ ይዤ ወደ ውድ አንባቢያን ብቅ ስል፣ ለቀጣዮቹ ተከታታይ መጻሕፍት የአንባቢያንን ገንቢ አስተያየትና ተሳትፎ በሰፊው እየጋበዝኩ ነው።ከዚህም በኋላ የሰባኪው ምሳሌ መጽሐፍ የሕዝቡን የኅብረት ሥራ ያካተተ፣ ከሕዝቡ ወጥቶ ለሕዝቡ የሚጠቅም እንዲሆን አስቤአለሁ። ስለሆነም ቀጣዩን መመዘኛዎች በማሟላት ፈቃደኛ የሆነ ሁሉ ምሳሌዎችን በአድራሻዬ ቢልክልኝ ለመጽሐፍ እንዲሆን አቀነባብሬና አስተካክዬ ምሳሌውን ከላኪው ሙሉ ስም ጋር የማሳትም መሆኔን በደስታ ለአንባቢያን እገልጻለሁ። ሆኖም፣ ምሳሌው በመጽሐፍ ላይ ታትሞ የሚወጣው የሚከተሉትን መመዘኛዎች አሟልቶና ሚዛን ደፍቶ ሲገኝ ነው፦

1. እውነተኛ ታሪክ ከሆነ፣
2. ምንጩ የተጠቀሰ ከሆነ፣
3. ከአንድ ገጽ ያልበለጠ ከሆነ፣
4. የላኪው ስም ከነአባት የሰፈረበት ከሆነ፣ እና
5. ሊነበብ በሚችል ጥሩ የእጅ ጽሑፍ የተጻፈ ከሆነ በቀጣዩ አድራሻዬ ላኩልኝ አስተናግዳለሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

ለወንጌላዊ ደመወዝ አበበ
/ለእርስዎም ይሞክሩት ፕሮግራም/
የመ.ሳ.ቁ. 70893
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# በግ አራጁ በግ ለልጁ

በዓመት ሁለት ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱ በምታዘጋጀው የጋብቻ ትምህርት ለተሰበሰበው ምእመን የዕለቱ አስተማሪ እንዲህ እያሉ አስተማሩ:: '«ዛሬ እግዚአብሔር የሰጠንን ትዳር ዘወር ብለን 'እንደ እግዚአብሔር ቃል እየመራሁ ነው ወይ? የሚጠበቅብኝንስ በትክክል እየተወጣሁ ነው ወይ?' ብለን እንድናስብ እፈልጋለሁ:: በተለይም ለቤተሰቦቻችን በቂ ጊዜ የማንሰጥ አገልጋዮችም ጭምር። አንዳንዶቻችን ምናልባት ጠዋት ሰው ሳይነሣ ወጥተን ማታ ሰው ከተኛ በኋላ እንደ አልቤርጉ ለመተኛት ብቻ ይሆናል የምንገባው። ይህ ትክክል አይደለምና መስተካከል አለበት። ልጆች የአባትና የእናት ፍቅርን ማግኘት አለባቸው፤ ባልና ሚስትም እንደዚሁ። ዛሬ ብዙ ትዳር የሚበተነው ሀብት ከማጣት ብቻ ሳይሆን፣ ጊዜም ከማጣት ሆኗልና ክርስቲያኖች ሁሉ ለቤተሰባችን ከሁሉ አገልግሎት በፊት ቅድሚያ እንስጥ። ቤተሰብ ከአገልግሎት ይበልጣልና::» ለዚህም እጅግ በጣም አስፈላጊና ግሩም የሆነ መልእክታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

«እንዳይርባቸውና እንዳይጠማቸው እንጂ ቤተሰቡ ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው፣ ልጆቹ ከእርሱ የአባትነት ፍቅር እንደሚጠብቁ ያላወቀ አንድ በየክፍለ አገሩ እየዞረ የሚሠራ ሾፌር ነበር። ስድስትና ሰባት ወር ቆይቶ ሲመጣ ጤፍ፣ ከሰል፣ በግ ይዞ ይመጣና ሰጥቶ ሳምንት እንኳን ሳይሰነብት ተመልሶ ይሄዳል። የዚህ ቤተሰብ አባላት ሥጋቸው ባይራብም መንፈሳቸው ግን የአባት ፍቅር ርቦታል፤ በተለይ ትንንሾቹ ልጆች በልባቸው ቂም ይዘው ኖረዋል። እንደዚሁ አንድ ቀን አባት ከስድስት ወር የክፍለ አገር ቆይታው በኋላ ለፋሲካ በዓል የሚሆን ሙክት በግ ይዞ መጣና ከቤቱ በር ላይ ለትንሹ ልጅ ሰጥቶ፣ ሌላ ሥራ ታዝዞ በጣም ስለ ቸኰለ ተመልሶ መኪናውን ይዞ ክፍለ አገር እንደ ሄደ ለቤተሰቡ እንዲነግር መልእክቱን ይሰጥና ይመለሳል። በዚህ ጊዜ የፋሲካን በዓል ከአባቱ ጋር ባለማሳለፉ በጣም የተናደደው ልጅ በጉን ይዞ ወደ ግቢ ይገባና እናቱን ጠርቶ 'እማዬ በግ አራጁ በግ አምጥቶልሽ ሄደ' ብሎ ተናገረ።»

አዎ ወገኖቼ፣ የእኛስ ልጆችና የትዳር ጓደኞቻችን ምን እያሉ ይሆን? ሥራና አገልግሎት እግዚአብሔር ከሰጠን ቤተሰብ አይበልጥምና እንመለስ። የአገር፣ የመንግሥት እና የቤተ ክርስቲያን ምንጩ ቤተሰብ ነውና ለቤተሰባችን ቅድሚያ እንስጥ። ጉዳናውን ለሞሉት የጉዳና ተዳዳሪዎች አንዱ ምክንያት ይኼ ነው:: ማንኛውም ተቋም (ድርጅት) ከመጀመሩ በፊት ቤተሰብ ተጀምሮ ነበር። እግዚአብሔር ቅድሚያ የሰጠውን ቤተሰብ እኛ ከሁሉ የመጨረሻ እንዳናደርገው ጌታ ይርዳን። አሜን።

*የቃል ጥናት ጥቅስ፣ "«ወደ ቤትህ በቤተሰቦችህ ዘንድ ሄደህ ጌታ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገልህ እንዴትስ እንደማረህ አውራላቸው አለው።»* (*ማር. 5:19*)

ግጥምጥም:- ቅድሚያ ለሚገባው ቅድሚያውን ሰጥቼ
ምሬትን ላስወግድ ከቤተሰቦቼ::

*ኢያሱ 24:15*
*ኢሳ. 8:18*

# የጎዳና ልጆች

ለባኪው የጋብቻ ትምህርት ለመማር ለተሰበሰቡበት ሰዎች ሁሉ እንዲህ እያሉ ትምህርታቸውን ቀጠሉ:: «ጋብቻ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ነው:: ከጋብቻ በፊት ያለ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ሲሆን፣ ከጋብቻ በኋላ ግን ንጹሕና የተቀደሰ ነው:: ከጋብቻ በፊት ልጅ መውለድ እንደሌለብን እንደምናውቅ ሁሉ፣ ከጋብቻ በኋላም የምንወልዳቸውን ልጆች ወስነንና አራርቀን መውለድ እንዳለብን ማወቅ ይገባል:: ብዙ ልጆች ወልደን እንደሚገባ ባለማሳደግ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት፣ ለአገርም ሸክም የሆነ ሥራ መሥራት የለብንም:: መጽሐፍ ቅዱሳችንን በደንብ ብንመረምር የሚጋጨው ማሳደግ የማንችላቸውን ልጆች በአናት በእናቱ ወልዶ እንደሚገባ ካለማሳደጋችን ጋር እንጂ፣ የምንወልዳቸውን ልጆች ወስነንና አራርቀን እንውለድ ከሚለው ጋር አይደለም:: ዛሬ በአገራችን ያሉ የጎዳና ልጆችን ብንመለከት በአቅማችን ወስነንና አራርቀን ካለመውለዳችን፣ ኃላፊነታችንን እንደሚገባ ካለመወጣታችን የተነሣ ከየቤቶቻቸው ተፈናቅለው የተበተኑ እንደሆኑ እንረዳለን:: ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ላይ ሕዝቧን አጠንክራ ማስተማርና ሁለቱንም ተጋቢዎች ከጋብቻ በፊት የጋብቻ ትምህርት እንዲማሩ ማድረግ፣ ከተጋቡም በኋላ የሚወልዷቸውን ልጆች ስለ መወሰንና አራርቆ ስለ መውለድ የሚቻልበትን መንገድ ከሕክምና ባለሙያዎች እንዲረዱ መምከር አለባት::» ይህንንም ትምህርታቸውን በቀጣዩ ምሳሌ አብራሩ::

«አሥራ ሁለት ልጆችን ከመውለዳቸው የተነሣ የተቸገሩና ሌሎች ልጆችንም ላለመጨመር ያሰቡ ሁለት ባልና ሚስት ለየብቻ መተኛት ልጅ ላለመውለድ ዋና መፍትሔ ነው ብለው እርምጃ ወሰዱ:: አንድ ቀን አሥራ ሁለቱም ልጆች ሁለት ብርድ ልብስ እየተጋፈፉ ወለሉ ላይ ተኝተው ነበር:: በዚህ መካከል ትልቁ ልጅ ቁጭ ብሎ በብስጭት "ድራማውን" ያይ ነበር:: ብርድ ልብሱ ከአንድ ወገን ሲስቡት ከሌላ ወገን ባዶ ሲሆን፣ አንዱ ሲለብስ ሌላው ራቁቱን ሲሆን አየና ለምን ከገቢያቸው ጋር የተመጣጠኑ ልጆችን ቤተሰቦቹ እንዳልወለዱ በደረቁ ሌሊት ቁጭ ብሎ እየተበሳጨ አሰበ:: አባታቸውም ልጆቹ በተኙበት በኩል ዳር ዳሩን እግሩን በቀስታ እያነሣ ወደ ባለቤቱ መኝታ ቤት ሲያዘግም፣ ቁጭ ብሎ የሚጋፈፉትን ልጆች ድራማ ይከታተል የነበረው ትልቁ ልጅ አባቱን አየውና፣ "እኛ ብርድ ልብስና አንሶላ እዚህ

እንጋፈፋለን አንተ ሌላ ለመጨመር እያደባህ ትሄዳለህ፣ ተመለስ ብሎ መለሰው::»

አዎ፣ ማሳደግ የማንችለውን ልጅ መውለድ በእግዚአብሔርም በሰውም፣ በትውልድም ዘንድ ተወቃሽ ያደርገናልና እንጠንቀቅ:: በቀረልንም ዘመን ወስነንና አራርቀን በመውለድ የእግዚአብሔርን ስጦታዎች እንደሚገባ ማሳደግ እንድንችል ጌታ ይርዳን::

ግጥምጥም:- «ምድሪቱን ሙሉ» ብሎ ጌታ ቢልም፣

ተባብረን ነው እንጂ ብቻህን አትሞላም::

| |
|---|
| ልጅህን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም:: (ምሳሌ 22:6) |

# ከራስ በላይ ራስ

ሰባኪው፣ "ባልና ሚስት እንድንከተለው የተሰጠን መመሪያ በቃሉ ውስጥ ነው፤ ቃሉም እግዚአብሔር የክርስቶስ፣ ክርስቶስም የባል፣ ባልም የሚስት ራስ ነው ብሎ ማንም ሊሽረው የማይችለውን ደረጃ አስቀምጧል። በዘመናችን ግን ይህንን ስንሽር እንገኛለን። አንዳንድ ቤት ራስ ባል መሆኑ ቀርቶ ሚስት ሆና ትገኛለች። ስለሆነም እግዚአብሔር በቃሉ ያስቀመጠው ቅደም ተከተል ተዛብቷልና ቤቱ ሲበላሽ፣ ፍቅርና ሰላም ሲጠፉ ይታያል። መጽሐፍ ቅዱስ ባል ሚስቱን ይውደድ ሚስትም ለባሏ ትገዛ ነው የሚለው። ይህ መዛባት የለበትም። ሁሉም እንደ እግዚአብሔር ቃል ኃላፊነቱን እየተወጣ አንዱ ለሌላው በክርስቶስ ፍርሃት እየተገዛ ሲኖር ነውና የሚያምረው፣ ያለ ቦታችሁ የሌላ ሰው ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ ሁሉ ወንበሩን ልቀቁ። ያን ጊዜ ሰላም፣ በረከትና ደስታ ወደ ቤቶቻችሁ ይመጣሉ" ለሚለው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

መጋቢው በቤተ ክርስቲያናቸው ለጋብቻ ትምህርት ለተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ፣ «ጋብቻ የሚያምረው እግዚአብሔር ባስቀመጠው ሥርዓትና ደረጃ ሲሄድ ነው። የሚስት ራስ ባል ነውና፣ ራስ የሆናችሁ ሴቶች ዛሬ ሥራችሁን ቀይሩ» እያሉ ያስተምራሉ። በዚህ መካከልም አንድ የሚያስገርም ጥያቄ ተጠየቁ። «እስቲ ሴቶች የበላይ ሆነው የሚያስጨንቋችሁና የሚያዟችሁ፣ የቤቱን አስተዳደር ለሴቶች የለቀቃችሁ ሁሉ ተነሡ።» በዚህ ጊዜ በጉባኤው ውስጥ ያሉት ወንዶች በሙሉ ተነሡና አንድ ወንድ ብቻ ሳይነሣ ቀረ። መጋቢውም፣ «ጥሩ እንግዲህ አንድ ሰው ብቻ ነው ራስ ሆኖ ቤቱን በማስተዳደር ላይ ያለ። ሌሎቻችን በቤታችን ራስ ሴቶች ብቻ ናቸው ማለት ነው» ብለው ወደተቀመጠው ሰው ዘወር አሉና፣ "የእኔ ወንድም፣ አንተ ያልተነሣኸው የቤቱ ራስና አዛዥ እንደ ቃሉ አንተ ስለሆንክ ነው አይደል?" ቢሉት፣ "አይ፣ አይደለም። ሚስቴ እዚያ ጋ ሆና በምልክት እንዳትነሣ ብላኝ ነው" ብሎ መለሰ።

አዎ፣ ትዳር የሚያምረው እንደ ቃሉ ባል ራስ ሲሆን ነውና የባልን ራስነት ሚስቶች አትውሰዱ፤ ይልቁንም ኃላፊነቱን ወስዶ ባል እንዲመራ እርዳታ ልታደርጉለት ይገባል። ከባላችሁ የበለጠ ደመወዝና ትምህርት ስላላችሁ እንዲሁም አፈ-ጮሌ ስለሆናችሁ የባላችሁን ቦታ መውሰድ አትችሉም።

ግጥምጥም:- *ከራስ በላይ ራስ እንዳለ ተረድተህ*

*ትዳርህን ምራ እግዚአብሔርን ፈርተህ*

| |
|---|
| *ኤፌ. 5፡22* |
| *1ኛ ጴጥ. 3፡7* |

# አሽሙርና ትዳር

የጋብቻ አማካሪው ሁለቱን ወጣቶች ቁጭ አድርገው ለዘለቄታ ትዳራቸው የሚጠቅማቸውን ትምህርት እንዲህ እያሉ ያማክራሉ:: «እናንተ ወጣቶች በትዳር ዓለም ስትኖሩ ሁለት ነገሮች እወቁ:: አንዱ፣ የከትና የዘወትር ባሕርይ እንዳለ፣ የከቱ አሁን ያላችሁበት፣ የዘወትሩ ደግሞ በኋላ ስትጋቡ የሚወጣው ነው። ሌላው፣ ሁልጊዜም በግልጽነት ተነጋግራችሁ መጨረስ እንጂ በኩርፊያና በአሽሙር ንግግር እርስ በርስ እየተቆሳሰላችሁ መኖር እንደሌለባችሁ ነው::» በተጨማሪም ይህንን ምሳሌ አከሉበት::

«ሁለት በግልጽነትና በአሽሙር ንግግር ከአሥር ዓመት በላይ ቆይተው ልጆች ወልደው የተፋቱ ባልና ሚስት አውቃለሁ:: ሁልጊዜ ሚስት ከባሏ ምን እንደምትፈልግና እንደሚፈለግባት አታውቅም፣ እርሱም እንደዚሁ። ልጆችም ከወለዱ በኋላ ጭቅጭቁ በልጆች ሁሉ ፊት ስለ ዘለቀ ልጆች 'ባልና ሚስት' የሚባለውን ቋንቋ መስማት ያስፈራቸው ጀመር። በትምህርት ቤት እንኳን ከጓደኞቻቸው ጋር የባልና ሚስት ድራማ ሲሠራ ይህንን ገጸ-ባሕርይ ተላብሰው መሥራት አይፈልጉም። የአባትና እናታቸው መጥፎ ምሳሌ በአእምሮአቸው ተቀርጾባቸዋልና ልጆቻቸውን እንኳን በመልካም አስተምረው ማሳደግ አልቻሉም። አስታውሳለሁ በመጨረሻ እንኳን ለመለያየት ምክንያት የሆነው የሚስቲቱ የአሽሙር ንግግር ነበር። ታሪኩ እንዲሁ ነው። ልጁ ት/ቤት ሲማር አንድ ያልገባውን ጥያቄ ቤተሰብ አለኝ ጥያቄዬን ይመልሱልኛል ብሎ ይዞ ይመጣል። እናቱንም 'እማዬ ዛሬ በት/ቤት የሰው ዘር የመጣው ከዝንጀሮ ነው የሚል ትምህርት ተማርኩ፣ እና እኔ የመጣሁት ከዝንጀር ነው ማለት ነው? ' ብሎ ሲጠይቅ፣ እናት ቀናና ትክክለኛ የሆነውን ወይም ከዝንጀሮ አለመምጣቱን ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱ በአምሳሉ ከአፈር እንደ ሠራው በመናገር ፈንታ ቀና ብላ በቁጣ፣ 'እኔ ምን አባክ አውቅልሃለሁ፣ አባትህ ዘሮቹን አላስተዋወቀኝም ብላው አረፈች::»

አዎ፣ አብሮ መኖርን የመሰለ ከባድና ጥሩ ነገር የለም። ሁለት ባሕርይ በአንድ አስማምቶ ለማስኬድ የጌታ ጸጋ ያስፈልጋል። ግልጽነትና ቅ(ን)ነት፣ ንጹሕ ልብና ገርነት ያስፈልጋል። ያን ጊዜ ቤት ሰላም ይሆናል፣ ሰላማዊ፣ በፍቅርና በእውነት የታነጸ ዜጋን መተካት ይቻላል። ስለዚህም የዘወትሩን የባልና የሚስት ባሕሪ ከእኛ ጋር ያለማቋረጥ ሆኖ በሚረዳንና በሚያስችለን ጌታ እንድናልፈው እርሱ ራሱ ያግዘን። አሜን።

የቃል ጥናት ጥቅስ:- *«የሚያሳፍር ነገርም የስንፍና ንግግርም ወይም ዋዛ የማይገቡ ናቸው»* (ኤፌ. 5:4)::

ግጥምጥም:- እግዚአብሔር የጣላውን ለምን ትወዳለህ፣

በሰላም የሚያኖር ክርስቶስ እያለህ።

*ኤፌ. 4:25-32፣5:2*
*ገላ. 6:2*

# አንድ ሥጋ በሁለት አልጋ

መጋቢው፣ «በአደባባይ ሲዞር የነበረ ሰይጣን ዛሬ መልኩን ለውጦ በጓዳ ቤተሰብን እያፈረሰ ይገኛልና ተጠንቀቁ። ይኸውም ዋና ዓላማው የክርስቲያኖችን ጋብቻ ከቻለ ማፍረስ፣ ካልቻለም ጤና ማሳጣት ነው። ዛሬ ብዙ ባለትዳሮች እርስ በርስ ካለመስማማት የተነሣ በአንድ ቤት እየኖሩ ተለያይተዋል፣ ለስሙ ብቻ ባልና ሚስት ናቸው ግን ለየብቻ ይተኛሉ። ወገኖቼ፣ እናስተውል፣ ይህ የሰይጣን ሥራ ነው አንድ ሥጋ በሁለት አልጋ። አይተኛም እግዚአብሔር አምላክ ያጣመረውን ዓለም፣ ሥጋና ሰይጣን ሊለየው አይገባም። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚል ባልም ሚስቱን ሚስትም ባሏን እንደገዛ ሥጋቸው አድርገው ይወድዱ ዘንድ ይገባል (ኤፌ. 5:28)። ሰይጣን ዘዴውን በመጠቀም አንዳችንን በሌላችን ላይ ያስነሣል፣ አሳቡን እንድንፈጽም ባሕሪውን ያለብሰናል፣ እንድንጠላላ ያደርጋልና ንቁ፣ ነቅታችሁም ተቃወሙት» ለሚለው ስብከታቸው ይህንን ምሳሌ በማስከተል ተናገሩ።

«አንድ ጊዜ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን እያመለኩ እያለ ድንገት በአንድ ወጣት ውስጥ ክፉ መንፈስ ነበረና ቤተ ክርስቲያንን ይበጠብጣል። በጉኑ ያሉትን መማታት፣ መጮህ፣ መዘለልና መወራጨት ሲያበዛ አጠገቡ ያሉትም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ገና ያልበሰሉ ነበሩና ሊጠጉት ፈሩ። በዚህ ጊዜ አንድ አማኝ ከሌላው ረድፍ ተነሥቶ እየተንደረደረ መጣና ግጥም አድርጎ ይዞ 'ፀጥ በል' አለው። በወጣቱ ውስጥ ያለውም አጋንንት 'እነዚህ ሰዎች ሁሉ ከአጠገቤ በርግገው ሸሽተው አንተ እንዴት ልትደፍረኝ ቻልክ?' ቢለው፣ ሰውዬው እየተበሳጨ፣ 'የአንተ ታናሽ እኅት እቤት ስላለችኝ ተለማምጄሃለሁ' ብሎት አረፈ። (ታናሽ እኅት የሚላት እንደ ሰይጣን ባሕሪ ተላብሳ ቁም ስቅሉን የምታሳየውን ባለቤቱን ነበር)።»

እንባቢ ሆይ፣ ቤትህ ገነት ነው ወይስ ገሃነም? ገነት ከመሰለና ሰላም ከሰፈነበት አመስግን፣ ነገር ግን ገሃነም ከመሰለ ወይ አንተ ወይ ሚስትህ ወይም ሁለታችሁም የሰይጣንን አሳብና የዓለምን ፈቃድ ተከትላችኋልና ተመለሱ። እግዚአብሔር ጋብቻን ሲጀምረው በመረዳዳትና በመግባባት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈጽም እንጂ ትእዛዙን በመጣስ እንደ ሔዋን መሣሪያ ለመሆን አይደለምና እንጠንቀቅ። እግዚአብሔር ትዳርን እንደሚፈልገው መምራት እንድንችል ጌታ የሥጋ ሥራንና የሰይጣንን አሳብ በኃይሉና በችሎታው ያስወግድልን። አሜን።

*የቃል ጥናት ጥቅስ፦* «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን» (ዕብ. 13:4)።

| |
|---|
| መክ. 9:9 |
| ማቴ. 13 |

*ግጥምጥም፦* ከራስ በላይ ራስ እንዳለ ተረድተን፣
እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንኑር ተስማምተን።

# የባል ዘመድ በዓይኑ አመድ

መምህሩ፣ ስለ ትዳር መፍረስ ሲያስተምሩ እንዲህ አሉ፡- «ዛሬ የብዙዎች ትዳር ፈርሶ ልጆች የተበተኑት ወይም ከአንድ ጣራ በታች ባልና ሚስት እንደ ደባል ተኮራርፈው የሚኖሩት ለምንድን ነው? ብንል የምንጋጭባቸውን ነገሮች ጠንቅቀን አውቀን መፍትሔ ባለመፈለጋችን ወይም አውቀን በግዴለሽነት በመተዋችን ነው:: ለመሆኑ ከእነዚህ ነገሮች ዋና ዋናዎቹ ምንድን ናቸው? ገንዘብ፣ ግንኙነት /Communication/፣ ዘመድ፣ ግብረ-ሥጋ፣ ልጆች፣ መንፈሳዊነት ናቸው:: የእግዚአብሔር ቃል እነዚህን ሁሉ በጋራና በኅብረት፣ በመተሳሰብና በመረዳዳት እንድናከናውናቸው ያዘናል:: ያኔ የሁለቱ ተጋቢዎች ፍቅር ይጨምራል:: ለምሳሌ፣ ዘመድን ብንመለከት ብዙ ጊዜ ግጭት የሚያመጣው የባል ዘመዶች ቢሆኑ "የባል ዘመድ በዓይኑ አመድ" የሚለው ከቃሉ ያፈነገጠ አባባል አስወግደን በጋራ መፍትሔ መፈለግ አለብን::

ለዚህ ትልቁ ተዋናይ ሚስት ናት፤ የእርሱ ዘመዶች የእኔም ናቸው በማለት ልቧን ብትከፍትና የሚደረገው እርዳታ ሁሉ በእርሷ በኩል ቢፈጸም ሰላም ይመጣል:: ባልና ሚስት የሁለታቸውንም ደመወዝ ማወቅ አለባቸው:: ጊዜ ሰጥተውም ወጪያቸውን ከገቢያቸው ጋር ማጣጣም ያስፈልጋቸዋል:: የእኔ የሚሉት ሃብት አይኖርም፤ በባንክም ገንዘብ ሲያስቀምጡ በጋራ ስም እንጂ በአንዱ ወገን ብቻ መሆን የለበትም:: ሌላው ግንኙነት ነው:: በጋብቻ ግልጽነት የተሞላበት ንግግር ያስፈልጋል እንጂ አሽሙር ወይም ደካማ ጐንን እያነሡ በነገር መውጋት ተገቢም፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊም አይደለምና እናርም:: ሌላው ግብረ ሥጋ ነው:: ባልና ሚስትን የሚያጋጨው ይህንን አስደሳች ነገር ለማድረግ አለመነጋገር፣ ባህል፣ ይሉኝታና መተፋፈር ናቸው:: እነዚህን ማስወገድና አለመከላከል ፍቱን መድኃኒት ነው:: ሌላው ልጆች ናቸው:: እነዚህን የእግዚአብሔር ስጦታ ተገቢ ጊዜ በመስጠት በጋራ ማሳደግ እንጂ ለአንዱ ወገን ብቻ የሚተዉ ዕዳዎች አይደሉም:: የመጨረሻው ባልና ሚስትን የሚያጋጨው ነገር መንፈሳዊነት ነው:: ባል ወይም ሚስት፣ "ድሮም ቢሆን ያለኸው (ያለሽው) በእኔ ጸሎት ብቻ ነው" ብሎ በመውቀስ መንፈሳዊነትን አጉልቶ ከማሳየት ይልቅ፣ በደከመበት ወይም በደከመችበት እያበረታቱ አብሮ ማደግ ያስፈልጋል::

እንግዲህ ይህንን ሁሉ ለማድረግ ለትዳራችን ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል:: አለበለዚያ ሁሉንም አጥተነው እናድጋለን::» ስለዚህም ግሩም የሆነ ትምህርታቸው ማስረጃ እንዲሆን ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ ብለው ተናገሩ::

«በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ የሚሠራ አንድ ሰው ነበረ:: ታዲያ ሁልጊዜ ቅድሚያ የሚሰጠው ለሥራው ነበርና ባለቤቱና ልጆቹ ከእርሱ ጋር የሚያሳልፉበት ጊዜ አጡ:: በሌሊት ይወጣል፣ በውድቅት ይገባል:: ባለቤቱም ስለዚህ ጉዳይ አናገረችው፣ አልሰማትም:: አስመከረችው፣ አላሻሻለም:: መጨረሻ ላይ ቢብስባት አንተ ያገባኸው እኔን ሳይሆን ሥራህን ነውና ደህና ሁን ብላ ጥላው ሄደች:: ሴቲቱ ወደ ቤቷ እንድትመለስ ቤተ ክርስቲያንም ብዙ ሞከረች፣ ግን አልቻለችም:: ሰውየውንም ጥሩ ምሳሌ አይደለምና ከሥራህ ልቀቅ ብላ አባረረችው:: ሥራውንም ትዳሩንም በአንድ ላይ አጣ::»

ወገኖቼ ሆይ፣ ቅድሚያ ለትዳራችን እንስጥ:: የውጭ ጠንካራ መሠረት ውስጡ ነው:: ውስጡ ፈርሶ ውጩን ብንገነባ እርካታ የለውምና ለትዳራችን የሚገባውን ጊዜ እንድንሰጥ ጌታ ይርዳን::

ግጥምጥም:- እስቲ ተረጋጋ መብከንከንህን ተው፣

ጊዜ አለመስጠት ነው ቤትን የሚያፈርሰው::

የቃል ጥናት ጥቅስ: «... ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ::» (1ኛ ጴጥ. 3:7)

| |
|---|
| ኤፌ. 5:33 |
| 1ኛ ቆሮ. 7:3-5 |

# ጭድ የሌለው ጭቃ

**የቃል ጥናት ጥቅስ:** «ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፣
በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።» (ምሳ.22:6)

ቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናኗ የጋብቻ ትምህርት እንዲማሩ ባዘጋጀችው ፕሮግራም ላይ ስለ ልጆች አስተዳደግ የሚያስተምረው መምህር እዚያ ለተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ እንዲህ እያለ ማስተማር ጀመረ:: «በመጀመሪያ ደረጃ ጌታ ወደ እኔ ሲመጡ አትከልክሉአቸው ካላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ዋናዎቹ ልጆች ናቸው:: ልጆች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄዱ፣ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙና የሰንበት ትምህርት እንዲማሩ ፍቀዱላቸው፣ አበረታቷቸውም:: በእግዚአብሔር ቃል ተኮትኩተው ያደጉ ልጆች የቤተሰብ ተስፋዎች፣ የአገር ተረካቢዎችና የእግዚአብሔር ክብር መገለጫዎች ይሆናሉ:: በተቃራኒው ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ተኮትኩተው ያላደጉ ልጆች የቤተሰብ መከራዎች፣ የሀገር ሸክሞችና የሰይጣን ክብር መገለጫዎች፣ በአጠቃላይም "ጭድ የሌለው ጭቃ" ይሆናሉና በንዳችሁ የምታሳድጉአቸውን ልጆች ለሥጋቸው ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳቸውና ለአእምሮአቸውም ተጠንቀቁላቸው:: ባልና ሚስት በአሳብ በምትጋጩ ጊዜ በልጆች ፊት አትጨቃጨቁ፣ ወደ መኝታ ቤታችሁ ግቡ እንጂ:: በእግዚአብሔርና በልጆቻችሁ ፊት ቀናውንና የከበረውን አሳብ ሁልጊዜ ተነጋገሩ፣ እናንተ የልጆቻችሁ ምሳሌዎች ናችሁና:: ደግሞም የልጆች አእምሮ ያልደረቀ ሲሚንቶ መሆኑን አውቃችሁ በመልካም ነገር ቅረጹአቸው፣ ሲያድጉ ከዚያ ፈቀቅ አይሉምና::» ለዚህ ግሩምና ፈዋሽ ለሆነ ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ አስከትለው ተናገሩ::

«አባትና እናት ትንሹ ልጃቸው መካከላቸው እንዳለ ረስተው ወይም እንደዚህ ያደርጋል ብለው ባለመገመት እቤታቸው እየመጡ ስለሚጎበኙአቸው ቄስ አበላል ይነጋገራሉ:: "አይገርምም፣ እኚህ ቄስ ሲበሉ እኮ እንደ አሳማ ነው፣ የቀረበላቸውን ሁሉ አንድ ሳያስተርፉ ነው ጥርግ አድርገው የሚበሉት::" ይህንን ሲነጋገሩ የሰማና በአእምሮው የቀረጸው ልጅ አንድ ቀን ቄሱ በር ላይ ቆመው በር ሲያንኳኩ ሄዶ ከፈተላቸውና በሚከላተፈው አንደበቱ እንዲህ አላቸው:: "እንደ አሳማ የሚበሉት ቄስ እርስዎ ነዎት?" ቄሱም በቆሙበት ድርቅ ብለው፣ "ማን ነገረህ ልጄ?" ሲሉት፣ "እማዬና አባዬ ሲያወሩ ሰምቼ ነው" አላቸውና አረፈው::»

ለመሆኑ፣ ልጆቻችንን እንዴት ነው እያሳደግን ያለነው? አእምሮአቸውን በመልካም ነገር እየገነባን ነው ወይስ መልካሙን ነገር ከአእምሮአቸው እያጋባን? ከክፉ ነገር እየመለስን ወይስ ሳናውቀው ክፉ ነገር እየከለስን? የልጆቻችን መጀመሪያ መጨረሻውን ይወስናልና ከመጀመሪያው እንድንጠነቀቅላቸው ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ልጅ በልጅነቱ ሲስተካከል ያምራል፣
ካደገ በኋላ ሲሰበር ይችላል::

ምሳሌ 23:13
ምሳሌ 17:6

# የእርግዝና መከላከያ ዘዴ

ሰባኪው ስለ እርግዝና መከላከያ ዘዴ ሲያስተምሩ እንዲህ አሉ:: «የዛሬ ቤተ ክርስቲያን ከማውገዝ ይልቅ ማስተማርን ልማዷ ማድረግ አለባት:: ስለሆነም ዛሬ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ስለ ጋብቻ እና ልጆችን መጥኖ ስለ መውለድ በግልጽ እንማራለን:: ጋብቻ በመተሳሰብና በመረዳዳት አብረን የምንኖርበት ተቋም ነው:: ጋብቻ ማለት የግልን ጥቅም በጋራ ጥቅም የምንለውጥበት የጋራ ስምምነት ነው:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ትዳርን ስንመለከት ተቃራኒውን ነው የምናገኘው:: ለምሳሌ፣ እዚህ ላይ ልጆችን መጥኖ ስለ መውለድ ሲነሣ ባሎች ፈቃደኛ አይሆኑም:: ልጅ ባናት ባናቱ ካልተወለደ ትዳሩ ትዳር አይመስላቸውም:: ይህ ደግሞ ወላጆችን በተለይም እናትና ልጆቹን ራሳቸውን ይጉዳል:: ስለዚህ ትዳር የፍቅርና የመተሳሰብ ተቋም ነው ካልን፣ ለሚስትም ማሰብ አለብን እንጂ ማኅጸኗን የተከራየን ይመስል በየዓመቱ ልጅን እንድትወልድ ማስገደድ የለብንም:: ደግሞ ለተወለደው ልጅ የሚገባውን አለማድረግ እኮ ኃጢአት ነውና እንጠንቀቅ:: የዚህ ዘመን ልጆች በድላቸው የሚያድጉ ብቻ ሳይሆን፣ በድሎትም የሚያድጉ መሆናቸውን አንርሳ:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያንን አገልጋዮችና የሕክምና ባለሙያዎችን በማማከር የእርግዝና መከላከያ መጠቀም ጥበብ ነው እንጂ ኃጢአት አይደለም:: ይህ ሆኖ ባይገኝ የወለድናቸውን ልጆች ማሳደግ አቅቶን፣ "ለምን ወለድከኝ" የሚል የዘላለም ጠባሳና ወቀሳ በራሳቸው በልጆቹ ይቀርባልና እንጠንቀቅ:: አገርን የሚያለሙ እንጂ አገርን የሚያወድሙ ልጆች አንውለድ::» ለዚህም ግሩም ለሆነ ምክራቸው ማጠናከሪያ ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

አሥር ልጆች የወለዱ ባልና ሚስት ሌላ ተጨማሪ ልጆች እንዳይወልዱ ማቆም እንዳለባቸው ተመካከሩ:: ለጊዜውም የደረሱበት የእርግዝና መከላከያ ዘዴ ለየብቻ መተኛት ሆነና ለየብቻ መተኛት ቀጠሉ:: ነገር ግን አንድ ቀን ባልየው ለብቻው ተኝቶ እስከ መቼም እንደማይዘልቀው በመረዳት ቃል ኪዳኑን ጥሶ ከአንደኛው ክፍል በሳሎን ቤት አቋርጦ ወደ መኝታ ቤታቸው ለመዝለቅ በዝግታ ድምፅ ተራመደ:: አሥሩም ልጆች የለበሷት ብርድ ልብስ አልበቃቸው ብላ ከአንዱ ጫፍ ወደ ሌላው ጫፍ እየሳቡ ግማሹ ሲለብስ ግማሹ ባዶ ሲሆን ትልቁ ልጁ በንዴት ተበሳጭቶ ቁጭ ብሎ ይህንን ሁሉ ድራማ ይመለከት የነበር ይኸው ልጅ አባቱ ወደ እናቱ እንደሚሄድ አወቀና በከፍተኛ ድምጽ ጮኾ እንዲህ አለው:- «እኛ ብርድ ልብስ አንሶን እንገፋፋለን አንተ ሌላ ልትጨምር በደረቅ ሌሊት ታደባለህ፣ ተመለስ!» አለው::

አዎ፣ በእኛ አለማወቅና ንዝህላልነት ወይም የእርግዝና መከላከያን ዘዴ መጠቀም እንደ ኃጢአት በሚቆጥር ከቃሉ ጋር በማይሄድ አጉል መንፈሳዊነት ተሸብበን የትውልድ ተወቃሾች እንዳንሆን ልንጠነቀቅና እንደ እባብ ብልህ እንደ ርግብ የዋህ ልንሆን ያስፈልገናል:: እንዲህ እንድንሆንም ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ማሳደግ እምችለውን ወልጄ ብነሣ፣
እኔም እድናለሁ ከትውልድ ወቀሳ::

| |
|---|
| መዝ. 127፣3 |
| ኢሳ. 8:18 |

## *ክፍል 2*
## *እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ኅብረትና ፍቅር*
# አንድ ብር ለአንድ ወገን

ሰባኪው ስለ መስጠት እንዲህ ብለው አስተማሩ:: «የመጨረሻው ጊዜ ደርሶ እኛ ወደ ጌታ ወይም ጌታ ወደ እኛ መጥቶ ወደ ዘላለሙ ቤታችን እስክንሰበሰብ ድረስ በዚህ ዓለም ላይ ስንኖር እርስ በርሳችን ተዛዝነንና ተሳስበን ልንኖር ይገባል:: ያለ ምንም ስስት ያለንን ለወገኖቻችን በማካፈል የእነርሱ ችግር ችግራችን ሊሆን ይገባል:: መስጠት መንግሥት ሰማይ የሚያስገባ የደኅንነት ሥራ ባይሆንም፣ የዳነ ሰው ግን መስጠት ይጠበቅበታልና እንትጋ:: ዛሬ ዓለም፣ "አንድ ብር ለአንድ ወገን" እያለች ሕዝብን ከረሃብ ለማትረፍ በምትሯሯጥበት ጊዜ እያንዳንዱ ሰው አብሮ በዘመቻው ሊሳተፍ ይገባል እንጂ በስስት ቆፈን ተይዘን እጃችንን አጣምረን ከዳር ቆመን ማየት አይገባንም:: የእግዚአብሔር ሰው መቼም ቢሆን ከእኔ ይልቅ ለወንድሜ በሚል መልካም አሳብ መሸቀዳደም አለበት እንጂ፣ ሁልጊዜ የማይሞላውንና እንደ መሰላል የተያያዘውን ምኞቱን ብቻ እየተከተለ በመስጠት የሚገኘውን በረከት ሊያጣ አይገባውም:: ሁልጊዜም ሁሉም ሰው ራሱን ሳያስቀድም ወንድሙን ቢያስቀድም ምድራችን የረሃብ ምድር ሳትሆን የበረከትና የፈውስ ምድር ትሆናለች::» ለዚህም ግሩም ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተጠቀሙ::

«ሁለት ጓደኛሞች ምግብ ቤት ውስጥ ገብተው ምግብ አዝዘው ምሳቸውን እየበሉ ሳለ ሁለቱም በውስጣቸው አንድ ፈተና ውስጥ ገብተዋል:: በቀረበላቸው ትሪ ላይ አንድ ትልቅና ትንሽም ዓሣ አብሮ ስላለ የትኛውን እንደሚወስዱ ሁለቱም ተቸግረዋል:: በዚህ መካከል የትሪው እንጀራ አልቆ ዓሣዎቹ ብቻ ስለቀሩ እንደተመኘው አንደኛው ትልቁን ዓሣ ብድግ አድርጎ መብላት ሲጀምር፣ ሁለተኛው ተቆጥቶ እንዲህ ማለት ጀመረ፣ "አንተን ሁልጊዜ ታዝቤሃለሁ:: ራስ ወዳድ ነህ፣ ለእኔ ብቻ ለእኔ ብቻ ነው የምትለው፣ ጓደኛህን አታስቀድምም ስስታም ነህ" እያለ የነገር ናዳውን አወረደበት:: ጓደኛ ውም ዓሣውን መብላቱን ቆም አደረገና፣ "ቆይ እስቲ እሺ አንተ ብትሆን የትኛ ውን ዓሣ ነበር የምትበላው?" ቢለው፣ "ትንሹን" አለ:: በዚህ ጊዜ፣ "ታዲያ ምን ያስቆጣሃል፣ የቀረውስ ትንሹ አይደለም ወይ ለምን እርሱን አትበላም?" ብሎት አረፈው::»

አዎ፣ ወገኖቼ፣ «ከእኔ ይልቅ ወንድሜ» የሚለውን ግሩም አመለካከት በተግባር እንጂ በአፋችን ብቻ አንግለጸው:: ሁልጊዜም የእኛን ጥቅም ብቻ ለሚያመጣ ነገር ራሳችንን አንስጥ፣ ለባልንጀራችንም ጭምር እንጂ:: እግዚአብሔርም ይርዳን::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፣
ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ!!» (ፊልጵ. 2:4)::

ግጥምጥም:- ለእኔ ለእኔ ማለት ስስቱ ይብቃና፣
ወንድሜን ላስቀድም ልሁን ከእርሱ ኋላ::

ያዕ. 2:14-17
1ኛ ዮሐ. 3:17

# አምስቱ ካልሲዎች!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ» (ገላ. 6:2)::

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥረው እርስ በርሱ እየተረዳዳና እየተደጋገፈ ፈጣሪውን በንጹሕ፣ ግብዝነትና ከንቱ ትምክህት በሌለበት አኳኋን እንዲያመልከው ነው:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ዛሬ ግን እየኖርን ያለነው ምናልባት ከዚህ የራቀ ይሆን? እርስ በርሳችን እንደ ቃሉ ፍቅር ሊኖረንና ልንተሳሰብ ይገባል:: ሰውን ማትረፍ የሚቻለው በፍቅር ሥራ ነውና? ይህንን ከማድረግ አንጉደል:: ክርስቶስ እኛን ገንዘቡ ያደረገን ራሱን በመሠዋት የፍቅር ሥራ በመስቀል ላይ ሠርቶ ነውና እኛም የእርሱን ፈለግ ተከትለን ዋጋ በመክፈል ወንድማችንን ገንዘብ ማድረግ እንድንችል ጌታ ይርዳን» ለሚለው መልእክታቸው በወጣትነት ዘመናቸው የገጠማቸውንና በድል ያለፉትን ታሪክ እንዲህ ብለው ተናገሩ::

«ትዳር ከመመሥረታችን በፊት የቤት ኪራይ እንዲቀንስልን ሦስት ጓደኛ ሞች አብረን በጋራ ቤት ተከራየን:: በጥሩ ሁኔታ እየኖርን ሳለ በመካከላችን ግን አንድ ችግር እየጎላ መጣ:: ከሦስታችን አንደኛው ወንድም ካልሲውን አያጥብምና ቤቱ መሽተት ልማዱ ሆነ:: አምስት ካልሲዎች ስላሉት በየተራ ያደርጋል፣ አንዱ ሲቆሽሽ ከአልጋው ሥር ይወረውርና ሌላውን ያደርጋል:: እንዲህ እያለ የአምስቱን ካልሲዎች ዙር ሲጨርስ የመጀመሪያው ካልሲ ደርቆ ይጠብቀዋል:: እንደገና ሳይታጠብ ለሁለተኛ ዙር ይደረጋል:: እንዲህ እያለ አምስቱንም ካልሲ ያደርጋል:: በአጭሩ እኛ ቤት ሰው ሲመጣ ከሞተ ከአንድ ሳምንት የሆነው ድመት ያለ ይመስላል - ግማቱ:: በዚህ ጊዜ ሁለታችንም ተማከርን:: "ጥለነው ወጥተን ሌላ ቤት ብቻችንን ከምንከራይ እና ወንድማችንን ከምናጣው ለምን ካልሲውን አናጥብለትም" ተባባልን:: ማታ እርሱ ከተኛ በኋላ የመጥረጊያ ጉራጅ እንጨት ይዘን ከአልጋው ሥር ያሉትን ካልሲዎች ከየአድራሻቸው ከሰበሰብን በኋላ አጥበን ውጭ አሰጣን:: ጠዋትም እርሱ ሳይነሣ አምስቱንም ካልሲዎች ራስጌው አጠገብ ያለችው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጥን:: እርሱም ከመኝታው በሚነሣበት ጊዜ ሁሉም ካልሲዎች "ዜግነታቸውን ቀይረውና" አምሮባቸው ተመለከተና ምንም ሳይናገር አራቱን ሳጥኑ ውስጥ ከቶ፣ አንዱን አድርጎ ሄደ:: ማታ ከሥራ ሲመጣ የመጀመሪያ ተግባሩ ካልሲውን አውጥቶ ማጠብ ሆነ:: እንዲህ አድርገን ወንድማችንን ገንዘብ አደረግነው:: በቤታችንም በጥሩ መዓዛ በእረፍት መኖር ጀመርን::»

አዎ ወገኖቼ፣ ወገናችንን ገንዘብ ማድረግ የምንችለው እርሱን ከነሸክሙ በመግፋት ሳይሆን ዋጋ ከፍለን ዝቅ ብለን ሸክሙን፣ ችግሩን፣ ረሃቡን በመጋራትና በማገዝ ነውና ይህንን እንድናደርግ ጌታ ይርዳን::

ግጥምጥም:- ይልቁን ልሸከም የወንድሜን ሸክም፣
በጉድፉ ምክንያት ዓይኑን ማውጣት ላቁም::

| |
|---|
| ዮሐ. 13:34-35፤ 15:12 |

# ጉንዳን ከተባበረ ወንዝ ይሻገራል!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው» (1ኛ ዮሐ. 1:3)::

መጋቢው፣ «እግዚአብሔር ሲፈጥረን በኅብረት፣ በመስማማትና በአንድ ልብ ሆነን እንድናመልከውና እንድናገለግለው ነው እንጂ፣ በተለያዩ በራሳችን ሥጋዊ ምክንያቶች ተለያይተን የጎሪጥ እየተያየን እንድንኖር አይደለም:: ዛሬ ሰይጣን የተባረከውን ኅብረታችንን ለማፍረስ ብዙ መንገዶችን እየተጠቀመ ነው፤ ቋንቋችንን፣ ስማችንን (ዝናችንን)፣ ውበታችንን፣ ዘራችንን፣ አገራችንን ሁሉ አጉልቶ በማሳየት ለዚህ ዋጋ ለሌው ግሳንግስ ነገር ዋጋ ሲያስከፍለን ይታያል:: በዚህ እግዚአብሔር አይከብርምና ሰውን ሁሉ በክርስቶስ አውቀን ክብራችንን፣ ዝናችንን፣ ቋንቋችንን እና ቤተ ክርስቲያንን ሁሉ ለእግዚአብሔር በማስገዛት በኅብረትና በፍቅር ልናመልከውና ልናገለግለው ያስፈልጋል:: በቀጣዩ ሕይወታችን የእኔነትን መንፈስ አስወግደን በጋራ እየገፋ ያለውን፣ አገሪቱን ድንበራችንን በራሱ ለማድረግ ሌት ተቀን በዐመፅ አሠራሩ ደፋ ቀና የሚለውን ጠላታችንን ልንመክትና ብሎም ልናጠፋ ይገባናል» ለሚለው መሠረታዊ ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ::

«ሰባት ልጆች ያሏቸው አንድ አባት በሞት አፋፍ ላይ ሆነው ልጆቻቸው ሁሉ እያንዳንዳቸው አንድ አንድ አርጩሜ ይዘው እንዲመጡ አዘዙ:: ከመጡ በኋላ ሁሉም ያመጡትን አርጩሜ በእርሳቸው ፊት በጉልበታቸው እንዲሰብሩ አዘዙ:: ሁሉም የራሱን ሰበረ:: እንደገናም ሌላ ሰባት አርጩሜ እንዲያመጡ አዘዙ:: አርጩሜ ማመላለስ ሊሞት ለሚያጣጥር ሰው ጥቅሙ ምን እንደሆነ ምሥጢሩ ባይገባቸውም፣ አሁንም የአባታቸውን ፈቃድ ለመሙላት ሄደው አመጡ:: አሁን አባታቸው እንዲህ አሉአቸው:: "ሰባቱንም በአንድ ላይ እሠሩና አንዳችሁ በጉልበታችሁ ለመስበር ሞክሩ::" እንደተባለው ለማድረግ ሞከሩ፣ ግን መስበር አልቻሉም:: በዚህ ጊዜ አባታቸው፣ "እያችሁ፣ ልጆቼ ለእናንተ ያለኝ የመጨረሻ የኑዛዜ ቃል ይህ ነው:: ጠላትን በተናጠል ማጥቃት አትችሉምና ኅብረት ይኑራችሁ:: ልጆቼ ስሙ፣ ጉንዳን ከተባበረ ወንዝ ይሻገራልና ተባበሩ፣ ተያያዙ፣ ተዋደዱ፣ ተጠያየቁ፣ ተነፋፈቁ፣ ያን ጊዜ በጠላት ወረዳ ላይ የበረታችሁ አሸናፊዎች ትሆናላችሁ::"»

አዎ፣ እኛም ሰው ከሰው ሳንለይና ሳንለያይ ሰው ሁሉ በውስጡ የእግዚአብሔር እስትንፋስ እንዳለበት ተረድተን፣ ለዚህም ሰው እግዚአብሔር ቋንቋውን እና ዝርያውን የሰጠው ለመግባቢያና ለመለያ መሆኑን አውቀን ቤተ ክርስቲያን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተቀራርበን፣ መሪ ከመሪ ጋር ተያይዘን በኅብረትና በአንድነት እግዚአብሔርን ልናገለግል ይገባናል:: ይህ ከሆነ ሽንፈት ለጠላት፣ ድል ለሕዝቡ ይሆናል:: ቀሪው ዘመናችን የኅብረት፣ የአንድነትና የፍቅር ይሁንልን:: አሜን!

ግጥምጥም:- በኅብረት ለኅብረት ለፈጠረኝ ጌታ፣
ራሴን ሳስገዛ፣ ለምን ልንገላታ::

ዮሐ. 3:17-11
ፊልጵ. 2:1-2

# ፍቅር እውር ነው

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወድዳል» (ምሳሌ 17:17)::

የታደሙት ሰዎች አዳራሹን ግጥም አድርገው ሞልተውታል:: ከፊት ለፊት ከሰባኪው ትይዩ የዕለቱ ሙሽሮች በክብር ልብሳቸው ተሰይመው፣ በሚዜዎቻቸው ታጅበው ጎልተው ይታያሉ:: የዕለቱም ሰባኪ ከፍ ባለ ድምፃቸው እነርሱንና ጉባኤውን ከእግዚአብሔር ቃል ያስተምራሉ:: «ፍቅራችሁ ጊዜያዊና ወረት የዳሰሰው አይሁን:: እውነተኛ ወዳጅ በሁኔታዎች አይለወጥም:: ዛሬ ብዙ ሰዎች ፍቅራቸው ከሚጠፋ ነገር ጋር የተያያዘ ነው:: የሚጠፋው ነገር ሲጠፋ ወዳጅነታቸውም ይጠፋል:: ዛሬ ከአንዱ ወዳጅነት ይጀምራሉ፣ ነገ አቋርጠው ወደ ሌላው ይሄዳሉ:: ይህ ደግሞ ኃጢአት ነው:: ፍቅራችሁ እስከወዲያኛው ይዝለቅ» እያሉ ያስተምራሉ:: ይህንን ትምህርት በምሳሌ አስረግጠው ሲናገሩ እንዲህ ይሉ ነበር::

«በአንድ አካባቢ ወ/ሮ አየለች የሚባሉ ሴት አራት ፎቅ ያለው ቤት ጀመሩና እስከ አራተኛ ፎቅ ድረስ ለመጨረስ የገንዘብ አቅማቸው ስላልፈቀደ ከሰሙን (ምሰሶዎቹን) ብቻ አቁመው ተዉት:: ለረጅም ዓመታት ሳይሠራ በመቅረቱ በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ የታወቀ ሆነ:: እንዲያውም ይባስ ብሎ ነዋሪው እርስ በርስ ላለመከዳዳት ቃል ኪዳን ሲገባባ አንዱ የአንዱን እጅ ይይዝና፣ "እንደ አየለች ፎቅ ጀምሮ ያስቀረኝ አልክድህም" እያለ መማያ አደረገው::»

አዎ፣ እኛስ ዛሬ ከአንዷ ጋር ጀምረን ዓመት ሳይሞላ ነገ ከሌላዋ ጋር እያልን «እንደ አየለች ፎቅ» ጀምረን የተውነው ብዙ የፍቅር ዕዳ ይኖርብን ይሆን? እንመለስ ወይም ይህንን ሥራችንን እንተው:: እውነተኛ ፍቅር ሙሉና ዘላቂ ነው፤ ጎደሎ አይደለም:: «ፍቅር እውር ነው» እንደሚባለው ሳይሆን ፍቅር ዐይናማና ሙሉ ነው:: ሁኔታን አይቶ አይለወጥም፣ ወይም በሁኔታዎች አይቀየርም:: ፍቅር የራሱን አይፈልግም:: በግብዝነትና በወረት የታጀበን ፍቅር አስወግደን በእውነትና በንጹሕ ልብ እርስ በርሳችን ተዋደን እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆናችንን ለዓለም በመመስከር ዘመናችንን እንድንፈጽም ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ፍቅር ዕውር ነው ለምን ትላላችሁ፣
ፍቅር ዐይናማ ነው እዩ አስተውላችሁ::

| |
|---|
| ሉቃ. 10:29-37 |
| 1ኛ ቆሮ. 13:4-8 |
| ዮሐ. 13:35 |

# ከእኔ በላይ ላሳር

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን...» (ሮሜ 12:6)

በየዓመቱ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለአገልጋዮች በምታዘጋጀው የአገልጋዮች የትምህርት ጊዜ ላይ ተገኝተው መጋቢው እንዲህ እያሉ ማስተማር ጀመሩ:- «አገልጋዮች በተሰጠን ጸጋ መሠረት እያገለገልን የሌላውንም ጸጋ ልናከብር ይገባናል እንጂ በቅንአትና በምቀኝነት የሌላውን ጸጋ ማንቋሸሽ የለብንም:: ጌታ ለሁላችንም የተለያዩ ስጦታ የሰጠው ለቤተ ክርስቲያን ጥቅምና ክብር እንጂ ለራሳችን አይደለምና ክብር ለራሳችን በመውሰድና በመኩፈስ ከእኔ በላይ ላሳር ማለት የለብንም:: በሁሉም ሰዎች ላይ እግዚአብሔር የሚጠቅም የጸጋ ስጦታ እና ብቁ ችሎታ ሰጥቷልና በየትኛውም ሰው ይሁን በየትኛውም የጸጋ ስጦታ አገልግሎት ይህኛው ከዚህኛው ይበልጣል፤ ያንሳል የምንለው መኖር የለበትም::» ለዚህ ግሩም ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ::

«አገርን በመጎብኘት ላይ ያሉ አንድ ፈላስፋ ትልቁን ወንዙ በጀልባ እያሻገራቸው ላለው ገበሬ እንዲህ እያሉ ጥያቄ መጠየቅ ጀመሩ:: "እኔ የታወቅሁ ፈላስፋ ነኝ፣ ብዙ ታዋቂነት በዚህች ዓለም ላይ አለኝ፣ ብዙ ሥራዎችንም በችሎታዬ ሠርቻለሁ:: ለመሆኑ አንተ የምትታወቅበት ሥራ ምንድን ነው?" ቢሉት፣ "ምንም" አለ:: "የእድሜህን ግማሹን አልኖርክማ" አሉት:: አሁንም ሌሎችም የተለያዩ ጥያቄዎችን ጠየቁት፤ እርሱም ምንም እንዳልሠራ በነገራቸው ጊዜ ሁሉ እየደጋገሙ በተከታታይ፣ "የዕድሜህን ግማሹን አልኖርክማ" እያሉ ሲሉት መጨረሻ ላይ ተበሳጨና ከወንዙ መሐል ላይ እንዳሉ እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው፣ "ጌታዬ፣ አሁን ለምሳሌ ከፊታችን ይህችን ጀልባ ሊገለብጥ የሚችል ማዕበል እየመጣ ነው:: እኔ ዋና እችላለሁ፣ ለመሆኑ እርስዎስ ዋና ይችላሉ?" አላቸው:: በዚህ ጊዜ ፈላስፋው እያፈሩና እየተደናገጡ፣ "አልችልም" አሉት:: ገበሬውም በመደሰት፣ "በቃ ከእንግዲህ በኋላ የዕድሜዎን ግማሹን አልኖሩትም" ብሎ መለሰላቸው ይባላል::»

አዎ፣ አንዳችን ውስጥ የሌለው ስጦታ በሌላችን ውስጥ አለና እየተደጋገፍንና እየተመካከርን በቀና እና በመቀባበል መንፈስ እናገልግል እንጂ እርስ በርሳችን እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ:: ይልቁንም በትሕትናና በተዋረደ መንፈስ የስጦታውን ባለቤት እግዚአብሔርንና የእርሱን ሕዝብ እንድናገለግል ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ስጦታው የእግዚአብሔር መሆኑን እውቁ፣
ከወንድሜ ጋራ ልኑር ተጠንቅቁ::

| |
|---|
| ሮሜ 12:3-5 |
| ሮሜ 12:10 |

# ክፍል 3
# እግዚአብሔርን ስለ ማመስገን

## ወንደላጤውና ድመቷ

ሰባኪው፣ «መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ያለ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁላችን ሁሉን እንመረምራለን እንጂ በማንም አንመረመርም። ስለሆነም በዚህ ምድር ላይ በሕይወታችን ላይ በሚገጥሙን መሰናክሎች ወይም አለመሳካቶች ላይ የእግዚአብሔር የመጨረሻው ፈቃዱ ምንድን ነው ብለን መመርመር፣ መጸለይ እና ማስተዋል አለብን እንጂ ገና ከመጀመሪያው ተስፋ ቆርጠን መቆዘም የለብንም። ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ ከደረሰብን ክፉ ነገር ባሻገር መልካም ነገር እንዳለ እናስብ። ከትጋሚን ኪሣራ ሩት እንደ ወጣች ሁሉ፣ ከእኛም ኪሣራ (ጉዳት) መልካም ነገር ይገኛል። እግዚአብሔር በመጀመሪያ መጨረሻውን ያውቃልና ሁልጊዜ በደረሰብን ነገር ሁሉ እናመስግን እንጂ አናጉረምርም፤ በመጨረሻው ፈውስ፣ በረከት፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ጸጥታና ሕይወት ነውና» ለሚለው ግሩም ስብከታቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

የገናን በዓል ለማክበር ሁሉም ሰው ከቤተሰቡ ጋር ምንም ሳይጎድል ቤቱን ሞቅ አድርጎ ለመዋል በጉን፣ ዶሮውንና፣ ቅርጫውን ለማስገባት ይሯሯጣል። አንድ ትዳር ያልመሠረተ ወንደላጤም እኔስ ከማን አንሼ በማለት ቅርጫ ገባና ሥጋውን በዘንቢሉ ወደ ቤቱ ይዞ ገብቶ አንድ ሙዳ ጠብሶ ለመብላት መከተፊያው ላይ አስቀምጦ ቢላዋ ለማምጣት ወደ ጓዳ ሲገባ፣ አንዲት ድመት ገብታ ያንን ሙዳ ሥጋ በአፈር ላይ እየጎተተች ወደ ውጭ ይዛ ትወጣለች። ወንደላጤው ቢላዋ ይዞ ከጓዳ ሲወጣ ሙዳ ሥጋው የለም። ወደ ውጭ ሲመለከት ድመቷ ትጎትታለች። በጣም ተበሳጭቶ በያዘው ቢላዋ የዘራችውን ሊያሳጭዳት ተከትሎ ሲሮጥ ሥጋውን ይዛ ጢሻ ውስጥ ገባች። በዚህ በጣም ተናዶ ወደ ቤቱ ሲመለስ፣ የቤቱ ጣራ እንዳለ ተደርምሶ ቤቱ ወድቋል። በዚህ ጊዜ ወንደላጤው የቤት ፍርስራሽ ተጭኖት ታፍኖ አለመሞቱን እያሰበ እንዲህ አለ። «ለካ አምላኬ ድመት ልኮ ሥጋዬን ያስወሰደው፣ እኔን ከቤት አውጥቶ ሥጋዬን ለማዳን ነው» ሲል አምላክን አመሰገነ።

እም፣ ሁልጊዜ የነገሮቻችን መጀመሪያና መጨረሻ አንድ አይሆንምና እናስተውል። እግዚአብሔር በራሳቸው በጎ ያልሆኑትን ነገሮች ሁሉ ለበጎ መለወጥ ይችላልና አሁን ያለንበትን መጥፎ ሁኔታ እግዚአብሔር መጨረሻውን ወደ መልካም ያመራና በረከት ያለበት ያደርገዋልና እርሱን እንጠብቅ። ይህንንም እንድናስተውል እግዚአብሔር በጸጋው ይደግፈን። አሜን።

የቃል ጥናት ጥቅስ፦ «ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም» (ኤር. 29:11)።

ግጥምጥም፦ አምላኬን ልጠብቅ ምንም ነገር ቢሆን፣
እንደ መጀመሪያው መጨረሻው አይሆን።

| |
|---|
| ኢዮብ 42:2 |
| መዝ. 107:13 |

# ሠላሳ - ሁለት ጥርስ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና» (1ኛ ተሰ. 5:18)::

መጋቢው፤ «የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእኛ ምንድን ነው? ብለን ስንጠይቅ፣ ቃሉ "በነገር ሁሉ እያመሰገናችሁ እንድትኖሩ ነው" የሚል ግልጽ የሆነ ምላሽ ይሰጠናል:: የእኛ ተግባራዊ ምላሽ ታዲያ በነገር ሁሉ ከማመስገን ይልቅ ማጉረምረም ይሆን? ሰይጣን፣ ከሆነልን ይልቅ የሆነብንን አጉልቶ ያሳየንና ከምስጋና ይልቅ አጉረምራሚዎች እንድንሆን ያደርገናል:: የእግዚአብሔር ቃል ግን፣ "በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ" (ፊልጵ. 4:6) ይላል:: ወገኖቼ፣ እግዚአብሔር የሚፈልገው ትውልድ ሲሆንለት ብቻ ሳይሆን ሳይሆንለትም የሚያመሰግን፣ ሲሞላ ብቻ ሳይሆን ሲጎድልም የሚያመሰግን፣ በነገር ሁሉ በምስጋና የተሞላን እንጂ በነገር ሁሉ በማጉረምረም የተሞላን አይደለምና እስኪ ለምስጋና እንነሣ:: በምስጋና ድል ይገኛል:: የሚያመሰግን ሕዝብ ሩጫውን ይጨርሳልና በነገር ሁሉ ጌታ ሁላችንንም አመስጋኞች ያድርገን» ለሚለው ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

ከሠላሳ ሁለት ጥርሳቸው ሁለት ጥርስ ብቻ የቀራቸው አሮጊት በአንድ የጸሎት ፕሮግራም ላይ ከጎኑ ቁጭ ብለው ሲያመሰግኑ የሰማቸው ወጣት ከጸሎቱ ፕሮግራም በኋላ፣ «እኔ ሠላሳ ሁለቱም ጥርሴ ግጥም ብሎ እያለ አንድ ቀን ትዝ ብሎኝ አመስግኜ አላውቅም፣ እርስዎ ግን ሠላሳውን አጥተው በሁለቱ ብቻ የሚያመሰግኑበት ይህ ምሥጢር ምንድን ነው?» ሲል ገርሞት ጠየቃቸው:: አሮጊቷም እንዲህ ሲሉ መለሱ፣ «ልጄ፣ እኔ የማመሰግነው እኮ ሁለት ጥርስ ስላለኝ ብቻ ሳይሆን፣ መንከስ እንዲችሉ አንዱን ከላይ አንዱን ከታች ስላደረገልኝም ጭምር ነው» ብለውት አረፉ::

አዎ፣ ወገኖቼ ሆይ፣ እግዚአብሔርን በነገር ሁሉ እናመስግን ካልን ያለንን እንቁጠር፣ በሁሉም እርሱን እናመስግን:: አሁን የሆንነውን የሆንነው ከጌታ ምሕረትና ጥበቃ፣ ከቸርነቱም የተነሣ ነውና በነገር ሁሉ እርሱን አመስግነን ጠላትን ማሳፈር እንድንችል ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ሲሞላ ማመስገን ሲጎድል ማማረር፣
ይበቃል ይቋረጥ እንዲህ ያለ ነገር::

መዝ. 92:1
መዝ. 118:1

## ክፍል 4

## ለእግዚአብሔር ስለ መኖር

# የኃለሞታ ልብስ

ሰባኪው: «ዛሬ የምናገረው መልእክት ለምንሰማው፣ ለምናየውና ለምናደርገው ነገር ሁሉ ጥንቃቄ እንድንወስድ ነው። ኃጢአት በዓይንና በጆሮ ገብቶ ነውና ልብን የሚለውጠው፣ በየቀኑ ለምንሰማውና ለምናየው ልንጠነቀቅ ይገባል። ሔዋን ፍሬው ለመብላት እንደሚያስጎመጅ አይታ ነው በኃጢአት የወደቀችው። ዳዊት ቤርሳቤህ ስትታጠብ አይቶ ነው በኃጢአት የወደቀው። ስለዚህ እኛም ሆንን ቤተሰቦቻችን ለምናየውና ለምንሰማው ልንጠነቀቅና ልናስጠነቅቅ ይገባል። የማየትና የመስማት ኃጢአት ወደ ተግባር ለመውሰድ ኃይል አለው። በተለይም በአሁን ሰዓት ሰይጣን ክርስቲያኖችን እየጣለ ያለው በዝሙት ነው። ለዚህ የሚጠቀምበት አቋራጭ መንገዱ የዝሙት ፊልም በማሳየት እና የኃለሞታ ልብስ በማልበስ ነውና እኛም ሆንን ልጆቻችን የምናያቸውን ፊልሞች እንመርምር። በተለይ እግዚአብሔር የሰጠንን ልጆች እንደ እግዚአብሔር ቃል ቀርጾ አሳድጎ ለእግዚአብሔር ሠራተኞች እንዲሆኑ የማብቃት ኃላፊነት አለብንና። ወላጆች ልጆቻችንን ብዙ አንራቅ፤ የሚያነቡት፣ የሚያዩትና የሚሰሙት ሁሉ ጽድቅን የሚያሳይ መሆኑን እንይ፣ እናሳይ፣ እንመርምር፤ ካልሆነም እንመለስ። በአጠቃላይ ሰይጣን ዛሬ እኛን ወደ ኃጢአት ለማስገባት ቴክኖሎጂውንም እየተጠቀመ ነውና የምናየውን ቴሌቪዥን፣ የምናነበውን ጋዜጣ፣ የምንላላክበትን ኢንተርኔት እና የምንሰማውን ሬድዮ ሁሉ ልንመረምር ይገባል። ፍሬውንም ከገለባው ለይተን ልንወስድና በሕይወታችን እግዚአብሔርን ልናከብር ይገባል» ለሚለው የጊዜው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

«እድሜያቸው ከመግፋቱ የተነሣ እቤት የዋሉትን እናቱን ማገላበጡ፣ ማውጣት ማግባቱ፣ ማቅናት ማስተኛቱ እጅጉን አድክሞታል። ብቻውንም ስለሆነ በጣሙን አሰልችቶታል። ታዲያ በዚህ ሁኔታ እያለ አንድ ሰው ሊፈትነው ወደ እርሱ መጣና፣ "እናትህን ትሸጣለህ ወይ?" ብሎ ጠየቀው። በጣም የደነገጠውም ልጅ፣ "እናቴን ያሳደገችኝን! ምን ዓይነት ሰይጣን ነህ? በል ሂድ ከአጠገቤ" ይልና ያባርረዋል። ትንሽም ሲያስብ ሲያሰላስል በጆሮው የሰማው ቃል ወደ ልቡም ሄደና ይስተናገድ ጀመረ። ገንዘብ ካወጣች ለምን አትሸጥም አለና ሮጦ በመከተል ሰውዬውን ጠርቶ፣ "ለመሆኑ ስንት ታወጣለች?" ብሎ ጠየቀ።»

አዎ፣ የምናየውና የምንሰማው ቃል ውስጣችን ገብቶ የመለወጥ ኃይል አለውና ለምንሰማውና ለምናየው ሁሉ አብዝተን ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል። ጌታም ለሁላችን ማስተዋሉን ይስጠን።

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ልጄ ሆይ፣ ወደ ጥበቤ አድምጥ ጆሮህን ወደ ትምህርቴ መልስ።» (ምሳሌ 5:1)

> «ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ»
> (ኢዮብ 31:1)

# አልማዝ ባለጭራ

መጋቢው፣ «በምድር ላይ ብንኖርም የተጠራነው "የሰማያዊ ኑሮ" እንድንኖር ነው እንጂ የምድራዊ ኑሮ እንድንኖር አይደለምና እግዚአብሔርን የማያስከብሩ ምድራዊ ምኞቶቻችንን ልንገድል ይገባል:: ዛሬም በምድራችን ኤች አይ ቪ/ ኤድስ፣ ሳርስ፣ አልማዝ ባለጭራ እያልን ስም የምንሰጣቸው ወረርሽኞች ሁሉ የመጡብን ክፉ ምኞቶቻችንን ማለት ዝሙትን፣ ርኩሰትን፣ ጣዖት ማምለክን፣ ሌሎችንም ስለአልገደልንና በንጽሕናና በቅድስና ስሙን ከሚጠሩት ጋር ስለአልተባበርን ነው:: ስለዚህ ዛሬ መልእክቴን የምትሰሙ እናንተ ሁላችሁ አሮጌውን ማንነታችንን ወይም አሮጌውን ሰው አስወግደን አዲሱን ማንነታችንን እርሱም ክርስቶስን እንልበስ:: እግዚአብሔር "ግደላቸው"፣ "አጥፋቸው"፣ "ምታቸው" ያለንን የማይጠቅሙንን ባሕርይዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ እናጥፋ እንጂ እየቀናነስን አናድርግ:: ፈጽሞ መግደል ያለብንን አሁኑኑ እንግደል::» ይህንን መልእክት ሳዘጋጅ አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጸመ ድርጊት ትዝ አለኝ::

«ጊዜው የፋሲካ ሰሞን ስለሆነ ቤተ ክርስቲያኒቱ በውስጧ ለሚገኙ ችግረኞች በሬ ገዝታ ሥጋ ለማከፋፈል አሰባለች:: በዕለቱም የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ይህንን ኃላፊነት ይወስዱና በሬው ተጥሎ ይታረዳል:: ነገር ግን በሬውን የሚያርዱ አራጆች ብዙ ልምድ የሌላቸው ኖሮ፣ ታርዷል ተብሎ የተገመተው በሬ ለካ ጉሮሮው አልተቆረጠም ነበርና ድንገት ተነሥቶ ደሙን እያዘራ በግቢው ውስጥ መሮጥ ጀመረ:: በዚህ ጊዜ አገልጋዮች ሁሉ እየተከተሉ "በኢየሱስ ስም! በኢየሱስ ስም" እያሉ መገሠጽ ጀመሩ::»

አዎ ወገኖቼ፣ መጀመሪያውኑ መግደል ሲገባን የእኛን ኃላፊነት ሳንወጣ የጌታን ስም ለመጥራት አንቸኩል:: ጌታ በቃሉ በምድር ያሉ ምድራዊ ብልቶቻችሁን ግደሉ ነው ያለው እንጂ እኔ እገድልላችኋለሁ አላለምና የእኛን ድርሻ እንወጣ:: አራጆቹ በያዙት ቢላዋ በሬውን እስከ መጨረሻው ማረድና መግደል እንደ ነበረባቸው ሁሉ፣ እኛም በተሰጠን ቃል፣ በመንፈሱና በጸሎት እግዚአብሔርን የማያስከብረውን በውስጣችን ያለውን ዓለማዊ ባሕርያችንን እንድንገድል ጌታ ይርዳን:: አሜን::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እንግዲህ በምድር ያሉ ብልቶቻችሁን ግደሉ እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት ፍትወት፣ ክፉ ምኞት፣ ጣዖትን ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው» (ቆላ. 3:5)::

ቆላ. 3:8-9
ኤፌ. 5:3

ግጥምጥም:- «በምድር ላይ ኖሬ ምድራዊ እንዳልሆን፣
አዲሱን ሰው ልብስ ላውልቅ አሮጌውን::

# ሴትን ክጃለሁ!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ፣ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ» (ዮሐ. 8:11)።

ሰባኪው፣ «ዛሬ ሕይወታችንን እያቀጨጨ ያለው ምንድን ነው? ለሚለው የብዙዎቻችን ጥያቄ ምላሹን ይገኘ መጥቻለሁ። ይኸውም ለዚህ ያበቃንን ኃጢአት ከሥር ከመሠረቱ መንግሎ በማውጣት መካድ ነው። በሚቀጥለው አዲስ ዓመት እንዲህ እሆናለሁ ወይም አደርጋለሁ ብለን አዲስን ነገር ለእኛና ለቤታችን ተመኝተን አዲሱ ዓመት አሮጌ ሆኖ ሲያልቅ ግን ምኞታችን ሁሉ የውኃ ሽታ ሆኖ እንዳምናው ዘንድሮም ሕይወታችን ያው የሆነው ለምንድን ነው? የልምምድ ኃጢአታችንን እስከ መጨረሻው ስላልካድን ነው፣ ወይም ስላላወቅን ነው፣ ወይም ብንክድም ከሀደቱ ከልብ አልነበረምና ተመልሰን በዚያው ኃጢአት ተይዘን ነው። ወገኖች፣ ዛሬ በዕለት ተዕለት ኑሮአችን በጌታ ፊት ስንገዝ «ምንም አይደለም» እያልን የምንሠራቸው ጥቃቅን ኃጢአቶች ሁሉ በጌታ ፊት ጎልተው ሕይወታችንን እያቀጨጩት፣ እንደ ምስጥ ውስጥ ውስጡን እየቦረቦሩን ይገኛሉና ጥቃቅኑን ቀበሮዎች አጥምደን በመያዝ አላሳድገንና ከጌታ ጋር አላገናኘን ያለውን አንቆ የያዘንን የልምምድ ኃጢአታችንን አሁን ልንክደው ይገባል» ለሚለው መሠረታዊና ግሩም ስብከታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«ቤተ ክርስቲያኒቱ ባዘጋጀችው ዓመታዊ ታላቅ የወንጌል ስርጭት ኮንፈረንስ ላይ የደጎንነት የወንጌል ስብከት ሰባኪው ከሰበከ በኋላ ጥሪ ሲያቀርቡ፣ "ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጣችሁ ብትኖሩ ከዘላለም የገሃነም እሳት መዳን የሚቻለው ስለ እኛ በሞተው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነውና አሁን እጸልይላችኋለሁ፣ እየተነሣችሁ ወደ ፊት ኑ" አሉ። በዚህ ጊዜ አንድ ሰው በፍጥነት ከመቀመጫቸው ተነሥተው ወደ ሰባኪው መጡ። ሰባኪውም፣ "እኔ የምለውን ከእኔ ቀጥለው በማለት ንስሐ ይግቡ" ብሏቸው እንዲህ እያለ ቀጠለ። "ጌታ ኢየሱስ ሆይ"፣ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ"፣ "አንተን አምናለሁ።" "አንተን አምናለሁ።" "ዓለምን ክጃለሁ፣" "ዓለምን ክጃለሁ፣" "ሰይጣንን ክጃለሁ፣" "ሴትን ክጃለሁ"፤ በዚህ ጊዜ ሰባኪው "ሰይጣንን ክጃለሁ በሉ ነው ያልኩት እንጂ ሴትን ክጃለሁ አላልኩም" ቢሏቸው። "እባክህ ተወኝ፣ በዝሙትዋ ቆላልፋ ከጌታዬ ጋር አላገናኝ ያለችኝን ጠላቴን እኔ አውቃለሁና ጸሎትህን ቀጥል" ብለውት አረፉ።»

አዎ ወገኖቼ፣ ሁሉ ጊዜ ሕይወታችንን እያቀጨጨ አላሳድግ ያለንንና ከጌታችን ጋር ያለንን ኅብረት የሚያሻክርብንን የልምምድ ኃጢአት ማወቅ አንድ ድል ነው። ዛሬ ለዘላለም እንካደው። ውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ ደግመን እንዳናደርገው አምላክ ይርዳን። አሜን።

ግጥምጥም:- የልምምድ ኃጢአት ሕይወቴን ጎድቶታል፣
ክጃለሁ ከእንግዲህ አምላኬ አይቶታል።

| |
|---|
| ሉቃስ 3:7-9 |
| ያዕ. 5:16 |

# ክፍል 5

## ስለ እግዚአብሔር አዳኝነት

# ሰይጣንን በቆመጥ

የቃል ጥቅስ:- «እነሆም፣ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» (ሉቃ. 24:48)::

ሰባኪው፣ «ማንም ሰው ከላይ በሚያገኘው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል እንጂ ከታች በሚያገኘው የሥጋ ኃይል ሰይጣንን ሊያሸንፍና በአገልግሎቱ የተሳካለት ሊሆን ፈጽሞ እንደማይችል አገልጋዮች ሁላችን ይህንን ማወቅና ለዚህም መገዛት አለብን:: ለዚህ ነው ቃሉ፣ "ማንም ሰው ሲያገለግል እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ይበል::" (ሉቃስ 17:10) ተብሎ የተጻፈው:: ደቀ መዛሙርት ከሰማይ ጌታ በላከላቸው ኃይል ሮጡ፣ ግን አልደከሙም፤ ተፍገመገሙ፣ ግን አልወደቁም፤ ወንጌልን ሰበኩ፤ እስከ ሞት ድረስም የታመኑ ሆኑ:: እኛስ ዛሬ የምናገለግለው በማን ኃይል ነው? በማንስ እውቀት ነው? መማር፣ ማወቅና የብዙ ዲግሪዎች ባለቤት መሆን ግሩም ነው:: ነገር ግን እነዚህን ሁሉ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል ካላስገዛን ውጤቱ ያማረ አይሆንም:: ለእኛ ለክርስቲያኖች ያለን ጠላት በሥጋ ኃይል የሚረታ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚሸነፍ መሆኑን ማወቅ በራሱ ድል ነው::» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

በከተማው እምብርት ባለው ስቴዲዮም ላይ ታላቁ ኮንፈረንስ መካሄዱን ቀጥሏል:: መዘምራኑ ከዘመሩ በኋላ ሰባኪውም በጌታ ድንቅ ኃይል ስብከታቸውን ሰበኩ:: በመጨረሻም የደኅንነት ጥሪ ካደረጉ በኋላ ለበሽተኞች ሲጸልዩ በሽተኞች መፈወስ ጀመሩ:: አጋንንት ከያሉበት እየጮኹ መውጣት ጀመሩ:: ስቴዲዮሙ በቅዱሳንና በርኩሳን ጩኸት ተደበላለቀ:: በዚህ ጊዜ መድረኩ አካባቢ ለአስተናጋጆች ያስቸገረውን፣ አጋንንት ያደረበትንና የያዙትን ሰዎች ለመማታት የሚወራጨውን አንድ ወጣት በጊዜው የስቴዲዮሙን ጸጥታ ለመጠበቅ ከተሰማሩት ፖሊሶች አንዱ አየውና ተንደርድሮ ሄዶ በያዘው ቆመጥ ሁለት ጊዜ ሲመታው ሰባኪው አዩና እንዲህ አሉ:: <ተው በሥጋ ኃይል ርኩስ መንፈስን ልታስወጣ አትችልም:: ሰይጣንንም በቆመጥ ልታሸንፈው አትችልምና ወደ እግዚአብሔር መንፈስ አምጣው> ብለው ጸለዩለትና ወጣቱ ነፃ ወጣ::»

አዎ ወገኖቼ፣የሥጋ ኃይል የመንፈስን ኃይል ሊቋቋም አይችልምና ወደ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል እንምጣ እርሱንም ታጥቀን በእኛ ያሉትን ሥጋዊ ቆመጦቻችንን አስወግደን እንድናገለግለው ጌታ ይርዳን::

ግጥምጥም:- የእኔን ኃይል በኃይልህ ጌታ ግዛውና፣
ምርኮን ከጠላቴ ልበዝብዝ ልውጣና::

የሐዋ. 1:8
1ኛ ጴጥ. 5:8

# መስተፋቅር በሎሚ

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር ስለ እኛ ይዋጋል። እግዚአብሔር ግን በጦርነቱ አሸናፊ እንዲሆን እኛ በቅድስናና በጽድቅ እርሱንም በመምሰል ልንኖር የግድ ነው። የእግዚአብሔር ኃይል በሰይጣን ኃይል ላይ ጥሶ እንዲወጣ መውጣት መግባታችን እንደ ቃሉ እና እንደ መንፈስ ፈቃድ ሊሆን ይገባል። ይህ ከሆነ ሰይጣን ዲያቢሎስ በእኛ ላይ የሚያሴረው ሴራ ይከሽፋል፣ የለጠጠው ቀስቱም ይሰበራል። እግዚአብሔርም በልጆቹ ሕይወት ላይ ከፍ ብሎ በዚህች ዓለም ላይ ይከብራል።» ለሚለው ሕይወት ለዋጭ ስብከታቸው ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተናገሩ:-

በአንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የክርስቶስን ሕይወት በሕይወቷ የምትመሰክር ታማኝ ክርስቲያን ልጅ ነበረች። በሥጋም ውብ ነበረችና ብዙ ወንዶች ተማሪዎች ይሳቡባታል። ግማሹ ለጊዜው፣ ግማሹ ለዘለቄታ እንደሚወዷት ይገልጹላታል። እርሷ ግን ሁሉንም በቀና መንፈስ እንዲህ ዓይነት ዓላማ ለጊዜው እንደሌላትና ትምህርቷን ብቻ መማር እንደምትፈልግ ትገልጽላቸው ነበር። አንድ በግቢው በመጥፎ ባሕሪው የሚታወቅ ወጠምሻ ተማሪ ግን ጠንቋይ ቤት ሄዶ መስተፋቅር በሎሚ አስደግሞ አመጣና በጓደኛዋ በኩል ላከላት። ለጓደኛዋም እንዲህ ብሎ አስጠነቀቃት፣ «እነዚህ ሁለት ሎሚዎች ላንቺና ለጓደኛሽ ናቸው። እንደነገርኩሽ ይኸኛው ምልክት ያለበት ሎሚ መስተፋቅር የተደገመበት የእርሷ ሎሚ ነው። ይኸኛው ምንም ምልክት የሌለው ደግሞ ያንቺ ነው። አደራ ተሳስተሽ የእርሷን እንዳትበይና ጉድ እንዳትሠሪኝ።» ይላትና ይሰጣታል። እርሷም እሺ ትልና በእረፍት ሰዓት ለጓደኛዋ ሎሚ እንደገዛችላት ትነግራትና ትሰጣታለች። ይህችም አማኝ ልጅ ስላደረገችላት በጎ ነገር ጓደኛዋን እያመሰገነች በእጇ ሎሚውን ሳትመጠው ይዛው ሳለ ከእርሷ ጋር ሁልጊዜ ለመቀለድ የሚፈልግ አንድ ሌላ ተማሪ ከእጇ ላይ መንትፎ ይዞ ይሮጣል። በዚህ ጊዜ ያቺ ጓደኛዋ ምሥጢሩን ስለምታውቅ እየተከተለች መጮኽ ጀመረች፣ ኧረ መልስ፣ ተው እንዳትመጠው፣ አለበት፣ አለበት፣ እያለች።» ልጁ ግን ያለችውን ሳያስተውል፣» ይኑርበት፣ ይኑርበት» እያለ ሎሚውን መርጦ ጨረሰው።

አዎ፣ እግዚአብሔር በየዋህ ልጆቹ ላይና ያለ ነውርና ነቀፋ በቅድስና በሚመላለሱ ልጆቹ ላይ ሰይጣን የደገሰውን ድግስ እንዲህ አድርጎ ያከሽፋል። ዛሬም በአንተ ሕይወት ሰይጣን ብዙ ነገር ያደርጋል። ግን በበጉ ደምና በመልካም የሕይወት ምስክርነት ድል እንድትነሣው ጌታ ይርዳህ፡ አሜን

የቃል ጥናት ጥቅስ፡ «በያዕቆብ ላይ አስማት የለም፣
በእስራኤልም ላይ ምዋርት የለም» (ዘኍል. 23:23)

ግጥምጥም:- ጌታን እያከበርኩ እኔ ስመላለስ፣
እርሱ ያከሽፈዋል የጠላቴን ድግስ።

መዝ. 124:6
ዘኍል. 23:21

# አጋንንቱና ሥራ አስኪያጁ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ፣ ደስ ይበላችሁ::» (ፊልጵ. 4:4)

መምህሩ ለመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎቻቸው ወደ ዕለቱ ትምህርት ከመሄዳችን በፊት አንድ ቃል ላካፍላችሁ ብለው ፊልጵ. 4:4 አንብበው እንዲህ አሉ::

«ጌታን በማመናችሁና በመከተላችሁ የተነሣ በሰዎች የተናቃችሁና ስፍራ የማይሰጣችሁ ከሆነ፣ በጌታ ደስ ይበላችሁ:: ምክንያቱም በጌታ የከበራችሁ በሰይጣን ደግሞ የተፈራችሁ ናችሁና:: አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ:: አማኝ ከመሆኑ የተነሣ በመሥሪያ ቤቱ ስፍራ የማይሰጠው፣ ከጨለማው ሥራ ጋር ባለመተባበሩ ጓደኞቹ የሚያገሉት፣ ነገር ግን በእግዚአብሔርና በሥራው ዘንድ ታማኝ የሆነ አንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ የሚሠራ ሰው ነበረ:: ሁልጊዜ በሰዎች ዘንድ የከበሬታ ቦታ አልነበረውም፣ በጌታ ዘንድ ግን ነበረው: አንድ ቀን እግዚአብሔር ይህን ባሪያውን አሰበ:: ስሙንም ድንገት በሥራ ገበታው ላይ እያለ ይጥለዋል፣ አረፋም ይደፍቃል:: የሥራ ባልደረቦቹ ተደናግጠው ይሸከሙና እየተሯሯጡ ወደ ሥራ አስኪያጁ ቢሮ ይዘውት ይመጣሉ:: ሥራ አስኪያጁም ተደናግጠው ከመቀመጫቸው እየተነሡ፣ "ምንድን ነው? ምንድን ነው? ወደ እኔ ይዛችሁ የምትመጡት" ይሏቸዋል:: ሰዎቹም፣ "ይህን ሰው አጋንንት ጥሎት ነው፤ አንድ መላ ይበሉ" ይሏቸዋል:: ሥራ አስኪያጁም እየተርበተበቱና የሰውየው አጋንንት ወደ እርሳቸው የሚዛመት እየመሰላቸው ቀጭን ትእዛዝ ሰጡ:: "ይህንን ሰው እዛ መጋዘኑ ጋ ወዳለው ጴንጤ ይዛችሁ ሂዱ:: እርሱ ጋ ነው ለዚህ ችግር መፍትሔና መድኃኒት ያለው እንጂ፣ እኔ ጋ ምንም የለም" ብለው መለሱ:: ሰውየውንም እዛ ወሰዱትና አማኙ ጸልዮለት ተፈወሰ:: እናንተ ጋ መፍትሔ አለና በጌታ ደስ ይበላችሁ:: እናንተ ጋ ለበሽተኞች መድኃኒት፣ ለተራቡት ጥጋብ፣ ለተጠሙት እርካታ አለና በጌታ ደስ ይበላችሁ:: ዛሬ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና እንደ ቃሉ በመሄዳችሁ ምክንያት በሰዎች የተናቃችሁ፣ ስፍራ የሌላችሁ ትሆኑ ይሆን? የምስራች በእግዚአብሔር ዘንድ የከበራችሁ ናችሁና ደስ ይበላችሁ::» መምህሩ የህንን ካሉ በኋላ ትምህርታቸውን ማስተማር ቀጠሉ::

አዎ፣ ወገኔ ሆይ፣ ዛሬ በምን ሁኔታ ላይ ትገኝ ይሆን? ከላይ እንደተጠቀሰው አማኝ በሰዎች የተናቅህ ሆነህ ቢሆን፤ በጌታ የከበርህ ነህና ደስ ይበልህ! በሰዎች ስፍራ የሌለህ ቢሆን፣ በጌታ ስፍራ አለህና ደስ ይበልህ! ክርስቶስ ከሌላቸው የዓለም ታላላቆች የማይገኝ ታላቅ ነገር በእኛ አለና ደስ ይበለን:: ይህንንም አስተውለን እንድናልፍ ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- የልጅነት ሥልጣን ተሰጥቶሃልና፣
ተጠቀም በስሙ የክርስቶስ ባሪያ::

ሮሜ 8:28፤ 2ኛ ነገ. 6:16
ዘፍጥ. 39:9

## ጥቁር አባቡሌ

ሰባኪው በክፍላቸው ተራ ቆመው ስለ እምነት እንዲህ እያሉ ያስተምራሉ:-

«ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም (ዕብ. 11:6):: በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ብዙ የምንታመንባቸው ነገሮች ይኖራሉ:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር ውጭ ከሆኑ እርሱን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም:: አንዳንድ ሰዎች በሰይጣን ያምናሉ፤ ሌሎች በገንዘባቸው ይታመናሉ፤ ሌሎች ደግሞ በጠንቋይ፣ ሌሎች ደግሞ በሌላ በሌላ:: ይህ ሁሉ ለሕይወታችን ፋይዳ የለውም:: ሲጠሩት የሚሰማውንና የሚረዳውን፣ ከዘላለም ሥቃይና ሞት የሚያድነውን፣ በሰይጣንና በመንግሥቱ ላይ በድል ተጫምተን እንድንኖር በሚያደርገው በእግዚአብሔር ብቻ ታመኑ:: እርሱ ደግሞ ለታመኑበት ታማኝ ነው:: ማንንም አይንቅም::» ስብከታቸውን በትጋት ለሚሰማቸው ጉባኤ ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ::

በሕፃናት የሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ ከጓደኞቹ ጋር እየተገኘ የሚማር አንድ ትንሽ ልጅ ነበረ:: ምንም እንኳን ቤተሰቦቹ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰይጣን እያደሩ ቢቃወሙትም፣ እርሱ ግን መማሩን ቀጠለ:: ታዲያ ገና ከልጅነቱ እግዚአብሔር ልቡናውንና አእምሮውን ከፍቶለታልና በመንፈሳዊነቱ እያደገ ሄደ:: ቤተሰቦቹ እንዳይጸልይ በቤት ስለከለከሉት በትልቁ ቁምሳጥን ውስጥ እየተደበቀ ቁምሳጥን ሳያግደው ለሚሰማው አባቱ መጸለይ ጀመረ:: አባቱ ለወትሯቸው ጠንቋይ ቤት መሄድ ይወዳሉ:: ነገር ግን ከዚህ ልጅ ጸሎት ወዲህ አጋንንቱ እንዳይሠራ ታግዷል:: እንደተለመደው አንድ ቀን ጠንቋይ ቤት ለማስጠንቀል ሄደው አባቱ በጠንቋይ አገልጋዩ በኩል ጥቁር አባቡሌ የሚለዩ ጊዜያዊ ስም ተሰጥቷቸው ወደ ጠንቋዩ መጋረጃ በተራቸው ተጠርተው በቀረቡ ጊዜ ጠንቋዩ በጩኸት ድምፅ፣ «ጥቁር አባቡሌ መጀመሪያ በቤትህ ያለውን እሳት አጥፍተህ ናና እፈውስሃለሁ::» አላቸው:: በዚህ ጊዜ ቤት ሄደው ሚስታቸውን እሳት ቢጠይቁ ከምድጃው እሳት በስተቀር ሌላ የለም:: እርሱኑ በሁለት እንስራ ውኃ ቸልሰው አጠፉና ሄዱ:: በዚህ መሃል ሚስት ቅዳሜ ጠዋት ገበያ ልትሄድ ገንዘብ ልታወጣ ቁምሳጥኑን ስትከፍት ማሙሽ ኩርትም ብሎ ይጸልያል:: ደነገጠችና፣ «ልጄ አንተ ነህ ለዚያ ጠንቋይ እሳት ሆነህ የምታስጨንቀው:: ነገሩ እንዲህማ ከሆነ ና ሳሎን ቤት

ጸልይ::" አለችው:: አባትየውም ጠንቋዩ ጋ ሄዶ በቀረቡ ጊዜ፣ "ምንም እሳት የለም" አሉት:: ጠንቋዩም "ምንም እሳት የለም ትላለህ፣ አሁንማ እሳቱ ከቁምሳጥን ወጥቶ ቤቱን ሞልቶታል::" አሉ:: አባትየውም እየተናደዱ እቤት ሲመጡ የሆነውን ታሪክ ሁሉ ከባለቤታቸው ሰሙ:: ከዚያም፣ "በልጃችን ውስጥ ያለው እሳት ኃይል ከጠንቋዩ የበለጠ ከሆነማ፣ እኛም በልጃችን አምላክ ከዛሬ ጀምሮ እንታመናለን::" አሉ::

አዎ፣ አምላካችን ስታመኑበት በእውነት የታማኝ ሰው፣ እርሱ ማንንም አይንቅም፣ ይልቁንም ጠላትን አዋርዶ ልጆቹን ከፍ ከፍ ያደርጋል፣ ያጸናልም:: በእንደዚህ ዓይነት ኃይል ጌታ ላይ ታምነንና ታውቀን የሰይጣንን መንግሥት እያስጨነቅን የእምነት ሩጫችንን በድል እንድንፈጽም እግዚአብሔር ራሱ ጸጋውን ያብዛልን:: አሜን::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን አንተ ልጅ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው::» (ማር. 2:5)

ግጥምጥም:- ለጠንቋዩ ጠንቋይ ለምን ትሆናለህ?

መንግሥቱን የሚያፈርስ ሥልጣኑ ተሰጥቶህ::

ዕብ. 11:1
ዘኁል. 23:23

# ፈታኙን እምቢ በል

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም።» (ኤር. 29:11)

ሰባኪው: ፈታኙን እምቢ ስለማለት ሲያስተምሩ እንዲህ አሉ፣ «መቼም በሕይወታችን የክፉ ክፉ ብለን የምንለው አሳቢና ተቆርቋሪ የመሰለ ጎጂ ጠላት ሲኖረን ነው። ለእኛ ለክርስቲያኖችም አሳቢ የመሰለው ጎጂ ጠላታችን ሰይጣን ነው። ሰይጣን ዛሬ ብዙ እኛን የማጥቂያ መንገዶች ዘርግቷል። ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው አሳቢ መስሎ መቅረቡ ነው። ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈተናውን ያቀረበው እንዲህ ብሎ ነው፣ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፣ እነዚህን ድንጋዮች ወደ እንጀራ ለውጠህ ብላ! (ማቴ. 4:3) እዚህ ጋ ሰይጣን አሳቢ፣ ተቆርቋሪና አዛኝ መስሎ ነው የቀረበው። ዛሬም "የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሽ እንዴት እስካሁን አላገባሽም? ሰው በ18 ዓመቱ ያገባል፣ አንቺ ግን ይኸውና ሁለት አሥራ ስምንት ደፍነሻል። ለምን ያንን ዓለማዊ ሰው አታገቢም። ወደ ጌታ ታመጪዋለሽ፤ ብቻሽን ከመሆን ይሻልሻል፤ ይህንን ዓለም ብቻሽን አትገፊውም" ብሎ አሳቢ ሆኖ መርዙን በማር ቀብቶ ያመጣል። ለአንዳንዱ ደግሞ፣ ለምን ጉቦ አትበላም። ከአንተ በኋላ የተቀጠሩ ይኸው በዓመታቸው ፎቅና ምድር ቤት ሲሠሩ፣ አንተ ይኸው አሥር ዓመትህ እስካሁንም ለምድር ቤቱ ተቸግረህ ነው ያለኸው> ይለዋል። በዚህ ሁሉ፣ "እግዚአብሔር ይገሥጽህ፣ አምላኬ ለእኔ በጽድቅና በትክክለኛው መንገድ የሚያዘጋጅልኝ ይሻለኛልና አልፈልግም።" ብላችሁ ፈታኙን ተቃወሙ።» ለዚህ ግሩምና መሠረታዊ ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ:-

አንድ ወጣት ክርስቲያን በአንዲት ኮረዳ ላይ የሰፈረውን አጋንንት በጌታ ስምና ሥልጣን ለማስወጣት በማሰብ፣ «በኢየሱስ ስም ልቀቃት» እያለ መጸለይ ጀመረ። ልጅቷ ሲያዩዋት በሥጋ በጣም ቆንጆ ልጅ ነበረችና ሰይጣን ይህንን ተጠቅሞ የዚህን ወጣት አእምሮ ለመለወጥ አሰበ። ክርስቲያኑም ልጅ እየገሠጸ መጸለዩን ቀጠለ፤ «በኢየሱስ ስም ውጣ፣ በኢየሱስ ስም ውጣ።» እያለ መጸለዩን ቀጠለ። በዚህ ጊዜ በልጅቷ ውስጥ ያለው አጋንንት እምቢ አልወጣም» አለ። «ለምን?» ቢለው፣ «እኔን ውጣ ውጣ የምትለኝ፣ እኔ ከወጣሁ በኋላ አንተ

እርሷን ልታገባት ነው አይደል?» አለው፡፡ በዚህ ጊዜ የሚጸልየው ወጣት ልጅ፣ «ሰይጣን እግዚአብሔር ይገሥጽህ፣ ሰው ያለሰበውን ታሳስባለህ» ብሎት አረፈው፡፡

አዎ፣ ሰይጣን ክፉ ነው፡፡ ሰው ያላሰበውን አሳቢ መስሎ ግብዣ በማቅረብ ይፈትነናል እና ፈታኙን እምቢ እንበል፡፡ ጌታችን ሰይጣን ያቀረበለትን ሦስት ፈተና ሦስት ለዜሮ በመሸነፍ አሸንፎታልና እኛም የእርሱን ምሳሌ እንከተል እንጂ ሦስት እኩል መውጣት የለብንም፡፡ እግዚአብሔር ስለ እኛ ያስባልና ፈታኙ የሚያስብልንን እምቢ እንበል፡፡

ግጥምጥም:- ባፉ ማር ጠብ ይላል ውስጡ ግን እሬት ነው፣

ፈታኙን እምቢ በል መጨረሻው ሞት ነው፡፡

ምሳሌ 16:8
ማቴ. 4:1-11

# ኑር ያልኩት ይኖራል!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።» (ዮሐ. 1:12)

ሰባኪው ለእግዚአብሔር ልጆች ስለ ተሰጠው የልጅነት ሥልጣን ሲያስተምሩ እንዲህ አሉ:- «በዚህ የተሰበሰብን ሁላችን እግዚአብሔርን የተቀበልንና በስሙም ያመንን ከሆነ፣ የልጅነት ሥልጣን ተሰጥቶናል። ይህም ሥልጣን በሁለት ይከፈላል። አንደኛው፣ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል። ቀድሞ የሰይጣን/የቁጣ/ ልጆች ነበርን፣ አሁን ግን የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል፤ የመንግሥቱም ወራሾች ነን። ሁለተኛው፣ በክፉው የመናፍስት ሥራ ላይ ሥልጣን ተሰጥቶናል። በዚህ ዓለም ስንኖር ይኸኛውን ሥልጣን ልንጠቀምበት መቻል አለብን። መንግሥተ ሰማይ ይህ ሥልጣን አይሠራምና። ሰይጣን ምንም ያህል ማስፈራራቱ ብዙና ትልቅ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ግን ከእግራችን ሥር እንድንቀጠቅጠው የልጅነት ሥልጣንን ሰጥቶናልና በእምነት ተነሥተን እንጠቀምበት።» ይህንንም መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ግልጽ ለማድረግ ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

በአንድ ከተማ ውስጥ የሚኖር አንድ አስፈሪ ጠንቋይ ነበረ። እርሱም፣ «እኔ የበላይ ነኝ፣ ኑር ያልኩት ይኖራል። ሙት ያልኩት ይሞታልና። ለእኔ ተገዙ» እያለ ሕዝቡን በማስፈራራት ይገዛል። ታዲያ ወደዚያ ከተማ የልጅነት ሥልጣኑን ብቻ ይዞ አንድ ወንጌላዊ ገባና ወንጌልን መናገር ሲጀምር፣ ብዙ ሰዎች ከአጋንንት እሥራት እየተፈቱ ወደ ጌታ መምጣት ጀመሩ። ይህም ወሬ ለጠንቋዩ ደረሰው። «አንድ ልዩ ኃይል ያለው ሰው ወደዚህች ከተማ ገብቷል። የኢየሱስንም ስም ሲጠራ ሰይጣን ያለበት ሰው ይወድቃል፣ አጋንንቱም ይጮህና ይወጣል።» አሉት። ይህም ጠንቋይ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወንጌላዊው በሄደበት ላለመሄድ ወሰነና ሲሸሽ ቆየ። ነገር ግን አንድ ቀን ቤተሰቡን ጠራና፣ «በተከበርኩበት አገር እስከ መቼ እየሸሸሁ እኖራለሁ። ሂዱና ወንጌላዊውን ጥሩትና ይለይልን። ግን መጀመሪያ ምናልባት ሰይጣን ይዞኝ ከወደቅሁ እንዳልጎዳ ጅባ አንጥፉልኝ» ብሎ አዘዘና ወንጌላዊው ተጠራ። ወንጌላዊውም ገና ከቤቱ በራፍ ሲደርስ ጠንቋዩ ጮኸና በታላቅ ድምፅ እንደፈራው ጅባው ላይ ተዘረጋ። በዚህ ጊዜም ወንጌላዊው በተሰጠው የልጅነት ሥልጣን ተጠቅሞ በኢየሱስ ስም በመጸለይ ከሰይጣን እስራት የከተማዋን ጠንቋይ ነፃ አወጣው።

አዎ፣ በእኛ ላይ ያለው በእነርሱ ላይ ካለው ይበልጣልና፣ የተሰጠንን የልጅነት ሥልጣን በክፉው ሥራ ላይ እንጠቀምበት። ወደ እውነተኛውም ብርሃን እንዳይመጡ የሰዎችን አእምሮ ያሳወረውን ሰይጣንን በኢየሱስ ስም አስወግደን፣ ሰዎችን ለክርስቶስ እንድንማርክ ጌታ ይርዳን። አሜን።

ጥቅስ:- «አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ፣» የሐዋ. 16:16-18

ግጥምጥም:- በሥልጣን ላይ ሥልጣን ተሰጥቶኛልና፣
በአምላኬም ስም ልዘመት ዛሬም እንደገና።

# «በሕግ አምላክ!»

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ...» (ያዕቆብ 4:7)::

ሰባኪው፣ «በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች አንዳንድ እንደ ቃሉ ያልሆኑትን ነገሮቻችንን ማስተካከል ስላለብን በእነርሱ ላይ ትምህርት እሰጣለሁ:: ይኸውም ለምሳሌ፣ እግዚአብሔርን ለማምለክ በምንሰበሰብበት ጊዜ ሰይጣንም አብሮን ተቀምጦ ወይም አዚምን ረጭቶ ምንም ሳይሆን ይወጣል:: የእግዚአብሔር ቃል የሚለው፣ <እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል> ነው:: ይህ የቃሉ እውነት በእኛ የማይፈጸመው ታዲያ ለምንድን ነው? ለእግዚአብሔር በሙሉ ኀይላችን ከመገዛት ይልቅ ዐመፀኞች ስለሆንን ነው:: ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ፈንታ በኃጢአታችን ምክንያት ከእግዚአብሔር ስለ ራቅን ነው:: ከእግዚአብሔር ደግሞ ከራቅን ሰይጣን ወደ እኛ ይቀርባልና ከእግዚአብሔር አንራቅ:: ለእግዚአብሔር ካልተገዛን ሰይጣን ለእኛ አይገዛምና ለእግዚአብሔር እንገዛ» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

«በአጋንንት ኀይል ቤተሰቡንና አካባቢውን ስላወከ በሰንሰለት ቤቱ ከታሰረ ሰንበት ብሏል:: እዚያው ሰፈር የሚኖር አንድ አማኝ አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያኑ የተካሄደውን ኮንፈረንስ ተካፍሎ በተነቃቃ መንፈስ መጣና በሰይጣን ወደ ተያዘው ሰው ቤት ሄዶ፣ "ዛሬ እጸልይለታለሁና ወደ ታሠረበት ክፍል አስገቡኝ" አለ:: ቤተሰቦቹም፣ "ተው እባክህ ብዙ ሰዎች መጥተው ጸልየው አልወጣምና ላንተም ሊወጣ አይችልም፣ ይቅርብህ" ቢሉት እንቢ አለ:: ወደ ክፍሉም ገባ:: "ሰንሰለቱን ፍቱትና ሁሉም ሰው ይውጣ" አለ:: ሁሉም ሰው ወጣ:: አጋንንቱም የሰፈረበት ወጣት ፈርጠም ያለ ነበርና ማጅራቱን ያዘና እግሩ ሥር አስገብቶ ሁለት ጊዜ በክርኑ ሲነርተው "ኡ ኡ" ብሎ አንባረቀ:: ሰዎቹ ገቡ፣ ሦስተኛ ሊደግመው ሲል <በሕግ አምላክ!> ብሎ ጮኸ::»

የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆይ፣ ሰዎችን ከሰይጣን እስራት ነፃ የምናወጣው ለእግዚአብሔር በመገዛትና ወደ እርሱ በመቅረብ እንጂ፣ ይህንን ሳናደርግ በኮንፈረንስ ተነቃቅተን በመምጣት ብቻ አይደለም:: ዛሬ አማኞች ሁላችን እግዚአብሔርን በመፍራትና የቅድስና ኑሮ በመኖር ብንመላለስ ከፊታችን ምንም ኃይል አይቆምም:: የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኀይል ታደርጋለችና::» ለእግዚአብሔር የማይታዘዙትን ለመግዛት፣ ከእግዚአብሔር የራቁትን ለማቅረብ ዛሬ ዲያብሎስ እያገሳ በዙሪያችን ይዞራል:: ሰይጣን መንፈስ ነው:: መንፈስን መምታት (መቃወም) የሚቻለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነውና ሥጋዊነታችንን ትተን በጌታ መንፈስ የተሞላን እንድንሆን ጌታ ይርዳን:: አሜን!

ግጥምጥም:- ሰይጣን ሕግ የለውም በሕግ አምላክ አትበል፣
ወደ አምላክ ቀርበህ መንፈሱን ተቀበል::

1ኛ ጴጥ. 5:8፣ 9
ዮሐ. 9:31

# የመቃብር አፈር

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም።» (ሮሜ 10:11)

ሰባኪው: «በሰማይም ሆነ በምድር ለማዳንም ሆነ ለመግደል ሙሉ ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሥጋንም ነፍስንም ሊያድን ወይም ሊያጠፋ የሚችል ባለሥልጣን ጌታ ብቻ ነው። ይህንን ካለመረዳት ዛሬ ሰዎች ለነፍሳቸውም ሆነ ለሥጋቸው ፈውስንና ደስታን ፍለጋ ከእግዚአብሔር ውጪ ሲንዙ ይታያሉ። አንዳንዱ ለጠንቋይ፣ አንዳንዱ ለአድባር፣ ሌላውም ለዛፍ ሲያጥንና ሲሰግድ ይታያል። ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድና እጅ የሌለበት መንገድ ነውና ተመለሱ። ከድህነት የሚያወጣ ጌታ እንጂ ሰባኪ አይደለም። ከጭንቀት የሚያሳርፍ ጌታ እንጂ መናፍስት ጠሪ አይደለም። ከኃጢአት የሚያድን ጌታ እንጂ የእኛ ሥራ አይደለም። ከሞት የሚያድን ጌታ ኢየሱስ እንጂ ጠንቋይ አይደለም።» ለሚለው መሠረታዊ የክርስትና ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ:-

ክፍለ ሀገር ለአገልግሎት ሄጄ የተቀበለኝ ወንጌላዊ ቤት ሄጄ ሁለት እኅቶችን አስተዋወቁኝ። «ይህችኛዋ ባለቤቴ ነች። ይህችኛዋ ደግሞ ጌታ የሰጠኝ እኅቴ ናት» አለኝ። «ጌታ የሰጠኝ እኅቴ ስትል ምን ማለትህ ነው ስለው፣ ታሪኩን አጫውትሃለሁ ብሎ ጥቂት ካረፍኩ በኋላ ያጫወተኝን ልንገራችሁ። ወደ ጌታ ከመምጣታቸው በፊት ከእኅቱ ጋር አብረው እየኖሩ ሳለ እርሷ በጠና ትታመማለች። እርሷን ለማዳን ያልሄደበት የለም፣ መፍትሔ ግን ጠፋ። አልጋዋ ላይ ተኝታ እስከማትታይ ደረሰች። በመጨረሻም ላይ የሄደበት ጠንቋይ ወደ ጌታ እንዲመጣ ምክንያት የሚሆነውን ነገር ሳያውቅ አዘዘው። «እኅትህ የምትድነው ለሦስት ቀን ገጣባ አህያ ላይ እያስቀመጥክ፣ ለሰባት ቀን የመቃብር አፈር ጠዋት ጠዋት እያጠጣህ፣ የጅብ ቆዳ አንገቷ ላይ ስታስርላት ነው።» አለው። እኅቱን ለማዳን የታዘዘውን አደረገ። እርሷ ግን ለውጥ አላመጣችም። አንድ ቀን ተስፋ ቆርጦ እንቅልፍ አጥቶ ፍጥጥ ብሎ አደረ። በሰፈራቸው መሃል ካለው ጸሎት ቤት ፕሮግራም መሪው የሚናገረው አንዳንድ ቃላት በድምፅ ማጉያው እያመለጠ ጆሮው ይገባል። ከዚህም ውስጥ እንዲህ የሚለውን ሰማ:- «ማዳን የእግዚአብሔር ነው!» ብድግ አለ። አዎ፣ ማዳን የጠንቋይ ሳይሆን

የእግዚአብሔር ነውና እነዚህ ጴንጤዎች ጋር ሄጄ ልሞክር ብሎ እኅቱን ተሸክሞ አመጣት ። በእርግጥም ማዳን የእርሱ የሆነ ባለሥልጣን ጌታ እኅቱን ፈወሳት። ዛሬ እርሱ የቤተ ክርስቲያኒቱ ወንጌላዊ፣ እርሷ ደግሞ በመዘምራን ቡድን ውስጥ ገብታ አምላኳን ታገለግላለች። ያለ አባትና እናት ያሳደጋቸውን ጌታ ሥራ ሲናገር እንባ በጉንጮቹ ይወርድ ነበር።

አዎ፣ ወገኖች፣ በእርግጥም ማዳን የእግዚአብሔር ነው። ነፍሳችንንም ሥጋችንንም ከጊዜው ጥፋትና ከገሃነም እሳት ሊያድን የሚችል እግዚአብሔር ነውና በእርሱ ላይ ብቻ እንታመን። እግዚአብሔር አንድምታ የሌለው ብቸኛ አዳኝ ነው። በዚህ ምድር መቶ እጥፍ ማኖር በላይ የዘላለም ሕይወትን መስጠት የሚችል በቀራኒዮ መስቀል ደሙን ያፈሰሰው ክርስቶስ ብቻ ነውና ከዛሬ ጀምሮ ሙሉ ሕይወታችንን ለእርሱ ሰጥተን ከዘላለም ሞት እንድናመልጥ ጌታ ይርዳን።

ግጥምጥም:- ሊገድልና ሊያድን ሙሉ ሥልጣን ያለው፣

ሊረዳህ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ሮሜ 10:9
የሐዋ.ሥራ 4:12

# ድንግል ማርያም

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፣ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ:: ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፣ ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፣ ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና::» (ማቴ. 11:28-30)

ሰባኪው፣ «በዚህ ዓለም የምንኖር ብዙ የሚከብዱ ሸክሞች ያሉብን ሰዎች ነን:: ከሁሉም ከሁሉም በጣም የሚከብደው ሸክም ደግሞ የኃጢአት ሸክም ነው:: እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፣ ይህንን የኃጢአት ሸክም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንድናራግፈው አደረገልን:: ቃሉ እንደሚል ከኃጢአት ሸክም ወጥተን ከገሃነም እሳት የምንድነው ከድንግል ማርያም የተወለደውን ልጁን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስናምን ብቻ ነው:: ከእርሱ ሌላ አዳኝ በሰማይም ሆነ በምድር የለምና፣ በእርሱ እመኑ፤ ከዘላለም ሞትም ትድናላችሁ፤ የከበደው ሸክማችሁም ይቃለላል:: ለነፍሳችሁም እረፍት፣ ለሥጋችሁም ፈውስ ታገኛላችሁ::» ለሚለው የአምላካዊ ቃል ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ:-

አንድ ሰው በቤቱ ሊደግሰው ስላለው ትልቅ ድግስ የሚያስፈልገውን የገብስ እህል ሸምቶ ለድግሱ እየተዘጋጀ እያለ የሸመተው የገብስ እህል መጠኑን በሙሉ መሸፈን እንደማይችል ተረድቶ እየተጨነቀ ሳለ፣ ይህንን ጭንቀቱን በቅርቡ ሊያቃልል የሚችል ሁኔታ ተፈጠረለት:: ይኸውም በሰፈሩ ውስጥ የሚሸጥ ገብስ ተሸክሞ፣ «ገብስ፣ ገብስ፣ ገብስ» እያለ የሚጮኽ ሰውን ሰማ:: ወጥቶም ወደ ቤቱ ጠራውና የተሸከመውን ገብሱን በሙሉ መግዛት እንደሚፈልግ ገለጸለት:: ገብስ ሻጬም፣ «እግዚአብሔር ረዳኝ፣ ከመሸከምና ከመዞርም አሳረፈኝ» ብሎ እሺ እንደማለት በተቃራኒው እንዲህ ሲል መለሰለት»፣ «ጌታዬ፣ ሁሉንም ገብስማ አልሸጥልዎትም:: ምክንያቱም ሁሉንም ገብስ ለእርስዎ ሸጬ እኔ ምን ተሸክሜ ልዞር ነው::»

አዎ፣ በእኛም በሰው ልጆች ሕይወት ይህ ዓይነት ሁኔታ ይታያል:: እግዚአብሔር፣ «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑና እረፉ» ሲል፣ የየራሳችንን ምክንያት በመስጠት እንቢ ሸክሜን እራሴ እሸከማለሁ እንላለን:: ምናልባት ብሎልን ወደ ጌታ ከመጣንም ሁሉንም ሳይሆን ግማሹን ሸክም ለእኛ እናስቀራለን:: ዛሬ ጌታ እንዲህ ይላል፣ «ሙሉ ለሙሉ በእኔ ብቻ በማመን ሁሉንም ሸክማችሁን በእኔ ላይ ጣሉና እረፉ::» ቃሉን ሰምተን እንድንታዘዝ አምላክ ይርዳን:: አሜን::

| |
|---|
| ዮሐ. 10:9 |
| የሐዋ. 3:6-9 |

ግጥምጥም:- ሸክሜን ለሚሸከም ለጌታ ሰጥቼ፣
ቀና ብዬ ሄድኩኝ ከእሥር ተፈትቼ::

## *ክፍል 6*
## *እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሕይወትና አገልግሎት*

# ምላጭ አበጠ በምን ይበጣ!

***የቃል ጥናት ጥቅስ: - «በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።» (ሮሜ 12:13)***

ሰባኪው፣ «ለእግዚአብሔርም ሆነ ለእኛ ትልቁ ቁም ነገር በእርሱ ፊት ከልባችን ተለውጠን እርሱን መከተላችንና ማምለካችን እንጂ ብዙ ዓመት ያለ ለውጥ በቤቱ መቆየታችን አይደለም። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብጥብጥ፣ መከፋፈል፣ መገፋፋትና መቆሳሰል ያለው ለምንድን ነው? ብንል ያልተለወጥን ሰዎች ስለሆንን ነው። 'ልጄ ሆይ፣ ልብህን ስጠኝ' ላለው ጌታ ልባችንን ስላልሰጠን ነው። ምን አልባት ልንሰብክ፣ ልንዘምር፣ የተለያዩ አገልግሎቶች በቤቱ ልንሰጥ እንችላለን። ነገር ግን እግዚአብሔር ልባችንን ሲመለከተው ከልቡ ጋር ካልሆነ 'እንደ ልቡ ነው' ነው የሚለን እንጂ 'እንደ ልቤ ነው' አይልምና እንመለስ። አንዳንድ ጊዜ ነገራችን የተገላቢጦሽ ይሆናል። ይኸውም ልባችንን ሰጥተንና ተለውጠን መከተልና ማገልገል ሲገባን ልባችንን ራሳችን ይዘን የልባችንን ለምን ጌታ አላደረገልንም ብለን እናኩርፋለን፤ 'ምላጭ አበጠ በምን ይበጣ' እንደተባለው እንሆናለን። ስለዚህ ትልቁ ነገር ከልብ ተለውጠን ጌታን መከተላችን ዓለምን መናቃችን ነው እንጂ ብዙ ዘመን በእግዚአብሔር ቤት ያለ ለውጥ መቆየታችን አይደለምና ዛሬውኑ እንለወጥ።» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ እንደዚህ ሲሉ ተናገሩ።

በአንድ የጨዋታ ሜዳ ላይ የሰርከስ ጨዋታ ይካሄድ ነበር። ሲያዩት የሚያስፈራራ ዓይነት ጭምብል /ማስክ/ ሰውነታቸውን ሙሉ ለብሰው ትልቅ ክንፍ ዓይነት በጉናቸው አድርገው በመድረኩ ላይ ከወዲያ ወዲህ እየሮጡ በአስገራሚ ሁኔታ እየተገለባበጡ ያሳያሉ። ትርኢቱ ሳያልቅ ድንገት በረዶ የቀላቀለ ኃይለኛ ዝናብ ይመጣና ጨዋታውን ያቋርጠዋል። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ለመጠለል በየፊናው ይበተናል። ሰርከስ ለማሳየት አስፈሪ ልብስ ከለበሰው ሰው አንዱ ለመጠለል ወደ መንደር ሲሮጥ ቀኑ ሰንበት ነበርና ሰዎች እያመለኩ ያሉበት ቤተ ክርስቲያን እየሮጠ ዘው ብሎ ይገባል። እዚያም ያሉት ሰዎች ምን መጣብን በማለት በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ በመውጣት ይሸሻሉ። በዚህ ጊዜ ለማምለጥ አቅም አጥተው ወደ ቆሙት አንዲት አሮጊት ሴት ይህ

የሰርከስ ሰው ጠጋ ብሎ ለምን ሰው እንደሚሸሽ ሊጠይቃቸው ቃል ከማውጣቱ በፊት አሮጊቷ ቀደም አሉና፣ «ሰይጣን ሆይ፣ አርባ ዓመት ሙሉ በቤተ ክርስቲያን ልሁን እንጂ አንተን ነበር ስከተል የኖርኩት» ብለውት አረፉ::

አዎ፣ ወገኖች፣ በልባችን ተለውጠን ጌታን እናገልግል፤ እናምልክ እንጂ ዘመን እየቆጠርን ከርሞ ጥጃ መሆን አይገባንምና ራሳችንን እናስተካክል:: ከእግዚአብሔር ቤት የሚጀምረው ፍርድ እንዳያገኘን ጌታ አብዝቶ ይርዳን:: አሜን::

| ያዕ. 1:8፣ 26 |
|---|

*ግጥምጥም:- የልቤን ደብቄ አፋዊ ከምሆን፣*
*ልቤን አስረክቤ እንደ ልቡ ልሁን::*

# ገንፎ በቂቤ

*የቃል ጥናት ጥቅስ: - «አባቶች ሆይ፣ ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻችሁን አታበሳጩአቸው::» ቆላ. 3:21*

አንዲት ሚስት ከልጆቿ ለይታ ለባለቤቷ ጥሩ ምግብ /ገንፎ በቅቤ/ አዘጋጀች:: ይህንን ምግብ በጓዳ ጨለማ ስፍራ ውስጥ ባልዬው ሲበላ አንዱ ትንሹ ልጅ ከልጆቹ ሁሉ ጋር ለከብት ጥበቃ ሜዳ ሳይሄድ ቤት ቀርቶ ነበርና በቂቤ የተዘጋጀው የገንፎ ሽታ አወደው:: ወደ ጓዳው አባቱ እንዳለ ያውቅ ነበርና አባቱን ጠርቶ መጠየቅ ጀመረ:: «አባዬ» አለው፣ «አቤት» አለ አባት:: «ምን እየበላህ ነው?» አለው እርሱ ጠዋት ከወንድሞቹ ጋር እንደ ነገሩ ስለ ተሸኘ በመቆጨት:: አባትም፣ «አፈር እየበላሁ ነው» አለው:: ልጅም አፈር እንዳልሆነ በሽታው ስላወቀና የእናቱም እንዲህ ዓይነት መሠሪነት ስላናደደው ድምፁን ከፍ አድርጐ፣ «አባዬ፣ አፈር ከሆነ የምትበላው እኔም መጥቼ ልብላ» አለው:: አባትየውም የልጁ ተከታታይ ጥያቄ ገንፎውን እንዳይበላ እያወከው ስለሆነ ተናዶ ለልጁ እንዲህ አለው:: «ልጄ፣ አፈር ለመብላት ትፈልጋለህ?» አለው:: «አዎን» አለ ልጁ:: «ጥሩ አፈር ለመብላት ከፈለግክ እዚያው ያለህበት ጀምር:: አፈር ሁሉም ቦታ አለና ከግድግዳው ጀምር» አለውና አረፈው::

አዎ፣ እውነተኛ ፍቅር ከራሱ ይልቅ ሌላውን ያስበልጣል፣ የሌላውን ጥቅም ያስቀድማል:: ዛሬ በየቤታችን ለልጆቻችን ያለን ፍቅር ምን ያህል ይሆን? ይህ ከላይ ያለው አባት ልጁን አፈር ብላ ነው የሚለው:: እኛስ? እናቱም የጉላ አድልዎ እያሳየች ነው:: እርስዎስ? የይስሐቅ ቤት የተበተነው በአድልዎ ነው:: የእርስዎስ ቤት ምን ዓይነት ይሆን? ምን ዓይነት ዜጎች እያፈራን ይሆን? እግዚአብሔር የሰጠንን ሲሳይ ያለ ከንቱ ወዳሴ በፍቅርና በእውነት አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ተባብለን ተካፍለን እንድንኖር የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- *ሁሉም ይደርሳል ፅዋው ሲሞላ፣*

ከአፈር በላይ ሆኖ ለምን አፈር ይብላ::

ዘፍጥ. 27:1-46
ፊልጵ. 2:3-4

# ጴንጤው በክሰኛ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ስለ ራሴ ግን ከድካሜ በቀር የምመካበት ነገር የለኝም» (2ኛ ቆሮ. 12:5)።

መጋቢው መልእክታቸውን ለመስማት ለተሰበሰበው ሕዝብ እንዲህ እያሉ ማስተማር ጀመሩ። «በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች ሁሉ የምንመካበት ብዙ ነገሮች አሉን። ለመሆኑ የእነዚህ ነገሮች ሁሉ ምንጭ ማን እንደሆነ አውቃችኋል? እግዚአብሔር ነው። ስለሆነም ትምክህታችን እርሱ ብቻ ሊሆን ይገባል። ዛሬ እውነቱን ልንገራችሁ፣ ሊመኩበት በሚያስመካው በዘላለሙ ጌታ ላይ ብቻ ትምክህታችንን ካላደረግን ከስረናል። ምናልባት በባንክ ባላችሁ ገንዘብ ብትመኩ ነገ ስለሚረግፍ ወይም ስለሚጠፋ ትምክህታችሁ ከንቱ ነው። ምናልባት በጊዜው ብትመኩ፣ ጊዜው ያልፋልና ከንቱ ነው። ወይም በጉልበታችሁ ብትመኩ፣ ጉልበት የእግዚአብሔር ነውና ከንቱዎች ናችሁ። እንግዲህ ትምክህታችን ምንድን ነው? ትምክህታችን ዛሬ ሲያምኑት ነገ በማይከዳና በማይለወጠው፣ ነገር ግን በሚለውጠው በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ሊሆን ይገባል።» ለዚህም ዘላለማዊ እውነትነት ላለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ። ለዚህም

ሰፈሩ ሁሉ የሚፈራው አንድ ሰውነቱ የፈረጠመ በክሰኛ ነበረ። ማንም እርሱን ቀና ብሎ አያይም (ዝንቡን የሚያባርር የለም)። አለበለዚያ ቀና ብዬ አያለሁ እናገራለሁ ቢል ጡንቻው ከምድር ጋር ነው የሚደባልቀው። በእንዲህ ሁኔታ ሲኖር ሳለ ከፍ ካለው በላይ ከፍ ያለው እግዚአብሔር በመለኮታዊው ኃይሉ የዚህን በክሰኛ ልብ ሰበረና ጌታን ተቀበለ። አማኝ መሆኑን የሰፈሩ ሰዎች ሁሉ ሰሙ። እሰይ እኛም አረፍን አሁን አይመታንም ብለው ተደሰቱ፤ የድሮ ፍርሃታቸውንም አስወግደው በፊቱ በንቀት መመላለስ ጀመሩ። ትንሽ ትልቁ፣ «ጴንጤው በክሰኛ» እያለ ማሾፍ ቀጠለ። አንድ ቀን ጴንጤው በክሰኛ ተበሳጨ፣ የድሮው ነገር ትዝ አለው። አንድ ልጅ እንደተለመደው፣ «ጴንጤው በክሰኛ» ብሎት ሲያልፍ ያዘና በቦክስ ሁለት ጊዜ ሲነርተው አማኞች በአካባቢው ደረሱና ገላገሉት። «ተው፣ ለምን ትማታለህ? አማኝ አይማታም» ቢሉት፣ «አይ፣ ጌታ ወንድ ልጅ እንዳለው ላሳያቸው ብዬ ነው» ብሎ መለሰላቸው።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆይ፣ የጌታ ልጅ መሆናችንን በሥጋችን ኃይል ማሳየት አንችልም፤ አልተፈቀደልንም። በፍቅር እና በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በከንቱ እየተነሣን እንድንመካ የሚያደርገንን የአሮጌውን ሰው ባሕርይ እናስወግድ፤ ጌታንም ክርስቶስን ለብሰን በብዙ ትሕትናና አክብሮት እንድንከተለው ራሱ ጌታ ይርዳን። አሜን።

ግጥምጥም:- «በኃይልህ አትመካ ድንገት ይከዳሃል፣

በእግዚአብሔር ተመካ እርሱ ያዋጣሃል።

| |
|---|
| 2ኛ ቆሮ. 10:17<br>ገላ. 6:14 |

# ሰላቢ የሰለበው ሀብት

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ቅንዓት እንደ ሲኦል የጨከነች ናት፤ ፍንጣሪዋም እንደ እሳት ፍንጣሪ ነው።» (ምሳ. 8:6)

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር ከሕይወታችን እንድናስወግደውና እንድንተወው የሚፈልገው ነገር በዚህ ዘመን ወገኖቼ ቅንዓትንና ምቀኝነትን ነው። ክርስቲያን በክርስቲያን ላይ መቅናት አይገባውም። የሌላው ማደግ የራሱም ማደግ እንደሆነ አድርጎ ሊቆጥር ይገባዋል። ጎረቤት በጎረቤት ላይ መቅናት የእርሱን ሀብት በሰላቢና በጥንቆላ ለማግኘት መፈለግ ኃጢአት ነው። ደግሞ ሰላቢ የሰለበው ሀብት ያጠፋል ወይም ይጠፋልና በጽድቅ የሚገኘውን ሀብት ተመኙ ። የእግዚአብሔር ቃል በሮሜ 13:13 ላይ መመላለሳችን በቅንዓት አይሁን ይላልና። ቅንዓትና ምቀኝነት የሥጋ ሥራ ናቸው። የሥጋ ሥራን የሚያደርጉ ደግሞ መንፈሳውያን አይደሉምና እንመለስ። ሰው በባልንጀራው ሕይወት መሳካት የሚቀናው ፍጹም ፍቅር ስለሌለው ነው። ፍቅር አይቀናምና (1ኛ ቆሮ. 13:4)። ቅንዓት ደግሞ እንደ ሲኦል የጨከነ ነውና ለመግደል እንኳ አይመለስምና ተጠንቀቁ።» ለሚለው ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«አንድ ቤተሰብ የመጀመሪያ ልጃቸው ሦስት ዓመት ከሆናት በኋላ እንደ ጌታ ፈቃድ ሌላ ልጅ ለመጨመር ወሰኑና ሚስት አረገዘች። የመውለጃዋም ጊዜ ከመድረሱ በፊት አዲስ ልጅ ስትመጣ የመጀመሪያዋ እንዳትቀና በተቻለ መጠን አእምሮዋን ለማዘጋጀት ሞከሩ። ልጅቱም ከእርሷ ያነሰ የሚያጫውታት ሕፃን ልጅ እስኪመጣ ቸኮለች። እናቲቱም በእግዚአብሔር በተመደበው ጊዜ ወለደችና ወደ ቤት መጣች። በዚህ ጊዜ ይህች ትልቋ ልጅ ለተወለደችው ሕፃን ልጅ ሁሉን እንደምትሰጥ ተናገረች። የእኔን ጡት ትጥባ፣ የእኔን ጡጦ ትጠጣ፣ በአልጋዬም ትተኛ አለች። ነገሩም ሆነ። ከሦስት ቀን በኋላ ግን ቅንዓት የሚባለው የውስጥ ቅንቅን ያዛት ልጅቷን ስታያት አልጋዋን ከመልቀቅ ይልቅ እየቀጠለች ሄደች። በዚህ ጊዜ ትልቋ የ3 ዓመቷ ልጅ ወደ አባቷ ጠጋ ብላ፣ «አባዬ፣ ይህችን ልጅ ከአልጋዬ ላይ ታነሣ ከሆነ አንሣ አለበለዚያ ጨፍልቄ ነው የምገልልህ።» ብላ ተናገረች።

አዎ፣ ወገኖቼ፣ ቅንዓት እስከ ሞት ያደርሳል። ሰው አይመርጥም እንደ ሲኦል የጨከነ ነውና እንመለስ። ዛሬ ወንድማችንን ወይም እኅታችንን ገፍተን ወይም አስወግደን የእነርሱን ቦታ በዐመፅ ለመያዝ አስበን ይሆን። እነሆ፣ የእግዚአብሔር ቃል፣ «አይሳካልህምና ተመለስ። በቀል የእኔ ነውና አይከናወንልህም» ይለናል። አዎ፣ ለዚህ የእግዚአብሔር መልእክት ታዛን በእግዚአብሔር ፈቃድ እንድንኖር ጌታ ይርዳን። አሜን።

ዘኁል. 12:1-5
ምሳ. 6:34

ግጥምጥም:- በቅንዓት ወስደህ የወንድምህን ሀብት፣
እኔ እፈራለሁኝ ሳትበላው እንዳትሞት።

# እግዚአብሔር አይዘበትበትም

ሰባኪው፣ «ሰው የዘራውን ያንኑ ያጭዳል። በዚህ ምድር ላይ ስንኖር የእግዚአብሔርን ቃልና የእግዚአብሔርን መልእክት ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለሰዎች ፈውስና ጥቅም ማዋል አለብን እንጂ ለራሳችን ክብርና ጥቅም ማዋል የለብንም። ቃሉ ያላለውን በግድ ማስባል፣ እግዚአብሔር ያልገለጠውን በውሸት ተገለጠልኝ ማለት የሚያስነውር ብቻ ሳይሆን ወደ ገሃነምም ያስገባልና እንጠንቀቅ። በተለይም እኛ ሕዝቡን እንድንመራና እንድናስተምር እግዚአብሔር ያስቀመጠን ሰዎች እንደ ፈቃዱ እንጂ እንደ ፈቃዳችን እናድርግ፣ ለክብሩ እንጂ ለክብራችን አንድከም። ዛሬ በቤተሰብ፣ በቤተ ክርስቲያንና በአገራችን መካከል መከፋፈል ለምን መጣ ብንል እንደ እግዚአብሔር ቃል ስለማንኖር ነው፣ ቃሉን ወደ ጎን ትተን የእኛን አጀንዳ ስለአስቀደምን ነው፤ በሌላው ሥቃይና ድካም ላይ ተረማምደን የራሳችንን እንጀራ ለማደለብ ስለሞከርን ነው። እንመለስ። እግዚአብሔር አይዘበትበትም የሚባላ እሳት ነውና።» በሚለው ጠንካራና አስፈሪ መልእክታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ።

ከሁለቱ ወንጌላውያን አንደኛው ወደ ክፍለ ሀገር ሄዶ እንዲያገለግል የሚወስነው የሽማግሌዎች ቦርድ ስብሰባ በቀጣዩ ቅዳሜ ከመካሄዱ በፊት <ምናልባት እኔን ሂድ ይሉኝ ይሆናል> ብሎ የሰጋው ወንጌላዊ ከስብሰባው በፊት የሽማግሌዎች ቦርድ ሰብሳቢ (ሊቀመንበር) ቤት ማታ ሄዶ ለእርስዎና ለቤተሰብዎ ለመጸለይ ጌታ ልኮኝ ነው የመጣሁት» አለ። ሰብሳቢውም 12 ልጆች ወልደው ነበርና እነዚህም ልጆች በጥሩ ሁኔታ ቦታ ቦታ እንዲይዙላቸው ከባለቤታቸው ጋር የሚጸልዩበት፣ ሌላም ልጅ ላለመውለድ ባለቤታቸው ማኅፀናቸውን ያስቋጠሩበት ሰሞን ነበርና፣ «ለቤተሰብዎ እጸልያለሁ» ሲላቸው ደስ አላቸው፣ ጸሎቱም ተጀመረ። ይህ ከበስተ ኋላ ድብቅ አጀንዳ ያለው ወንጌላዊ ታዲያ በጸሎቱ መሐል ተነሥቶ እግዚአብሔር ሳይለው እንዲህ አለ፤ «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚስትህን ማኅፀን እሰምልሜአለሁ ይላል»።

ወገኖቼ፣ በሕይወታችን ሊመጣ ያለው ይምጣ፣ ሊሄድም ያለው ይሂድ እንጂ እግዚአብሔር ያላለንን አንበል። እግዚአብሔር ያለውን ብለን ሳንጨርስ ያላለውን ማለት ዓመፅ ነው፤ ኃጢአት ነው ያስቀስፋልም። የምላስን ሽንገላ፣ መሠሪነትንና ግብዝነትን ከሕይወታችን አስወግደን እውነትን በፍቅር እየገለጽን የምንኖር ታማኝ ባሪያዎች ያድርገን። አሜን።

የቃል ጥናት ጥቅስ፡- «አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም...» (ገላ. 6:7)

ግጥምጥም፡- እውነትን በእውነት ለአንተ ተናግሬ፣

ይጨምራል እንጂ መች ይቀንስ ክብሬ።

# ጌታ ልቤን እንጂ እጄን አልሰበረውም

የቃል ጥናት ጥቅስ «... በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።» (ሮሜ 12:2)

ሰባኪው: «የክርስትና ሕይወት የሚያምረው የተለወጠ ልብ አብሮ ሲኖረው ነው። በአሁኑ ጊዜ በተግባር የማይገለጽ ሥጋዊነት የበዛበት ያልተለወጠ ክርስትና ይዘን ግን ክርስቲያን ነኝ እንላለን። እግዚአብሔር ይቅር ይበለን። ክርስትና ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ደግሞ በልቡ ትሑት፣ አቅምና ጉልበት እያለው ክብሩን ለሌሎች የተወ ጌታ ነው። የእርሱ ልጆች ከሆንን ከልባችን መለወጥ አለብን እንጂ አፋዊ ክርስትና አያዋጣም። በእግዚአብሔር ዘንድ ያልተለወጠ ሰው መሥዋዕቱ ተቀባይነት የለውም። ስለዚህ በባህሪያችንና በተግባራችን ከዓለም ተለይተን እና ፈጽሞ ክርስቶስን በመምሰል ተለውጠን ልንከተለው ይገባል።» ለሚለው ግሩም የሆነ ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

በከተማ አውቶቡስ ላይ ሁልጊዜ ስለ ክርስቶስ መናገር የሚወዱ አንድ ሰው አንድ ቀን የተለየ ነገር ገጠማቸው። ሲመሰክሩ አጠገባቸው ሆኖ ይሰማ የነበረ አንድ ወጣት ልጅ እንዲህ እያለ ያሾፍባቸው ጀመር። «ጴንጤው ሽማግሌ፣ ጴንጤው ሽማግሌ» ያልሰሙ መስለው ዝም አሉት። አሁንም ማሾፉን ቀጠለ። ቦታ ቀየሩ እየተከታተለ ለሰው ሁሉ እኚህ ጴንጤው ሽማግሌ ናቸው ይላል። ታገሡት፣ አሁንም ደግመው ቦታ ቀየሩ። እየተከተለ ያሾፍባቸዋል። በመጨረሻም ላይ በጣም ስለተናደዱና ትዕግሥታቸው ስለአለቀ፣ «ጌታ ልቤን እንጂ እጄን አልሰበረውም» ብለው ሁለት ጊዜ በጥፊ አጮሉት። ጠላትም ይህንን የሥጋ ሥራ ተጠቅሞ በአውቶብሱ ውስጥ ያለውን ሰው አስነሣባቸው: በልጁ ላይ ከሰነዘሩት ጥፊ ይልቅ በእርሳቸው ላይ የተሰነዘረው ድብደባ ስለበዛ ያለ መውረጃቸው ወርደው አመለጡ።

አዎ፣ ወገኖቼ፣ እኚህ ሰው ከተግባራቸው ሲታዩ ልባቸውም የተሰበረ አይደለም። ልቡ የተሰበረ /የተለወጠ/ ሰው ሲሰድቡት ይመርቃል እንጂ አይረግምም፣ ወይም አይማታም። የራሱንም ክብር ለማስከበር ኃይል አይጠቀምም። ከዚህ ነገር ለመውጣት ጌታ ጥበብ እንዲሰጠው ይጸልያል እንጂ። ስለዚህ የዚህን ዓለም ሰዎች ክፉ ጠባይ አንከተል። በግብዝነትም ሳንለወጥ አናገልግል። ብዙ ቂምና ቁርሾ ይዘን በቤተ ክርስቲያን ግን በመድረክ ላይ እንደ መልአክ እንታያለን። እግዚአብሔር አይዘበትበትም እርሱ የሚባላ እሳት ነውና ከእሳት ጋር መጫወቱን ትተን በፍርሃትና በተለወጠ ልብ እንድንመላለስ ሁሉን ችሎ የሚያስችለው አምላክ እራሱ በጸጋው ይደግፈን። አሜን!

ግጥምጥም:- ላገልግለው እንጂ በተለወጠ ልብ ለእርሱ ሆኜ ትሑት ሮሜ 12:18
የአንጀት ክርስትና ለምን ይሁን የአንገት። ሉቃስ 10:27

# የምድር ጨው ወይስ የእንግሊዝ ጨው?

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ከዘላለም ሞት ያዳነን እንድናመልከውና ለሌሎችም ብርሃንና ጨው እንድንሆን ነው እንጂ በመጥፎ የሕይወት ምስክርነት እየተመላለስን የወንጌል እንቅፋት እንድንሆን ፈጽሞ አይደለምና ዛሬ ሕይወታችንን ልንፈትሽ ይገባል:: እኛ ለጨለማው የምንገለጥ የዓለም ብርሃን እንጂ በጨለማው የምንዋጥ መሆን የለብንም:: በመልካም የሕይወት ምስክርነት ክርስቶስን የምናሳይ መራራውን የምናጣፍጥ የምድር ጨው እንጂ፣ ክርስትና እንደ እነርሱ ከሆነ በአፍንጫዬ ይውጣ የምንባል መራሮችና ለዚህ ዓለም የምንመች ሰዎች መሆን የለብንም:: ስለዚህም ዓለም ስታማ አብረን አንማ፣ ዓለም ስትቀና አብረን አንቅና፣ ዓለም ስትዘፍን አብረን አንዝፈን፣ ዓለም ስትሰርቅ አብረን አንስረቅ፣ ዓለም ስትጠጣ አብረን አንጠጣ፣ ዓለም ስትሰክር አብረን አንስከር፣ ዓለም ስታኮርፍ አብረን አናኩርፍ፣ ዓለም ስታምፅ አብረን አናምፅ:: የእግዚአብሔር ቃል፣ «ኖኅ በሥራው ዓለምን ኮነነ» (ዕብ. 11:7) እንደሚል የምድር ጨው ሆነን የዓለምን ክፉ ሥራ በጽድቅ በመለወጥ በሥራችን እንኰንን እንጂ በዓለም ሥራ አብረን እየተባበርን አብረን መኰነን የለብንም» ለሚለው ግሩምና አስደናቂ መልእክታቸው እንደሚከተለው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

አንድ ወንጌላዊ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ሲሰብክ የምድር ጨውን ከእንግሊዝ ጨው ጋር እያወዳደረ እንዲህ ተናገረ፣ «እኛ ክርስቲያኖች የምድር ጨው ነን እንጂ የእንግሊዝ ጨው አይደለንም:: እንደምታውቁት የእንግሊዝ ጨው ጊዜው ደርሶ ከሆዳችን እስከሚወገድ ጉትጉትጉት እያለ ያምሰናል:: ልክ እንደዚሁ በቤተ ክርስቲያን ያልተደረገውን ተደረገ፣ ያልታየውን ታየ እያሉ ወሬ በክርስቲያኖች መካከል የሚያመላልሱ፣ ቅዱሳንን የሚያጋጩና የሚያምሱ የእንግሊዝ ጨዎች አሉ:: እከሌ ከእከሊት ጋር እጮኛ ሆነ፤ እከሌ እኮ፣ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ሰርቆ ቤቱን ሠራ! እከሊት በተሳሳተ የዲቪ ባልና ሚስት ከአገር ልትወጣ ነው፤ እከሊት ከጋብቻ በፊት የወለደችት ልጅ አላት፤ እከሌ እጮኛዋ አስረግዟት ሰሞኑን አስወረደች እያሉ በየመንደሩና በየቡና መጠጫው የሚያወሩ የምድር ጨው ሳይሆኑ የእንግሊዝ ጨው ናቸው:: የእንግሊዝ ጨው ሆድን አምሶ በሽታን የሚያስወግድ ሆኖ ሳለ፣ እነዚህ ግን በበሽታ ላይ በሽታ የሚጨምሩ

የወሬ ሱሰኞች ናቸው። እንደነዚህ ያሉት የምድር ጨው የዓለም ብርሃን ለመሆን የልብ ለውጥ ያስፈልጋቸዋልና ልንጸልይላቸው ይገባል።»

አዎ፣ ወገኖች፣ እኛስ ዛሬ በሕይወታችን የምድር ጨው ሆነን አልጫውን ዓለም፣ ቤታችንን፣ መንደራችንን፣ ቤተ ክርስቲያችንን፣ እያጣፈጥን ነው ወይስ እያመስንን? እግዚአብሔር ባስቀመጠን ቦታ ጨውና ብርሃን ሆነን በዓለም ኃጢአት ላይ ጨውን እንድንጨምር፣ በዓለም ጨለማ ላይ ብርሃንን እንድናበራ ጌታ ኢየሱስ ይርዳን። አሜን!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «የምድር ጨው ናችሁ. . . » (ማቴ. 5:13)።

ግጥምጥም:- ጨው አልጫ ሆኖ በምን ይጣፍጣል፣
ወደ ውጭ ተጥሎ በእግር ይረገጣል።

ዮሐ. 13:35
2ኛ ቆሮ. 6:14-15

# ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «አቤቱ፣... የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን» (መዝ. 19:14)::

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር የመነሻ አሳብን ይመዝናል:: <ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን> ተብሎ እንደ ተጻፈ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ውስጥን ይመለከታልና ግብዝነትን ከእኛ እናስወግድ:: ሰውን እንደምንሸነግል ወይም ሰውን እንደምናታልል እግዚአብሔርን ልናታልለው አንችልምና ግልጽነትን የተላበስንና የተደበቀ አጀንዳ ወይም ስውር ነገር የሌለን የእርሱ ልጆች ልንሆን ይገባናል:: እግዚአብሔር የውጭ ብቻ ሳይሆን የውስጥም አምላክ ነው፤ የአፍ ብቻ ሳይሆን የልብም አምላክ ነው:: ስለዚህ ፍቅራችን የልብ ይሁን እንጂ የአፍ ብቻ አይሁን:: ዛሬ ብዙ ሰዎች በቤታቸው እሾክና ጋሬጣ የሞላበት ሕይወት አላቸው:: በቤተ ክርስቲያን ግን ለስላሳ ናቸው:: ይህን አስመሳይነትህን ጌታ አንድ ቀን ሲገልጠው ትዋረዳለህና ተጠንቀቅ:: ይልቁንም የምትችለውን እችላለሁ፣ የማትችለውን አልችልም፤ የምታደርገውን አደርጋለሁ፣ የማታደርገውን አላደርግም ብለህ እውነትን በፍቅር ግለጽ እንጂ የማትችለውንና የማታደርገውን እፈጽማለሁ ብለህ <ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ> የሚሉትን የግብዞች ብሂል ፈጽሞ ከሕይወትህ አስወግድ::» ለሚለው ቀናና ግልጽ ለሆነ መልእክታቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

ከደሃ ቤተሰብ ስለመጣች ሁልጊዜ ኑሮአቸው ከእጅ ወደ አፍ ብቻ እንደሆነ ታውቃለች:: ስለዚህም እንደ ጓደኞቿ የፈለገቸውን የልብስ ዓይነትና ጌጣጌጥ ማድረግ አትችልም:: ለዚህም ነው ሁልጊዜ በሁለቱም ጆሮዎቿ ላይ ደህና ቀን ሲመጣ ብርና ወርቁ ሲመጣ አደርግባቸዋለሁ፣ እስከዚያ ግን በሰበዝ ይቆዩ ብላ ሰበዝ የምታደርግባቸው:: ሰዎች ግን፣ «ሰበዝ በጆሮሽ ላይ የምታደርጊው ለምንድን ነው?» ብለው ሲጠይቋት፣ «ጌጤ ክርስቶስ ስለሆነ ሌላ ጌጥ አያስፈልገኝም» ብላ በውሸት ትመልስላቸው ነበር:: ታዲያ በዚህ መልሷ የተገረሙ ሰዎች፣ «በቀራኒዮ መስቀል ላይ የተሰቀለው ክርስቶስ እርሱ ጌጥሽ ከሆነ ታዲያ ለምንድን ነው ሰበዝ በጆሮዎችሽ ያደረግሽው:: ሰበዙንስ ለምን አትተይውም» ቢሏት፣ «እይ እንዳይደፈንብኝ ነው::» ብላ መለሰች::

አዎ፣ እግዚአብሔር የአፋችንን ሳይሆን የልባችንን ይመለከታልና በልባችን ያሰብነውን እንሁን:: በልባችን ጠልተን በአፋችን አንውደድ:: በልባችን ረግመን በአፋችን አንመርቅ:: በልባችን ተቃውመን በአፋችን አንስማማ::

ግጥምጥም:- ልብሀ ያላለውን ተናግረህ የአፍህን፣
አፈ ቂቤ ሆነህ ልበ ጩቤ አትሁን::

«አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ»
(መዝ. 51፡10)

# የአርባ ቀን ዕድሌ

መጋቢው፣ «እግዚአብሔር ወደዚህ ምድር ሲያመጣን በከንቱ ሳይሆን በዓላማ ነው:: የሠራንም ለሥራ ነው እንጂ ለመቀመጥ አይደለም:: አምላክ በሰጠን ጸጋና ችሎታ ሁሉ፣ በሰጠን ዕድሜና ዘመን የበኩላችንን ድርሻ በታማኝነት ልንወጣ ይገባል:: ስንፈጠር ድሃ ሆነን አልተፈጠርንም ወይም ለድህነት አልተመደብንም፤ ነገር ግን ሁላችንም የየራሳችንን ኃላፊነት (ሥራ) በታማኝነት ስለማንሠራና በሌላው ትከሻ ለመኖር ስለምንፈልግ ድህነት ወርሶናል:: ስለዚህ ሁላችንም እግዚአብሔር ባስቀመጠን ቦታ እንደ እርሱ ፈቃድና ትእዛዝ ተግባራችንን ስንወጣ የሁላችንም ውጤት ተዳምሮ አገርን ይጠቅማል::» እያሉ ለተሰበሰበው ሕዝብ በሥራ የማደግ ባሕርይን ያስተምራሉ:: ትምህርታቸውንም የበለጠ ለማስጨበጥ ይህንን ምሳሌ ተናገሩ::

«በአንድ አገር የሚኖር ንጉሥ ልደቱን ለማክበር ፈለገና እያንዳንዱ የአገሪቱ ኗሪ መሳተፍ አለበት ብሎ አስቦ ቀጣዩን አዋጅ አስነገረ:: 'የአገሬ ሕዝብ ሆይ፣ ልደቴን በሚመጣው ወር መባቻ ላይ ስለማከብር ሁላችሁም ለግብር የሚሆን አንድ አንድ እንስራ ጠላ አዘጋጅታችሁ እንድታመጡ::' ይህንን አዋጅ የሰማ አንድ ሰው ጠላውን ማዘጋጀት ስንፍና ሆነበትና 'በጠላው ፋንታ አንድ እንስራ ውኃ ይዤ እሄዳለሁ' ብሎ አሰበ:: 'ምክንያቱም ይህች የእኔ አንድ እንስራ ውኃ ከዚያ ሁሉ ጋን ጠላ ውስጥ ብትገባ ውኃነቷ ይጠፋል እንጅ አትታወቅም' ብሎ አሰበና በተቆረጠው የንጉሥ ልደት ማክበሪያ ቀን አንድ እንስራ ውኃውን ይዞ ሄደ:: ሄዶም በጋኑ ውስጥ ሲገለብጥ በጋኑ ሙሉ ውኃ አዬ:: ለካስ እርሱ ብቻ ሳይሆን አንድ እንስራ ውኃ ይዤ እሄዳለሁ ብሎ ያሰበው የአገሩ ሰው ሁሉ ነበርና የንጉሡ ልደት በውኃ ተከብሮ ዋለ::»

አዎ፣ ሁሉም በታማኝነት የራሱን ድርሻ ሲወጣ ተደምሮ መልካም ውጤት ያመጣልና ዛሬም በተሰማራንበት መስክ ሁሉ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳንል ሥራችንን እንሥራ፤ ዋጋችንንም እግዚአብሔር ይከፍለናል:: በምድርም የዘራነውን መልካም ዘር እናጭዳለን:: ድህነት የአርባ ቀን ዕድሌ ነው ብለን ደምድመን ተስፋ አንቁረጥ:: የአርባ ቀን ዕድል የሚል ለድሃዎች የተሰጠ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም:: በውስጧ ለዓለም ሁሉ የሚበቃ ያልተነካ ሀብት በያዘች ድንግል መሬት ላይ ቁጭ ብለን ከማማረር እግዚአብሔር ይጠብቀን:: አሜን::

*የቃል ጥናት ጥቅስ: - «የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና» (ሮሜ 8:19)::*

ኤፌ. 2:10
2ኛ ተሰ. 3:6-10

ግጥምጥም:- *የአርባ ቀን ዕድሌ ብሎ ከማማረር፣*
*የአርባ ቀን ዕድልን ይሻላል መመርመር::*

# ደምህን አቁሜአለሁ

*የቃል ጥናት ጥቅስ: - «ነገር ግን ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍ ራቅ፤ ኃጢአተኝነታቸውን ከፊት ይልቅ ይጨምራሉና::» (2ኛ ጢሞ. 2:16)*

እንደተለመደው ከመኝታ በፊት በቁጥር በርከት ያለው ቤተሰብ በሙሉ ተገኝቶ አንድ ላይ የማታ የቤተሰብ ጸሎት አድርገን ነው የምንተኛው:: እና እስኪ ዛሬ አንድ ቃል ላካፍላችሁ ብለው ቁሉ ጀመሩ:: (የተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ እየተገኙ የቤት ለቤት ፕሮግራሞች የመካፈሉ ጉዳይ በእጅጉ አሳስቧቸዋልና::)

«በትሕትናና በተሰበረ ልብ የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብና ለመንፈስ ቅዱስ ስንታዘዝ እግዚአብሔር ለሕይወታችን በቃሉ በኩል ይናገረናል:: ነገር ግን በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ይህንን ጉዳይ ሳናስተውል ከመቅረታችን የተነሣ ለእኛ ሌላ ሰው ቃል እንዲነግረን፣ ሌላ ሰው እንዲጸልይልን፣ ሌላ ሰው መገለጥ እንዲያመጣልን በመፈለግ ስንሯሯጥ እንገኛለን:: እነዚህ ነገሮች ሁሉ መልካም ቢሆኑም የእውነት መገለጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚቀበሉ አገልጋዮች የመኖራቸውን ያህል በተቃራኒው ደግሞ የሐሰትን ቃል ከጥቅም ጋር አያይዘው የሚናገሩ፤ ሳይታያቸው ታየኝ፣ ተጨፍኖባቸው ሳለ ተገለጠልኝ የሚሉ መንፈሳዊ መሳይ አሳሳቾች አሉና ተጠንቀቁ:: መጽሐፍ ቅዱስ የያዘ ሁሉ ክርስቲያን፣ 'የሠራዊት ጌታ እንዲህ ይላል' ያለ ሁሉ እውነተኛ ነቢይ አይደለም:: ይህን ሳስብ አንድ የሰማሁት አሳፋሪ ድርጊት ትዝ አለኝ፣ እርሱን ልንገራችሁ» ብለው የሚከተለውን ምሳሌ ፊታቸውን ከስክሰው እንዲህ ሲሉ ተናገሩ::

«አንድ ሰፈር ውስጥ የማታ የጸሎት ፕሮግራም አለ:: ይህንን ፕሮግራም ለመካፈል ሰው ሁሉ እየተጠራራ፣ 'አንድ መገለጥ ያለው ሰው አለ፣ ኑ እንሂድ' እያለ ይመጣል:: በዚያም ቀን ምንም እንኳን ጊዜው ክረምት ሆኖ ቢበርድም፣ ሁሉም ሰው ጋቢውን፣ ካቦርቱን፣ ብርድ ልብሱን እየለበሰ ታደመ፤ ፕሮግራሙም ተጀመረ:: ጥቂት ሰዓት ከተጸለየ በኋላ ያ ታዋቂ አገልጋይ የተባለው አንድ ብርድ ልብስ ተከናንቦ ወንድ ይሁን ሴት ምንነቱ በማይታወቅ የተንበረከከ ሰው ላይ እጁን ጭኖ እንዲህ ብሎ ተናገረለት፤ 'የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ደምሽን አቁሜአለሁ ይላል' አለ:: ሰውዬው ደንግጦ 'ከንብንቡን አወረደና፣ 'ኧረ ወንድ ነኝ! ወንድ ነኝ!' አለ:: በዚህ ጊዜ ባለ ራዕይ ነኝ

ባዩ ሰው ማጣፊያው ቢያጥረው፣ 'አይ እንግዲህ ወንድም ብትሆን ደምህ ቆሞልሀል' ብሎት አረፈው።»

እዚህ ላይ ለአገልጋዮችም ለተገልጋዮችም መልዕክት አለኝ። በእግዚአብሔርም በሰውም ዘንድ ሲገለጥ ከክብር ይልቅ ውርደትን የሚያመጣ አገልግሎት አንስጥ፤ አንቀበልም። የከበረውን የእግዚአብሔርን የጸጋ አገልግሎት በግል ጥቅም፣ ስምና ዝና እንዳንለውጠው እግዚአብሔር በቸርነቱ ያግዘን፤ የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍር ሠራተኛም ያድርገን። አሜን።

ግጥምጥም:- *ያልተገለጠውን መግለጥ ከምትሞክር፣ የተገለጠውን ለመናገር ጨክን።*

ሕዝ. 34: 1-10

# ስኬት

ኮንፍራንሱን በጉጉት ሲጠብቅ ለነበረው ሕዝብ የዕለቱ ሰባኪ እንዲህ እያሉ መስበክ ቀጠሉ:: «በሕይወታችን ሁል ጊዜ መሰካት ሲገጥመን ሰይጣን ይህንን ተጠቅሞ እንዳይጥለን እንጠንቀቅ:: ብዙዎችን በመርዙ ወግቶ የጣለበት መሣሪያ አንዱ ስኬት ነውና ሁል ጊዜም በጠላት ወረዳ ውስጥ እንዳለን እናስብ እንጂ አንዘናጋ:: አሁን ያለንበትን ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከየት እንደመጣንም እናስብ፤ ያን ጊዜ እግዚአብሔር ይከብራል፣ እኛም ከጠላት ፍላጻ እናመልጣለን:: መቼም ቢሆን ምቾት፣ ማግኘት፣ ክብር፣ ዝና፣ ተቀባይነት ሲመጣ የዚህ ሁሉ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን እንርሳ:: እርሱን ከረሳንና ራሳችንን ከፍ ከፍ ማድረግ ከጀመርን ውድቀታችን ቀርቧል ማለት ነውና ተጠበቁ::» ለዚህ ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ አስረግጠው ተናገሩ::

«በአንድ ወቅት በሁለት አገሮች መሐል ያለችውን ደሴት ለመያዝ ሁለቱም አገሮች ለጦርነት በባሕር ማዶና ማዶ ተሰለፉ:: የአንደኛው አገር የጦር ኃይሉ በጦሩ መሐል ቀዶ ሄዶ በጀልባ ቀድሞ ደሴቲቱ ላይ ባንዲራ እንዲተክልና እንዲይዛት ለአንዱ ጄኔራል ትእዛዝ ሰጠ:: ይህም ጄኔራል በጀልባው አንደኛ ጐን የእነርሱን አገር ባንዲራ፤ በሌላው ጐን የጠላታቸውን አገር ባንዲራ ሳለና በመሐላቸው ከተወሰኑ ወታደሮች ጋር ባንዲራዎቹን በሳለበት ጀልባ ላይ ሆነው ሲሄዱ፣ ወዲህ ማዶና ወዲያ ማዶ የሰፈረው የጦር ኃይል ሁሉም በራሱ በኩል የየአገሩን ባንዲራ ሲመለከት በደስታ አጨበጨበ፣ ጮኸ፣ ሁካታ አስተጋባ:: በዚህ አስደናቂ ሥራው ጄኔራሉ ተደሰተ፤ ስኬት በማግኘቱም ልቡ ተኩራራ:: የተላከበትን ዓላማ ባንዲራ ተክሎ መምጣት ሲገባው ሳይተክል ጭብጨባውና አክብሮቱ ጥሞታልና፣ 'አንድ ጊዜ ልድገመው እስኪ' ብሎ ዞሮ በመሐላቸው ሲመለስ ሁሉም አሁን የየራሱን ባንዲራ ሳይሆን የጠላትን ባንዲራ በመመልከቱ፣ ወዲህና ወዲያ ማዶ የሰፈረው ጦር ተኩስ ከፍቶ ሁለቱም ወገን በጥይት እሩምታ አርከፍክፈው ጄኔራሉን ከነወታደሮቹ ገደሏቸው::»

አዎ፣ ዝና፣ ክብርና ስኬት ጠላት ሰዎችን የሚጥልባቸው ዋና መንገዶቹ ናቸውና እንጠንቀቅ:: ጸልየን ሰዎች ቢድኑ፣ ሰብከን ሰዎች ቢጽናኑ፣ ትንቢትና መገለጥ አምጥተን ሰዎች ቢመለሱ፣ ስጦታውን፣ ችሎታውንና ጸጋውን ላበዛልን ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን:: የራእያችን፣ የስኬታችን ምንጩ እግዚአብሔር ነውና፣ ጌታ ማስተዋሉን ያብዛልን::

*የቃል ጥናት ጥቅስ: - «... ባላጋራችን ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና...» (1ኛ ጴጥ. 5:8)::*

ዘዳግ. 8:11-18

*ግጥምጥም:- ዛሬ የሆንኩትን የሆንኩት በእርሱ ነው፣*

*ላከበረኝ ጌታ ክብሩን እሰጣለሁ::*

# መገለጥ ወይስ ማጋለጥ

ሰባኪው፣ «በዚህ ዘመን በአንዳንዶች ዘንድ ቅድሚያ እየተሰጠ ያለው ለእግዚአብሔር ክብር ሳይሆን ለእኛ ክብር ሆኗል፤ እንዲታወቅ የሚፈለገው እግዚአብሔር ሳይሆን እኛ ራሳችንና ስማችን ሆኗል። መቼም በየመንደሩና በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን የሚደረገው መንፈሳዊነት የመሰለው ግርግር አፍ አውጥቶ የሚናገረው ይህንን ነው። ዛሬ ነቢይ ነን ባዮቹም ሆነ ነቢይ ፈላጊዎቹ የሚሯሯጡት ለራሳቸው ጥቅምና ክብር ሆኗል። ይህንን ስናገር አዝናለሁ። ሙሉ ሥልጣን ያለው ሕያው ቃሉ በቤታችን ሽልፍ ላይ አቧራ እየጠጣ ከቃሉ ውጪ የሆነ የምን ይታይሃልና ምን ይታይሻል በሰዎች ስሜትና ፍላጐት ላይ ያተኮረ የሥጋዊ መገለጥ ልምምድ እውነተኛ መገለጥ ሳይሆን ማጋለጥ ነው። እውነትን የሚናገሩ እንዳሉ ሁሉ በተቃራኒው ግን አንድም ነፍስ በማይድንበት ለጆሮአቸው የሚጥሙ የራሳቸውን አስተማሪዎች/ነቢያቶች/ እየጋበዙ /እየተጋበዙ/ በየመንደሩ በክርስቶስ ስም የሚደረገው መንፈሳዊ ግርግር ይቁም! የራስን ክብርና ዝና በመፈለግ እግዚአብሔር ያላሳየውን አየሁ፣ እግዚአብሔር ያልተገለጠውን ተገለጠልኝ እያሉ ወንጌልን ለሥጋ ድሎት ማኖሪያ ማድረግና የዋህ ሴቶችን እየሰበሰቡ ማደናገር ይቁም። እግዚአብሔር ያላለውን፣ "ጌታ ፈውሶሃልና መድኃኒት እንዳትወስድ፣ ሐኪም ቤትም እንዳትሄድ" በማለት ሰዎችን መግደል ይቁም! "እግዚአብሔር ሊጠቀምብህ ይፈልጋልና ሥራህን ለቅቀህ ሙሉ ጊዜህን ካልሰጠህ ትቀሰፋለህ" በማለት ጌታ ባላለው መግባትና ቤተሰብን መበተን፣ ይልቁንም ጌታ ሳይፈውስ "ከኤች. አይ. ቪ. ኤይድስ ተፈውሰሃልና እከሊትን አግባ" ብሎ ሕዝብን መጨረስ ይቅር። ለሚለው ጊዜያዊ ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ፡-

አንድ መንደር ውስጥ ሁለት ሰዓት ጫማ ተወልቆ የሚገባበት ያለ አሥር ሰዓት የማይወጣበት መንፈሳዊ ፕሮግራም የሚካሄድበት የመሰለ ግን ከጥንቆላ ቤት ያልተናነሰ ሥራ የሚካሄድበት ቤት ነበር። እዚያ ፕሮግራም ላይ እግዚአብሔር ያላለውን የሚል ዛሬ በዝና ፈረስ ላይ ወጥቶ ሽምጥ የሚጋልብ ነገ ግን ተከስክሶ ከነመታሰቢያው ሊጠፋ የተዘጋጀ ነቢይ ነኝ ባይ ሰው እንዲህ ብሎ ተናገረ። «በዚህ እንዳትኖሪ ተለዪ ይልሻል ጌታ» ብሎ ተናገረ። ይህ መልእክት ለእኔ ነው ብላ የተቀበለች ሴት ከዚያ ጊዜ ጀምራ ሦስት ከወለደችለት ባለቤቷ ተለይታ

ልጆቿን ይዛ ወጥታ ዛሬ ከነልጆቿ የምትበላው አጥታ በረሐብ አለንጋ እየተቀጣች ትገኛለች፡፡

አዎ፣ ወገኖቼ ሆይ፣ እግዚአብሔር ያጣመረውን ከመለየት እንቆጠብ፡፡ እኛን የሚያኖረን ምላሳችን ሳይሆን እግዚአብሔር ነው፤ ብልጠታችንና ጥበባችን ሳይሆን በእግዚአብሔር መታመናችን ነው፡፡ ስለዚህ ያላየነውን ከመናገር ያየነውን ተናግረን እንሙት፡፡ ያልተገለጠልንን ተገለጠልን ከማለት የተገለጠውን ወንጌል ብቻ እንስበክ፣ እግዚአብሔር የሚባላ እሳት ነውና፡፡

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ክፋውን መልካም መልካሙን ክፉ ለሚሉ ጨለማውን ብርሃን ብርሃኑን ጨለማ ለሚያደርጉ፤ ጣፋጩን መራራ መራራውን ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው፡፡»

ግጥምጥም:- «ሳይታየኝ ታየኝ ብሎ ከማጨለም፣

ሁሌም በሕይወቱ አምላክ ያየው ይቅደም፡፡

| |
|---|
| ኢሳ. 5:20-21 |
| 2ኛ ጢሞ. 3:6-7 |

# ነብር በቤታችን አለ!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ... ጠቦቶቼን ጠብቅ» (ዮሐ. 21:16)

የዕለቱ አገልጋይ በየዓመቱ ሁለት ጊዜ እየተሰባሰቡ በሚመክሩበትና የእግዚአብሔርን ቃል ከእግዚአብሔር ሰዎች በሚሰሙበት የመሪዎች ስብሰባ ላይ እንዲህ እያሉ መልእክታቸውን ማሰማት ጀመሩ:: «እኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ከሚፈልግብን ዋናና የመጀመሪያው ነገር የምንመራቸውን መንጐቻችንን /ሕዝቡን/ መንከባከብ፣ መመገብና መጠበቅ ነው:: በተለይም በዚህ ዘመን የበጎቻችንን መልክ ለይተን ማወቅ በሚገባን ጊዜ ላይ ነው ያለነው:: ምክንያቱም የበግ ለምድ ለብሰው ሾልከው የሚገቡ ተኩላዎች አሉ:: ቃላቸው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከሚያተኩር ይልቅ በጊዜያዊ ስሜት ላይ ብቻ አተኩሮ፣ በቃሉ ላይ ያልተመሠረቱ ስሜታውያንን በስሜት ኰርቻ ላይ አሳፍረው በመንዳት ከቤት የሚያስወጡ ሐሰተኞች ናቸው:: ትምህርታቸው የሥላሴን ማንነት የሚክድ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በማመን ብቻ የሚገኘውን የጸጋ ዘላለማዊ ደኅንነት በሰዎች ጥረትና ሥራ መዳን እንደሚቻል የሚለውጥ ጭድ የሌላው ጭቃ ነው:: ከእነዚህ ሐሰተኞች ራሳችንና ሕዝባችንን ለማዳን ቤተ ክርስቲያን ሕዝቧን በራሷ አገልጋዮች የበለጠ በመጠቀም በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተና ሥር የሰደደ ትምህርት ማስተማር አለባት::» የሚለውን ትምህርታቸውን የበለጠ ለማስረዳት ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ::

ሁለት የተጣሉ ወንድማማቾች ማታ በጎች ከብቶች ወደ እየበረታቸውና ጋጣቸው ሲገቡ አንዱ ቆጥ ላይ አንዱ መደብ ላይ ሆነው ተኰራርፈው ይመለከታሉ:: ቆጥ ላይ ያለው ነብር ከእንስሳዎቹ ጋር አብሮ ተቀላቅሎ ሲገባ አይቷል:: እንዳይናገር ግን ተጣልተዋል:: ስለዚህ ዝም ተባብለው ጊዜው መሽቶ ሁሉም ተኙ:: ስለተጣሉ እንዱም ነብር እንቅልፍ እምቢ ብሏቸዋል:: ከቆጥ ላይ ያለው መደብ ላይ የተኛውን ወንድሙን ሲያዳምጠው ይወራጫል፤ ይቃኘዋል:: በዚህ ጊዜ በደረቁ ሌሊት በስሙ ወንድሙን ጠርቶ «ምን ሆነሃል? ቢለው፣ «በህልሜ ነብር በጫካ አይቼ ነው የምገላበጠው» አለው:: ቆጥ ላይ ያለው ወንድሙ ደግሞ፣ «ይኸው ነብር በጫካ ሳይሆን በቤታችን አለ» አለውና አረፈው::

አዎ፣ ዛሬም መንጋውን ሊያደሙና ሊበሉ መንፈሳዊ የመሰሉ ነብሮች ተመሳስለው በበጐች በረት አሉና ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል እውነቱን ከሐሰቱ፣ ምርቱን ከግርዱ ለይታ ልታወጣና መንጋዋን ልታድን፣ ልትጠብቅና ልትንከባከብ ይገባታል:: ይህንንም ለማድረግ ከብዛት ይልቅ ጥራት ላይ ማተኰር ይገባታልና ይህንን እንድታደርግ ጌታ ይርዳት:: አሜን::

ግጥምጥም:- እረኛው በጐቹን ካልለየ በቅጡ፣

ቤት ባዶ ይሆናል ተኩላዎች ካልወጡ::

2ኛ ጢሞ. 15:16

1ኛ ጴጥ. 2:1-21

## መንፈስ ቅዱስ የለም?

ሰባኪው፡ በሰንበት የእምላኩን ቃል ለመስማት ለተሰበሰበው ሕዝብ እግዚአብሔር የሰጣቸውን መልእክት በከፍተኛ ድምፅ እንዲህ እያሉ መስበካቸውን ቀጠሉ።

«እዚህ የተሰበሰብን ሁላችን ዛሬ ወደዚህ የመጣነው ሁሉን ቻይ የሆነው ጌታ ያስተምረኛል፣ ይፈውሰኛል፣ ያጽናናኛል ብለን ነው። ይህ መልካም አሳብ ነው። እግዚአብሔር አለ ብሎ አምኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ነው። አንዳንዶች ዛሬ ከዚህ የራቀ አሳብ ይዘው ነው ያሉት። ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚሄዱት በራሳቸው መመዘኛ ምሪት ብቻ ነው። "እዚያኛው ቤተ ክርስቲያን ነው የምሄደው ምክንያቱም እዚያ መገለጥ ስለሚናገሩ፣ ልሳን ስለሚናገሩ፣ በሽተኛ ስለሚፈውሱ፣ የታወቁ ነቢያቶች ስላሉ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ስለሚካሄድ፣ አምልኳቸው በሰዓት ሳይገደብ የተለቀቀ ስለሆነ፣ አጋንንት እየተንጫጫ ስለሚወጣ..." እነዚህ ሁሉ ፈር በያዘ ሁኔታ ቢካሄዱ መልካም ናቸው። ነገር ግን እነዚህን ማድረግ የሚችል እግዚአብሔር ስሙን በእውነት አምነው በሚጠሩት ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ አለና ባላችሁበት አባል በሆናችሁበት ቤተ ክርስቲያን ሆናችሁ ጠብቁት እንጂ የዘላን ኑሮ አትኑሩ። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን አፏን ሞልታ ይህንን ያህል አባል አለኝ ለማለት የተቸገረችበት ዘመን ላይ ነው ያለነው። ለምን ቢባል ስሙን አስመዝግቦ ልቡን የሚነሳ ምእመን በዝቷልና ነው። እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ።» ለሚለው ምክር አዘል ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ።

ድንገት አንድ ቀን ክትትል ትምህርት የማስተምረው ተማሪዬ እንዲህ ሲል አስደንጋጭ ነገር ነገረኝ፣ «ሁለተኛ እዚህ ቤተ ክርስቲያን አልመጣም፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ የለምና። ይኸው ሦስት ወር ሆነኝ፣ እስከአሁን በአምልኮ ላይ አጋንንት ጮኾ ሲወጣ አላየሁም። ሌላው ቤተ ክርስቲያን እየተንጫጫ ነው የሚወጣው።» አለኝ። በዚህ ጊዜ ራሴን ተቆጣጥሬ፣ «ወንድሜ፣ እውነቱ እንዲህ አይደለም። በአንድ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ የመኖሩ ምልክት የአጋንንት ጮኾ መውጣትና አለመውጣት አይደለም። ከፈለግክ ደግሞ ከሳምንት ጀምሮ ታያለህና ተስፋ ሳትቆርጥ ተመላለስ» አልኩትና ተለያየን። እኔም ለዚህ ሰው ጌታ በሚገባው መንገድ ራሱን እንዲገልጥለት፣ ቢቻል ወደ ቤተ

ክርስቲያን አጋንንት የሰፈረበት ሰው መጥቶ ጮኾ ሲያወጣ እንዳይ ጸለይኩ። እግዚአብሔርም ታማኝ ነው። ብዙም ሳይቆይ በሳምንቱ እርሱ ከተቀመጠበት ሁለተኛው ወንበር ላይ አጋንንት የያዘው ሰው ልክ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ሲጀመር ተነሣና ተፈጠፈጠ። በጣም ደስ አለኝ። ሰው ሁሉ «በኢየሱስ ስም» ሲል፣ እኔ፣ «ኢየሱስ ጌታ ነው» አልኩኝ። ከአምልኮ መጨረሻ የከትትል ተማሪው ወደ እኔ መጥቶ፣ «በእውነት የእግዚአብሔር መንፈስ በዚህ ቤተ ክርስቲያንም አለ።» በማለት ንስሐ ገባ።

አዎ፣ እግዚአብሔር በእምነት በመጽናትና በተስፋ ለሚጠባበቁት በአሉበት ቦታ ተገልጦ ተአምራቱን ይሠራል፤ ጠላትንም ያሳፍራልና በአስቀመጠን ቦታ በፍቅር፣ በጸሎትና በታማኝነት እንድንጠብቀው ጌታ ሁላችንንም ይርዳን።

ጥቅስ:- «ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ» (ዮሐ. 14:14)

ግጥምጥም:- እግዚአብሔር በቦታ መቼ ይገደባል፣
መንፈሱና ስሙ በየትም ይሠራል።

| |
|---|
| 1ኛ ቆሮ. 15:58 |
| ኢሳ. 35:3-4 |

## ክፍል 7
## እግዚአብሔርን ስለመጠበቅ

# በክሰኛ አፍንጫውን ይሰበራል!

የቃል ጥናት ጥቅስ፥ «ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ።» (ኤር. 29፡11)

ሰባኪው፥ «ብዙ ጊዜ ሰይጣን ባለንበት ሁኔታ እንድናጉረመርም እንጂ እንድናመሰግን አይፈቅድምና ኃጢአታዊ ተፈጥሮአችንን ተጠቅሞ በብስጭት፥ በቁጣና በማጉረምረም ሕይወት ይሞላናል። ሆኖም አሁን ካለንበት ሁኔታ ወዲያ እግዚአብሔር የተሻለ ነገር እንዳዘጋጀ ማመንና ማወቅ ለሰይጣን የማያዳግም ምላሽ ነው። ማንኛውም ሰው ገባውም አልገባውም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያለንበት ቦታ የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት የሥራ ቦታ ነው። እዚህ ያለነው ለሥራና ለተሻለ ነገር ነው። ይህንን የተረዳና ያመነ ክርስቲያን የጊዜውን መከራ ችሎ ከመከራው ባሻገር አምላኩ የሚሠራውን ድንቅ ሥራ በእምነት ሊጠባበቅ ይገባል። እግዚአብሔር ያያልና።» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንዲት ሰው ቤት የምትሠራ ሠራተኛ ነበረች። ከእምነቷ የተነሣ ብዙ መንከራተትና ሥራ ማጣት ቢደርስባትም በእምነቷ የጸናች ነበረች። እና ጌታም ለሥራ አንድ ጌታን ከማይወዱ አክራሪ ሰዎች ቤት ውስጥ ከተታት የምትጸልይበትም ስለአጣች ቤተሰቡ መተኛታቸውን ካረጋገጠች በኋላ ኩሽና አመድ ላይ ተንበርክካ ትጸልይ ነበር። በዚህ ጊዜ እመቤቷ ከመኝታ ቤታቸው ይሄዱና ጸጉሯን ይዘው፥ «ተነሽ፥ አንቺን ብሎ ጸላይ፡፡ ጴንጤ ደግሞ እቤቴ ገባ፡፡ ሁለተኛ ባገኝሽ አንቺን አያርገኝ» ብለው ሄዱ። ደነገጠች፥ «ተኝተው አልነበር እንዴ? እንዴት ሰሙኝ? ድምጼን ዝቅ አድርጌ ነገ እጸልያለሁ» አለች። አሁንም መጥተው አደናቀፉዋት። የመጨረሻም ማስጠንቀቂያ ሰጧት። እርሷም፥ «ሐናን የሰማ ጌታ እኔንም ይሰማኛል። በቃ አሁንም ድምጼን ሳላሰማ እጸልያለሁ» ብላ ስትወስን፥ የጌታ መንፈስ ምሥጢር ገለጠላት። ጉዳዩ ከድምጽ አይደለም። አንቺ ስትንበረከኪ በሴትዮዋ ውስጥ ያለው ሰይጣን ያውቃልና ስትሰሚ ገስጪ አላት። በደስታ ዘለለች። እንዲህም አለች፥ «ነገ ማታ የእኔ ጌታና የእሜቴ ጌታ ይዋጣላቸዋል።» እንዳለችውም በቀጣዩ ቀን ማታ አመዱ ላይ ተንበርክካ ስፍራ ወደማይወስነው ጌታ ስትጸልይ እሜቴ እንደለመዱት በሩን ከፍተው መጥተው ጸጉሯን ሊይዙ ሲሉ፥ «በኢየሱስ ስም» ስትል እሜቴ ወደቁ። ጸልያላቸው አጋንንቱ ለቅቋቸው ወደ አእምሮአቸው ሲመለሱ ያዩት ነገር የተገላቢጦሽ ሆነባቸው በ60 ብር የቀጠሯት ሠራተኛቸው በክብር ቆማ እሳቸው ሽቶ በጠገበው ቢጃማቸው አመድ ላይ ተንከባልለው ባዩ ጊዜ፥ ልጄ፥ ምን ሆኜ ነው?» አሉ። እርሷም፥ «ምን ያልሆኑት አለ» ብላ ሊገድላቸው ከነበረው አጋንንት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደፈወሳቸውና እርሱን ማመን እንዳለባቸው መናገር

ስትጀምር፥ እጁን ይዘው፥ «ነይ፥ ይህንን ያዳነኝን ጌታ ወንጌል አመድ ላይ አትነግሪኝም፥ ወደ ሳሎን ቤት እንሂድ» ብለዋት ሄዱ፥ ያመዱ ዘመን አበቃ።

አዎ፥ እግዚአብሔር የሚጎበኝበት ጊዜ አለው እና ባስቀመጠን ቦታ ሳናጉረመርም የፊታችንን ክብር እያየን እናገለግለው በክሰኛ አፍንጫውን ይሰበራል። በፊት ያለውን ክብሩን እያለመ የዛሬ ውበቱን ያጣል። በአሸናፊነትም ክብሩን ይጎናጸፋል። ክርስትናም እንዲሁ እንደሆነ እንድናስተውል ጌታ ይርዳን።

ግጥምጥም:- ባስቀመጠን ቦታ ብንቆም ይሻላል፥

የጊዜው መከራ እንደ ጥላ ያልፋል።

ኤር. 2፡2
ኢሳ. 54፡4-5

# የሩቅ ሣር ለምለም መስሎ ይታያል

## የቃል ጥናት ጥቅስ፦ «እርሱም አይዋሽም፤ ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው እርሱ አይዘገይም።» (እንባ. 2፡3)

ሰባኪው፥ «በዚህ ዘመን ሰይጣን የእኛን ሕይወት በምሳሌ ውስጥ የሚከተው እንዲህ እያለ ተስፋ በማስቆረጥ ነውና አትስሙት። ‹እግዚአብሔር ጸሎትሽን አይሰማም፥ የተስፋ ቃልሽንም አይፈጽምም፥ ትቶሻል፥ ትቶሃል። ይህንን አገር ለቅቀሽ ሂጂ› በማለት ነው። እግዚአብሔር በእውነት ማንንም አይተውምና ተስፋ አትቁረጡ፤ የዘገየው ለበጎ ነው። ለበለጠ ጥቅም (ክብር) ነው። የእኛ ነገር ይገደዋል፥ ደግሞ አንድ ልጁን የሰጠን ጌታ እንደ ፈቃዱ ከሆነው ምንም ነገር አያጎድልብንምና ተስፋ እንቁረጥ። ሥጋ፥ ዓለምና ሰይጣን በመተባበር የሚሰብኩንን ስብከታቸውን አንስማ። የሩቅ ሣር ለምለም መስሎ ይታያልና ጌታን እንጠብቅ። እግዚአብሔር ከልባችን ይልቅ ታላቅ ነውና በልባችን የምንመኘውን ለክብሩና ለጥቃማችን የሆነውን ያደርጋልና ተስፋ ሳንቆርጥ፥ የጠላትን ክስ ሳንሰማ በእምነት ጸንተን ልንጠብቀው ይገባል።» ለሚለው ስብከታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ፦

በግብርና የሚተዳደር አንድ ገበሬ ሁልጊዜ እንደዚህ የሚል ምኞት ነበረው። «መቼ ነው ይህች ላሜ ወልዳ ባለቤቴ ቂቤ የምትቀባው? ልጆቼ አጓት፥ አይብ፥ አሬራ፥ የሚጠጡት?» ይህንን ሁልጊዜ ያስባል፥ ያልማል፤ ነገር ግን ላሚቱ ልትወልድ አልቻለችም። መደበኛው የምትወልድበት ጊዜ አለፈ። አሁን ላሚቱ አሥር ወሯ ገብቷል። ሳትወልድ ስለዘገየችበት ገበሬው አዘነ፥ ከላይ የተመኘውም ምኞቱ ሁሉ ከንቱ መስሎ ታየው። ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም በጊዜው ለበጎ አድርጎ ይለውጣልና ላሚቱ በጣም ደስ የምትል ኾንጉርጉር፥ ነጭ፥ ጥቁር፥ ቡናማ የተለያዩ ቀለማት በጥሩ የአቀማመጥ ሁኔታ ያላት ጥጃ ወለደች። በዚህ ጊዜ ገበሬው ምኞቱ ሁሉ በእግዚአብሔር ጊዜ እንደሆነለት አውቆ ለካ አምላኬ የዘገየው እያበጃጀ ነው።» ብሎ ተናገረ።

አዎ፥ ወገኖቼ፥ እግዚአብሔር የዘገየው ነገራችንን እያሳመረ፥ የበለጠ የተሻለ እኛ ከምናስበውና ከምንገምተው፥ ከምንጠብቀው በላይ ውብ እያደረገ እንጂ ሰይጣን እንደሚለው ረስቶን፥ ትቶን አይደለምና ተስፋ አንቁረጥ፤ ከምሬትና ከማጉረምረም ወጥተን በጊዜው የጊዜውን ሥራ በመሥራት እጅን በአፍ ላይ የሚያስጭነውን ጌታ ብቻ እንድንጠብቅ ጌታ ይርዳን። አሜን።

ግጥምጥም፦ ተስፋ እንዲህ መቁረጤ ከቶ ለምንድን ነው? | የሐዋ. 27፡25

የእኔ ጊዜ ቢያልፍም የእግዚአብሔር ገና ነው።

# ጠብቀነው ጠብቀነው

የቃል ጥናት ጥቅስ፦ «እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፥ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፥ አይደክሙም» (ኢሳ. 40፡30-31)

መጋቢው፥ «እግዚአብሔር ለሚጠብቁት በእውነት ታማኝ ነው። በጊዜውና በሰዓቱ ይደርሳል። አንዳንድ ጊዜ በሕይወታችን የተወገና የረሳን ወይም የዘገየ የመሰለን ጊዜውን እየጠበቀ እንጂ ጌታ ልጆቹን ረስቶ አይደለምና በትዕግሥት እንጠብቀው። ልክ እንደ ቃሉ፥ «የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልከተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።» (ዕብ. 12፡2)። ቅዱሳን ሆይ፥ በፊቱ ስላለው ደስታ የሚለውን ልብ ብላችሁ አስተውሉ። ደስታ በፊታችሁ አለ ግን መታገሥን ይጠይቃል፤ ነውርን መናቅ ይጠይቃል፤ ሁሉን ቻዩን ጌታ ኢየሱስን ብቻ መመልከት ይጠይቃል፤ የነገሮቻችንን ፈጻሚና ራስ የሆነውን አምላክ በትዕግሥት መጠበቅ ይጠይቃል።» ለሚለው ገሩምና ድንቅ መልእክታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ።

የሕጻናት ሰንበት ትምህርት አስተማሪዋ እግዚአብሔርን ስለመጠበቅ በዕድሜያቸው ለጋ ለሆኑ ልጆች እንዲህ እያለች ታስተምራለች»። ልጆች፥ እግዚአብሔር በእምነት ለሚጠባበቁት ይደርሳልና ከተንኮልና ከክፋት እየራቃችሁ ጠብቁት» አለቻቸው። በዚህ ጊዜ አንዱ ልጅ እጁን አውጥቶ እንዲህ ሲል ጠየቀ። «ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ባይመጣ ምን እናድርግ?» መምህሯም እንዲህ ብላ መለሰች፥ «ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ ባይመጣ እንደገና ጠብቁት» አለቻቸው። በዚህ ጊዜ መልሱ ያላጠገበው ያ ሕጻን ልጅ እንደገና ጠየቀ ደስ በሚሉ እንደበቱ፥ «እኔ እኮ የምለው ቲቸር፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው፥ ጠብቀነው ባይመጣስ ነው የምለው» አለ። መምህሯም መልሳ፥ «ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ፥ ጠብቃችሁ ባይመጣ አሁንም ጠብቁት።»

አዎ፥ ወገኖች፥ ካቻምና ጠብቀነው፥ አምናም ጠብቀነው፥ ዘንድሮም ጠብቀነው አልመጣ ይሆን? በጉዳዮቻችን ላይ እግዚአብሔር ታማኝ ነው በጊዜው ይደርሳልና አሁንም ጠብቁ። ተስፋ አትቁረጡ። ባለመታከት የማይታክተውን ጌታ እንድንጠብቅ ከራሳችን እርምጃ ጌታ ይጠብቀን። አሜን!

ዘኁል. 23፡19
ኢሳ. 41፡13

ገጥምጥም፦ ተስፋ የሚታደሰው በተስፋ ነውና፥
አምላኬን ልጠብቅ ዛሬም እንደገና።

# እግዚአብሔር ጊዜ አለው

ሰባኪው፣ «ይዋል ይደር እንጂ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚጐበኝበት የራሱ ጊዜና የራሱ መንገድ አለው:: ስለዚህ የጌታን ጊዜና የጐብኝቱን መንገድ እንጠብቅ እንጂ አንቸኩል:: እግዚአብሔር አይዘገይም፣ ደግሞም አይቸኩልም፤ ግን የታቀደ የተወሰነ የራሱ ጊዜ አለው:: አንዳንድ ጊዜ የዘገየ፣ ጠላታችንም ሊወርሰን ያለ ይመስለንና እንደ ሳኦል የራሳችንን እርምጃ እንወስዳለን፣ (1ኛ ሳሙ. 13:8):: 'ሳኦልም ሳሙኤል እንደቀጠረው ጊዜ ሰባት ቀን ቆየ ሳሙኤል ግን ወደ ጌልጌላ አልመጣም::' ይህ ግን እግዚአብሔር እመጣለሁ ብሎ ተናግሮ የቀረበት ሳይሆን ሰዓቱ እስኪሞላ የቆየበት ነው:: ዛሬም የእግዚአብሔር ጊዜ ደርሶ ጽዋው እስኪሞላ እንጠብቅ እንጂ በዓለም፣ በሥጋና በሰይጣን ተገፋፍተን አንዳች ማድረግ የለብንም» ለሚለው ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተናገሩ::

«ሰፈሩ ሁሉ የሚሰግድለት አንድ ሀብታም ሰውና በተቃራኒው ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ የሆነበት አንድ ድሃ ሰው ነበሩ:: ታዲያ አንድ ቀን ሀብታሙ ሰውዬ ሰው ሁሉ ሲሰግድላቸው የዚህ ድሃ ሰው አለመስገድ አበሳጭቷቸዋልና እንዲህ ብለው ጠየቁት:: 'አንተ! ሰው ሁሉ ለእኔ ሲሰግድ አንተ ወድቀህ የማትሰግደው ለምንድን ነው?' ቢሉት፣ ለካ ድሃው አማኝ ኖሯልና 'ስግደት የሚገባው ለፈጣሪ ብቻ ነው፤ ሰው ለሰው እንዴት ይሰግዳል? ደግሞስ እኔና እርስዎ ምንድን ነው ልዩነታችን? እርስዎም አንድ እንጀራ ነው የሚበሉት እኔም አንድ እንጀራ ነው የምበላው' ሲል መለሰ:: በዚህ ጊዜ ሀብታሙ 'ጉዳዩ ከእንጀራው ሳይሆን ከወጡ ነው:: ለመሆኑ እንደ እኔ አራት ዓይነት ወጥ ትበላለህ?' ቢሉት፣ የእርሱ ወጥ ከአንድ አያልፍምና ዝም አለ:: በዚህ ሁኔታ እየጸለየ ሳለ ያሉበት ሰፊ ግቢ ለንግድ ሥራ አመች ነበርና ለራሱ ትንሽ ቦታ ብቻ አስቀርቶ ለባለሀብቶች በብዙ ሺህ ብር ሸጠላቸው:: አሁን ኑሮውም፣ ወጡም ተስተካከለና ያንን ሀብታሙን ጐረቤቱን ሰው አንድ ቀን መንገድ ላይ አግኝቶ 'ጌታዬ፣ የእርስዎ ወጥ አራት ዓይነት ነው አይደል? የእኔ አሁን ስድስት ገብቷል፤ እግዚአብሔር በጊዜው ከነወጡ ያበላል' አላቸው::»

አዎ፣ የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ አንገታችንን የደፋንበትን ነገር ይጐበኝና እኛም ቀና ብለን እንሄዳለን:: በእውነት እግዚአብሔር ስለ ተስፋ ቃሉ ሲል አይዘገይምና ይህንን አስተውለን ከምንወስደው ሥጋዊ እርምጃችን ጌታ ይጠብቀን::

*የቃል ጥናት ጥቅስ: - «አላበጀህም፣ አምላክህ እግዚአብሔር ያዘዘህን ትእዛዝ አልጠበቅህም፤ ዛሬ እግዚአብሔር መንግሥትህን በእስራኤል ላይ ለዘላለም አጽንቶልህ ነበር» (1ኛ ሳሙ. 13:13)::*

*ግጥምጥም:- እግዚአብሔር በጊዜው አውቃለሁ ይመጣል፣*
*ሳልቀድመው ታግሼ ልጠብቅ ይገባል::*

ዘፍጥ. 18:10፤ 21:1፤ መክ. 3:1

# ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም

የቃል ጥናት ጥቅስ: «አምላካችሁን እግዚአብሔርን ታመልኩታላችሁ እርሱም እህልንና ውኃህን ይባርካል፤ በሽታንም ከመካከልህ አርቃለሁ::»

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔርን በእውነትና በፍቅር ብናመልከውና ብንከተለው እኛን የሚያኖረን እግዚአብሔር ነው:: የዕለት እንጀራችንን የሚሰጠን እግዚአብሔር ነው:: አንዳንዶች ከዚህ እውነት ርቀው ራሳቸውን በራሳቸው ለማኖር ምድዊ ብልጽግናን ለማትረፍ የራሳቸውን መንገድ ይጠቀማሉ:: የሌላውን እንጀራ በሐሰት በማጭበርበር ሲዘርፉና ሲያካብቱ በጥንቆላ፣ በአስማት፣ በሰላቢ፣ የአልጠግብ ባይነት ሥራ ሲሠሩና ሲያሠሩ ይታያሉ:: ጉቦ ሲበሉና ሲያመቻቹ ይውላሉ:: በቴሌቪዥን ግዙን ብለው ጥሩ ዕቃዎች አስተዋውቀው በግምባር ዋንኛው ሲመጣ መናኛውን ሲያቀርቡ ይገኛ ሉ:: በሐሰት ዘመናዊ ሐብትን ሊያግበሰብሱ ይሯሯጣሉ:: እውነቱ ግን ወዲህ ነው:: እግዚአብሔር ያልባረከው ብልጽግና ቋሚ ሳይሆን ጠፊ ነው፤ የሚያስከብር ሳይሆን የሚያዋርድ ነው፤ የሚያሳድግ ሳይሆን የሚጥል ነው፤ በልብ ደስታ የሚያኖር ሳይሆን በሕሊና ወቀሳ የሚያኖር ነው፤ በቅን መንገድ ሳይሆን በድጥ መንገድ የሚያስኬድ ነው:: ዛሬ አንዱ በሌላው እንጀራ ላይ አፈር እየጨመረ፣ ግማሹ ሲጠግብ ግማሹ ተርቦ ያድራል:: በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይሁን:: እግዚአብሔርን አምልኩት፤ እርሱ ያላችሁን እህል ውኃ ይባርክላችኋል::» ለሚለው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

አንድ ሰው ለጓደኛው፣ በሕልሜ በሬ ሊወጋኝ ሲያሳድደኝ አደረ:: ላመልጠውም ቤት ብገባ አብሮኝ ይገባል፣ ባህር ውስጥም ብገባ እሳት ውስጥም ብገባ፣ ቤተ መንግሥትም ብገባ በሁሉም አብሮኝ ይገባል:: ይህ ምንድን ነው እባክህ?» ብሎ ቢጠይቀው፣ ጓደኛው፣ ጥያቄውን በጥያቄ ለመመለስ እንዲህ ይለው ጀመር፣ ብድር አለብህ?» «የለብኝም::» «ከሰው ጋር ተጣልተሃል?» «አልተጣላሁም::» «እሺ፣ ከመሥሪያ ቤት ሰውን በግፍ ከሥራው አባረሃል?» «አላባረርኩም::» «እሺ፣ የምትተኛው ምን ላይ ነው?» የጭድ ፍራሽ ላይ ሲለው ጓደኛው እንዲህ አለው፣ «በቃ ተወው፣ በሬው ታዲያ ምን ያድርግ? እንጀራው ላይ ተኝተህበት እኮ ነው የሚያሠቃይህ::» ብሎት አረፈው::

አዎ፣ መቼም ይህ ምሳሌ የሚያስቅ ቢመስልም ወደ ሰዎች ስንመልሰው ግን እውነትነት አለው። ዛሬ ዓለማችን እርስ በርሷ የምትበጣበጠው አንዱ በሌላው እንጀራ ላይ እየገባ፣ ራሱን አሳድጎ ሌላውን ለመጣል በሚያደርገው ትግል ነው። ወገኖች፣ እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችን አምነን ብንከተለው እንጀራችንን /ኑሮአችንን/ እርሱ ይባርካል፣ ከዓለም መጨረሻ ሳይሆን ከዓለም መጀመሪያ ያደርገናል። እስቲ ቆም ብለን እናስብ። ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የበላና ደስ ብሎት የሚኖር ማን ነው? ማንም የለም። የእኛን እንጀራ የሚባርክ እግዚአብሔር ነውና ከዚህ ክፉ አሳብ ተመልሰን ኑሮዬ ይበቃኛል ወደሚለው እግዚአብሔርን የማትረፊያ መንገድ እንድንመለስ ጌታ ይርዳን።

ግጥምጥም:- «እንጀራ በእንጀራ እያነባበርኩኝ፣
በአሳብ ከመኖር ፈጽሞ ይቅርብኝ።

| |
|---|
| 1ኛ ጢሞ. 6:6 |
| 2ኛ ተሰ. 3:11፣ 12 |

## ክፍል 8
## እግዚአብሔን በሙሉ ኃይል ስለማገልገል

# የአሜሪካን ፕሬዚዳንት

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ::» (1ኛ ጴጥ. 5:4)

ቤተ ክርስቲያኒቱ እንደተለመደው በዓመት ሁለት ጊዜ ባላት የአገልጋዮች የትምህርት ጊዜ ላይ መጋቢው እንዲህ እያሉ ማስተማር ቀጠሉ:: «እኛ አገልጋዮች ሙሉ ዋጋችንን የምንቀበለው ከምድር ወይም ከሰው ሳይሆን ከእረኞች አለቃ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነውና፣ እርሱን እያየን እናገለግል:: ደግሞ በዚህ ምድር ላይ የምናገኘው ነገር ሁሉ ያልፋልና፣ የማያልፈውን የክብር አክሊል ለማግኘት እንድከም:: በድካማችን ተገቢውን ክፍያ አለማግኘ ታችን ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም:: ለድካማችን በሕዝብ ዘንድ ክብር አለማግኘታችን ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም::ዛሬ በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘ ነውን ክብርና ወደፊት ደግሞ የእረኞች አለቃ ሲገለጥ የምናገኘውን የማያልፈውን የዘላለም የክብር አክሊል እያሰብን በደስታ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳንል በታማኝነት ልናገለግለው ይገባል:: ይህንን ሳስብ አንድ የሰማሁትን ምሳሌ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ::»

በአንድ ሐገር ውስጥ ለ40 ዓመት በሚሽነሪነት ያገለገሉ ባልና ሚስት ነበሩ:: ታዲያ ከዚያ አገር አገልግሎታቸውን ፈጽመው ወደ አገራቸው አሜሪካ ሲመለሱ እነርሱ ሲያገለግሉ የቆዩበትን አገር በዕረፍታቸው ለአንድ ሳምንት ጎብኝተው የሚመለሱት የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ባሉበት መርከብ ነበር እየተመለሱ ያሉት:: ሀገራቸውም አሜሪካ ሲደርሱ የሀገሩ ሕዝብ ወጥቶ የተለያዩ መፈክሮች፣ ፊኛዎች ነጫጭ እርግቦች፣ አበባዎች፣ ይዘው በደስታ ጮኸት ፕሬዚዳንቱን ሲቀበሉ ሚሽነሪው አዩና በጣም አዝነው እንዲህ አሉ:- «እኔ ለ40 ዓመት እግዚአብሔርን አገልግዬ ነጩ ቆዳዬ በጥቁር ተበርዞ ሲመጣ ማንም የእቅፍ አበባ ይዞ አልተቀበለኝም:: እኚህ ፕሬዚዳንቱ ግን ለሳምንት ቆይተው ከዕረፍት ሲመለሱ ይኽ ሁሉ ክብር ጠበቃቸው::» በዚህ ጊዜ ባለቤታቸው፣ ይህንን አመለካከትህን ሳትቀይር ከዚህ መርከብ አንወጣም::» አሏቸው:: አብረውም ጸለዩ:: እግዚአብሔርም በመንፈሱ እንዲህ አላቸው:: ይህ የሚያልፍ ክብር ነው፣ የማያልፈውን የክብርን አክሊል እኔ እሰጣችኋለሁ::

አዎ፣ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሆይ፣ የማያልፍ የክብር አክሊል ሊሰጠን ጌታ ታማኝ ነውና በሚያልፈው ክብር ተጠላልፈን እንዳንወድቅ እንጠንቀቅ:: የሚያልፈውን የዛሬውን ክብር እየናቅን የማያልፈውን ክብር ለማግኘት እንድንደክም ጌታ ይርዳን::

ግጥምጥም:- ለሚያልፈው ክብር ለምን እለፋለሁ፣
በቃ ከእንግዲህ ይቅርብኝ ብያለሁ::

2ኛ ጢሞ.4:6-8
መዝ.75:6

# የቄሳርን ለቄሳር

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹም ኃይልህ ውደድ።» (ዘዳግ. 6:5)

ሰባኪው በዕለቱ ስለ መስጠት ለተሰበሰበው ሰው ሲያስተምሩ እንዲህ አሉ:- «እግዚአብሔር የተከፋ ልብ ሁለት አሳብ ያለውን አገልግሎትና አምልኮ አይፈልግም። አንድ እግራችንን በዓለም ሌላውን በቤተ ክርስቲያን አድርገን መመላለስ የለብንም። በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች የብዙ ነገር ሰዎች ሆነናል። እንዲያው ለደንቡ ቤተ ክርስቲያን መጥተን እንቀመጣለን እንጂ ለዚህች ለእግዚአብሔር ስጠተናታል ለምንላት የሦስት ሰዓት ጊዜ እንኳ ግማሹ አሳባችን (ልባችን) ውጪ ነው ያለው። በሥጋችን ጉባኤው መሐል ተቀምጠን፣ በልባችን ግን ወይ ስለ ቤታችን እናስባለን፣ ወይ ከሰዓት ስለሚኖረን የሠርግ ጥሪ፣ ወይ ከአምልኮ በኋላ ስለሚሰበሰበው ዕቁብ፣ ወይም ከአምልኮ በኋላ ከቤተሰባችን ወይም ከእጮኛችን ጋር ስለምናሳልፈው ጊዜ፣ ሌላም ሌላም እናስባለን። ይህ ሁሉ ባልከፋ ነበር። ነገር ግን አምልኳችን በግማሽ ልብና አሳብ መሆኑ እግዚአብሔርን እጅግ ያሳዝነዋልና ጌታን ስናመልክ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርገን በጌታ ፊት መሆን ያስፈልጋል።» ለሚለው ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ።

የልጆች ሰንበት ትምህርት አስተማሪዋ ልጆችን የሰንበት ትምህርት እያስተማረች በዓይኗም ከእርሷ ጋር በሙሉ ልባቸው መሆናቸውን አለመሆናቸውን በዓይኗ ትከታተል ነበር። ታዲያ አንደኛው ልጅ በዓይኑ እርሷን ይመልከት እንጂ በሃሳቡ ከእርሷ ጋር እንደሌለ ገባትና። የምታስተምረውን ትምህርት ቆም አድርጋ ተማሪዎችን ጥያቄ ጠየቀች። «መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ስንት መጽሐፍት አሉት?» በዚህ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች ለመመለስ እጃቸውን አወጡ። እርሱም ምን እንደ ተባለ ሳይሰማ በግማሽ አሳቡ እጁን አብሮ አወጣ። አስተማሪዋም እራሱን፣ እሺ፣ አንተ መልስ» ስትለው፣ «የምስጋና ቀን ነው ለእኛ ዛሬ» ብሎአት አረፈ።

አዎ፣ ሁልጊዜ በግማሽ ልብ ከሆንን የእግዚአብሔር ነገር ያመልጠናል ሁለት አሳብ አንሁን። የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር እናድርግ እንጂ አናቀላቅል። ሁለት አሳብ ያለው ሁለት ጊዜ አይኖርም። በዚህ ምድር ላይ አንድ ጊዜ ብቻ ኖረን ነውና የምናልፈው በምንኖርበት ዘመን ሁሉ ጌታን በፍጹም ኃይላችን በፍጹም ልባችንና በፍጹም ነፍሳችን አምልከነውና አገልግለነው እንድናልፍ ጌታ ይርዳን።

ግጥምጥም:- ልጄ ሆይ፣ ልብህን ሁሉ ስጥ እያለ፣
ግማሽ ልብ ሰጠሁት ሙሉ ሰጥቶኝ ሳለ።

ኢያሱ 14:8

# ኃይሌ ገብረ ሥላሴና ቀነኒሳ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ያገባህልን ዕብራዊው ባሪያ ሊሣለቅብኝ ወደ እኔ ገባ፤ እኔም ድምፄን ከፍ አድርጌ ስጮኽ ልብሱን በእጄ ተወና ወደ ውጭ ሸሸ።» (ዘፍጥ. 39:17፣18)

ሰባኪው፣ «ብዙ ጊዜ እንደተገነዘብኩትና ቃሉም እንደሚያረጋግጥልን በክርስትና ሕይወታችን የማሸነፊያው መንገድ እኛ ዝም ብለን ለጻድቅ ፈራጅ ጌታ እሳልፈን ስንሰጠው ነው። ዮሴፍ ይህንን ነው ያደረገው። ዮሴፍ ለጴጥፋራ ሚስት የሐሰት ክስ የመልስ መልስ ሲሰጥ አንመለከትም። የእውነት አምላክ በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራትን እመልሳለሁ ያለ ጌታ የመልስ መልሱን ሰጠለት። ለምንድን ነው ዛሬ በሕይወታችን ስልፍ የሚበዛብን፣ ከጐረቤት ከቤተ ክርስቲያንና ከመሥሪያ ቤት ሰዎች ጋር ሰላም ያጣነው? መልሱ ለጌታ ጊዜ ሳንሰጠው የመልስ መልሱን እኛ በለምንሰጥ ነው። በዚህ ዓለም ስንኖር የሚደግፉን እንዳሉ ሁሉ የሚነቅፉንም አሉ። ይህንን ካወቅን እንጐዳም። በክርስትና የሕይወት ሩጫ ውስጥ ሕዝቡ ሁሉ ይደግፈናል ማለት የለብንም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑን እርግጠኞች ከሆንን ለእርሱ ዕድል ፈንታ እንስጠው እንጂ እንደ ሥጋችን ፈቃድ ለመጣብን እመልሰዋለሁ ብለን የመልስ መልስ ለመስጠት ቆም ብንል ሽንፈት ይገጥመናል። የእግዚአብሔርንም እጅ ሳናይ እንቀራለንና እንጠንቀቅ።» ለሚለው የአምላካዊ ቃል ምክር ቀጣዩን ምሳሌ አስረግጠው ተናገሩ:-

ኃይሌ ገብረ ሥላሴና ቀነኒሳ ሲሮጡ ደጋፊ እንዳላቸው ሁሉ ነቃፊም አላቸው። ደጋፊ እንዲህ ይል ይሆናል:- «ኃይሌ በርታ! ጥሩ እንደተለመደው በዚህ በባዕድ ምድር የሐገራችንን ባንዲራ አውለብልብ።» ነቃፊዎች ደግሞ፣ «ኃይሌ ሁልጊዜ እያሸነፍክ ለመደነቅ ዘንድሮስ አትችልም። ፖል ቴርጋት ከኋላህ አለ።» ኃይሌ በዚህ ጊዜ ቆም ብሎ ለደጋፊው፣ «በደንብ እየጮሃችሁ ሞራል ስጡኝ፤» ለነቃፊውም፣ «ዛሬ እንደተለመደው አሸንፌ አሳያችኋለሁ» ቢል እስከአሁን ፖል ቴርጋት ሮጦ ሄዶ ያሸንፈው ነበር። ነገር ግን በሩጫ ሜዳ ላይ ኃይሌም ሆነ ቀነኒሳ፣ ሌሎችም ቆመው የመልስ መልስ አይሰጡም። የመልስ መልስ ከፊት ይገኛልና ሁሉም ከፊታቸው በትልቅ ቴሌቪዥን ያለውን ሰዓት ያያሉ፣ አሸንፈው የአገራቸው ስም በዓለም ሁሉ ሲከበር ያያሉ፣ ጨርሰው ሲመለሱ በአገራቸው የሚጠብቃቸውን የክብር አቀባበል ያያሉ። ስለዚህም የመልስ መልስ ሳይሰጡ ይሮጣሉ፣ ያሸንፋሉም።

አዎ፣ የእግዚአብሔር ቃል በዕብ. 12:2 ላይ፣ «የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፣ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ።» አዎን፣ ወገኖቼ፣ ጌታችንን ተመልክተን የመልስ መልሱን አቁመን ለቁጣው ዕድልና ፈንታ እየሰጠን የሕይወታችንን ሩጫ በትዕግሥት ብንሮጥ እናሸንፋለን እንጂ አንሸነፍም፣ እንወርሳለን እንጂ አንወረስም፣ እንደምቃለን እንጂ አንደበዝዝም። አሜን።

ግጥምጥም:- የመልስ መልስ ሲሰጥ እግዚአብሔር ጊዜ አለው፣
እኔም ዝም ብዬ እስቲ እርሱኑ ልየው።

ዕብ. 12:1-3
ሮሜ 12:14-21

## ክፍል 9

## እግዚአብሔርን አምኖ ከሞት ስለ መዳን

# ሙሉ ወንጌልን እወዳለሁ

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።» (ዮሐ. 3፥16)

ሰባኪው፥ ወደ ውጪ የምትሄድ የጎረቤታቸው ልጅ የሽኝት ፕሮግራም ላይ ተገኝተው እንዲህ እያሉ መልእክታቸውን ማቅረብ ጀመሩ። «ዛሬ የተሰበሰብነው ለምስጋና ነው። ግን ለመሆኑ የምናመሰግነው ማንን ነው? የምናመሰግነውስ ለምንድን ነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጠን የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይኸውም በመዝሙረ ዳዊት (136)፥1 ላይ፥ «እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ቸር ነውና፥ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።» ይላል። እንግዲህ የምናመሰግነው እግዚአብሔርን የምናመሰግንበትም ዋና ምክንያት የዘላለም ምሕረትን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰጠንና ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት ስላሻገረን ነው። ዛሬ ይህንን ወንጌል ለምታችሁ ያላመናችሁ ከሆነ የዘላለም ሞት ይጠብቃችኋልና አምልጡ፥ ወደ እግዚአብሔር ኑ። ልብ በሉ፥ እያልኩ ያለሁት ወደዚህኛው ቤተ ክርስቲያን ወይም ወደዚያኛው ቤተ ክርስቲያን ሂዱ ሳይሆን፥ ስለ እኛ ራሱን አሳልፎ በመስቀል ሞት ወደ ሰጠውና ሞትንም አሸንፎ በእግዚአብሔር ቀኝ ወዳለው ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። በእርሱ ታመኑ ነው እያልኩ ያለሁት። ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ መልካም ቢሆንም፥ የሄደ ሁሉ ከሞት የሚድነው እውነት፥ መንገድና ሕይወት ብቻ በሆነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የታመነ እንደሆነ ነው። በዚህ ሙሉ ወንጌል ማመን የምትፈልጉ ብትኖሩ መጨረሻ ላይ አነጋግሩኝ። ብለው ጨረሱ።

በዚህ መልእክታቸው ጉባኤው ሁሉ ተነካ። በተለይም አንድ ሽማግሌ ሰባኪው በመጨረሻ አነጋግሩኝ ባሉት መሠረት ወደ ኋላ ቀርተው እንዲህ አሏቸው። ዛሬ ገና እውነተኛውን ወንጌል ሰማሁ፥ ሳትጨምር ሳትቀንስ በመስበክህ ደስ ብሎኛል። እኔ ሙሉ ወንጌልን እወዳለሁ። ከሁሉ በላይ የመጣህበትን ድርጅት ወይም ቤተ ክርስቲያን ሳትሰብክ ሙሉ ወንጌል በመስበክህ ደስ ብሎኛል። ከዘላለም ሞት የምድንበትን መንገድ ስፈላልግ ነበር ዘመኔን ሁሉ የኖርኩት። ዛሬ እግዚአብሔር በቃሉ ለልቤ ስለተናገረኝና መዳን በክርስቶስ ብቻ መሆኑም ስለገባኝ አሁን ጌታን አምናለሁና ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ?» ብለው ጠየቁ።

አዎ፥ ወገኖቼ ሆይ፥ ከዘላለም ሞት መዳን የሚቻለው በእግዚአብሔር ነው። መዳን በሌላ በማንም የለም። ከሰማይ በታች እንድንበትና እናመልጥበት ዘንድ የተሰጠን ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና። አሁኑኑ በእርሱ እንመን። እኛም አገልጋዮች እግዚአብሔር በከፈተልን አጋጣሚ ሁሉ የሰውን ልብ የሚለውጠውንና ከሞትም መዳን በጌታ ብቻ መሆኑን የሚናገረውን ሙሉውን ወንጌል እንድናስተምር አምላክ በጥበቡ ያግዘን። አሜን!

ግጥምጥም፦ ሞትን ያሸነፈ ኢየሱስ እያለህ፥
ከሚሞት አምላክ ጋር ለምን ትሞታለህ?

ሮሜ 1፥16
ቲቶ 2፥11–14

# የአስቄዋ ልጆች

የቃል ጥናት ጥቅስ፤ «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።» (ራእይ. 3፡20)

በጣም ድምጻቸውን ከፍ የሚያደርጉት በተለይ «እምነት የግል ነው» የሚለው አሳብ ላይ ነው። ምክንያቱም በቦታው የተሰበሰቡት አብዛኛው ወጣቶች በክርስቲያን ቤተሰቦቻቸው እምነትና ስም እንጂ በግላቸው ጌታን ተቀብለውና አምነው በእርግጥ አምላክ መሆኑን ተረድተው አልነበረም የሚመላለሱትና የሚያገለግሉት። ስለዚህም ሰባኪው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ጮኹ። «ወጣቶች በክርስቶስ መታመን የግል ነው። እንዳችሁም በቤተሰቦቻችሁ እምነት ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደማትገቡ ዛሬ እወቁ። የእናንተ የራሳችሁ ስም በሕይወት መጽሐፍ ላይ መጻፍ አለበት። ይህ የሚሆነው ደግሞ ጌታ ጌታ መሆኑን አውቃችሁ ስትታመኑትና እንደ ቃሉ በጽድቅ ኑሮ ስትመላለሱ ነው። ያን ጊዜ እግዚአብሔር ይከብራል፤ እናንተም ትድናላችሁ፤ ሰይጣንም ያፍራል። ይህም ደግሞ በምድር ሁሉ የታወቀ ይሆናል። ይህ ካልሆነ ግን የአስቄዋ ልጆች ዕጣ ይደርስባችኋል።» ብለው ስለ አስቄዋ ልጆች ከሐዋ. 19፡11–20 ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል ተናገሩ። «በጊዜው በእርሱ በታመነው ባሪያው በጳውሎስ እግዚአብሔር ድንቅ ተአምር ያደርግ ነበር። ከአካሉ ጨርቅ ወስደው በድውዮች ላይ ሲያደርጉ በሽታ ይለቅቃቸው፥ መናፍስትም ይወጡ ነበርና ይህንን የሰሙ የካህናት አለቃ የሆነው የአስቄዋ ሰባት ልጆች በከተማው ሰይጣን የያዘው ሰው ፊለጉና ጨርቅ በራሱ ላይ አድርገው፥ ‹ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ እናዛችኋለን፥ ውጡ› ይሉ ነበር። በዚህ ጊዜ አጋንንቱ ኢየሱስን በግላቸው ጌታቸው መሆኑን እንዳላመኑ አውቆ እንዲህ አላቸው፥ ‹ኢየሱስንስ አውቀዋለሁ፥ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ። አሁን እኔ ግራ የገባኝ እናንተ እነማን ናችሁ?› ብሎ ዘሎ ተነሣና ልብሳቸውን ቀድዶ፥ አካላቸውንም አቆሳስሎ ሰባቱንም ከእናታቸው ሆድ እንደወጡ እራቁታቸውን አድርጎ አባረራቸው።» አሉና፥ አሁንም ጮክ ብለው፥ «የእነዚህ ልጆች አባት የካህናት አለቃ ነው፤ ያ ግን ለእነርሱ አልጠቀማቸውም። ስለዚህ በግላችሁ ጌታን የእኔ ጌታ ነው ብላችሁ ካላመናችሁ በስተቀር የቅዱሳን ቤተሰቦቻችሁ እምነትና በአፋችሁ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ነኝ ማለታችሁ ብቻውን በቂ አይደለም።»

አዎ፥ ክርስትና ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ደግሞ በመስቀል ላይ ደሙን ያፈሰሰው ለእያንዳንዳችን ነው። ስለሆነም የእያንዳንዳችንን ልብ ከፍተን በእውነት ይህንን ጌታ ዛሬውኑ ልናምንና የዘላለምን ሕይወት ልንቀበል ያስፈልጋል። ይህንን ወንጌል አምነንና የጌታንም ድምጽ ሰምተን ራሳችንን ለጌታ እንድናስረክብ እርሱ ይርዳን።

ማጥምጥም:- እምነት የግል ነው፥ አገር የጋራ ነው፤
ምክንያትህን ትተህ ሕይወትህን ስጠው።

2ኛ ጢሞ. 3፡14–15
ቆላ. 3፡17

# ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት

ሰባኪው፣ «በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ብዙ ነገሮች የመጀመሪያውን የልባችንን ዙፋን መውሰድ ቢፈልጉም መስጠት ግን የለብንም:: በሁሉም አቅጣጫ በሕይወታችን ቅድሚያው ቦታ ለክርስቶስ ብቻ ሊሆን ይገባል:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ግን በዚህች የክርስቲያን ደሴት እየተባለች በምትጠራው አገራችን የተገላቢጦሽ ሆኖ እናገኘዋለን:: እንደ ስማችን አይደለም ሥራችን፣ ቅድሚያ የምንሰጠው ለጣዖት፣ ለአድባር፣ ለጠንቋይ፣ በአጠቃላይ ለራሳችን ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህ ደግሞ ኪሳራን ያመጣል:: ለፈጣሪ ቅድሚያ መስጠት ሲገባን፣ ለፈጠረው ነገር ቅድሚያ ከሰጠን እግዚአብሔር በእኛ ላይ እንዲበቀል በቅንዓት እያነሣሣን ነው:: ስለዚህ በቀረልን ዘመን መገዛት፣ ክብር፣ ውዳሴ፣ ገናንት፣ አድናቆት ሁሉ ከዘላለም ሞት ላዳነን ጌታ ብቻ ልንሰጥና ልናሰጥ ይገባል» ለሚለው ጥልቅ ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

«ሁለት ጓደኞች በአንደኛው ቤት ምሳ እየበሉ ሳለ አንደኛው ጓደኛ ሁሌም የጓደኛውን ቤት ይወደዋልና ዙሪያ ገባውን እየተመለከተ ማድነቅ ጀመረ:: የተሰቀሉትን የአገር ባህል ዕቃዎችና ሥዕሎች ጭምር ሲመለከት በድንገት በተለምዶ «ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርት ጋር የመጨረሻውን ራት ሲበላ» ብለን የምንጠራውን ሥዕል ተመለከተና ማድነቅ ጀመረ::<አቤት፣ ደቀ መዛሙርቱ እንዴት ደስ ይላሉ! አቤት፣ በራሳቸው ላይ ያለው ክብ ነገር እንዴት ደስ ይላል! አቤት፣ የሚጠጡበት ዋንጫ እንዴት ደስ ይላል! አቤት፣ የለበሱት ልብስና የእግር መታጠቢያው ሳህን እንዴት ደስ ይላል!> እያለ ማድነቁን በቀጠለ ጊዜ፣ ጓደኛው እስከአሁን ያነሣቸው ወይም የሚደነቅባቸው በሙሉ ለዘላለም ሕይወት ማግኘት አንዳቸውም ዋጋ አለመክፈላቸውን ያለማወቁ አሳዝኖት እንዲህ አለው፡ «እባክህ ዙሪያ ዙሪያውን ከመሄድ የሰው ልጆችን ሁሉ ለማዳን በቀራኒዮ መስቀል ላይ ሞትን ድል ያደረገውን ጌታ ኢየሱስን ብቻ ተመልከት፣ እርሱንም አድንቅ» አለው::

አዎ፣ ዛሬስ እኛ ቅድሚያ ሰጥተን የምናደንቃቸውና የምንገዛላቸው ነገሮች ምን ይሆኑ? ቅድሚያውን ቦታና ክብር ለጌታ ስጡ:: እርሱ ብቻ የበላይ ነው:: በእውነት ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ተብላ የምትጠራው ከዝሙቷ፣ ከጥንቆላዋ፣ ከአስማቷ እና ከጣዖቷ ፈጽሞ ርቃ ሁሉን ቻይ እግዚአብሔርን የበላይ ስታደርግ ብቻ ነው::

የቃል ጥናት ጥቅስ፡ «...እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፣ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም::» (ኢሳ. 44፡6)

ግጥምጥም፡- ስሜና ሥራዬ አብሮ እንዲሄድልኝ፣

በቃኝ ከአምላክ ሌላ ንስሐ ገባሁኝ::

ኢሳ. 4:4-17
ሮሜ 13:7

# የተበላ ዕቁብ!

ሰባኪው፣ «በዚህ ዓለም ላይ ከፍቅር ሁሉ በላይ የሆነው ፍቅር ራስን ለሌሎች አሳልፎ መስጠት ነው:: በዮሐ. 15:13 ላይ እንደተጻፈው፣ «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም»:: ይላል:: ሰው ለወዳጁ ገንዘቡን፣ ቤቱን፣ ያለውን ጥሪት ሁሉ አሟጦ ሊሰጥ ይችላል፤ ነፍሱን ግን መስጠት አይችልም:: ይህንን ማድረግ የቻለው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: ስለዚህ እኛም ነፍሳችንን የምንሰጠው ለእርሱ ብቻ ሊሆን ይገባል:: እርሱ በሞቱ ሞታችንን ሽሮ፣ በቅዱስ ደሙ የገዛን ነውና ልብ በሉ:: ነፍሳችሁን ለሌላ ብትሰጡ አታገኟትም:: ለእርሱ ብትሰጡ ግን በመንግሥተ ሰማይ እንደገና ታገኟታላችሁ:: ጌታ ብቻ ነው ዋጋ ከፍሎ፣ ያውም ለመስቀል ሞት ራሱን ሰጥቶ፣ ሞቶ እኛን ከዘላለም ሞት ያዳነን» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

«በዶሮ እርባታ የሚተዳደር አንድ ገበሬ ነበር:: አንድ ቀን ባልታወቀ ምክንያት የእሳት ቃጠሎ ተነሥቶ የእርባታውን መጋዘን ከነዶሮዎቹ አቃጠለው:: ገበሬው የአካባቢውን ሕዝብ እርዳታ ጠይቆ እስከሚያስገነዝብ ድረስ ጊዜ የማይሰጠው እሳት አብዛኛውን ክፍል አወደመው:: ሕዝቡም ተሰብስቦ እሳቱ ከተባዛ በኋላ ፍርስራሹን ሲያነሣሡ የተወሰኑ ጫጩቶች ከአንድ የከሰለ ነገር ውስጥ ውልቅ ውልቅ እያሉ እየበረሩ ወጡ:: ለካስ እናታቸው በእሳት ተቃጥላ፣ እነርሱን ግን ከክንፎቿ በታች ሸሽጋቸው ኖሯል::»

አዎ፣ ይህ ለእኛ ትልቅ ምሳሌ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶ እኛ ዳንን ማለት የምንችለው ግን ይህ ያደረገው ሥራ ገብቶንና ማርከን ስናምን ነውና ሰዎች ስለ ክርስቶስ ሲነገራቸው እንደተበላ ዕቁብ ችላ ይሉታል:: እርሱ ግን ሕይወት ነው:: ለዚህም ራሱ ቸሩ እግዚአብሔር ይርዳን:: አሜን!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐ. 3:16)::

ዮሐ. 4:14፤ 5:24

ግጥምጥም:- በእኔ ፈንታ ሞቶ ከሞት ያዳነኝን፣
ኢየሱስን አምኜ መንግሥቱን ወረስኩኝ::

# ዕዳ መቶ ሲሞላ አይከብድም

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን::» (ኤፌ. 1:5)

ሰባኪው:- «እግዚአብሔር ስለ ደኅንነታችን ያደረገው ነገር በዚህ ጥቅስ ላይ ግልጽ ብሎ እንደተቀመጠው ቢገባን ጌታን ቆመን ሳይሆን ተንበርክክን ብናመሰግነው ባልበዛበት ነበር:: እስቲ ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ላንሣ:-

1. እኛ ከዘላለም ሞት የዳንነው በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ እንጂ በራሳችን አልነበረም:: እኛም «ዕዳ መቶ ሲሞላ አይከብድም» እንደተባለው፣ ኃጢአት በኃጢአት ላይ እየጨመርን ወደ ሞት እየገሰገስን ነበር:: ጌታ ግን እንደ በጎ ፈቃዱ ደረሰልን:: ለዚህ ነው፣ "ጌታን ተቀበልኩ ከማለት ይልቅ ጌታ ተቀበለኝ" ማለት ያለብን::
2. እኛ ከዘላለም ሞት የዳንነው በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ነው:: ቃሉም እንደሚል፣ ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም» (ኤፌ. 2:8):: ጌታ በመስቀል ላይ ሆኖ ተፈጸመ ብሎ በፈጸመው የደኅንነት ሥራ ታምነን መዳን ያስፈልጋል::
3. እኛ ከዘላለም ሞት የዳንነው አስቀድሞ በተወሰነው የእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት ነው:: «ዓለም ሳይፈጠር፣ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን::» (ኤፌ. 1:4):: እንደዚህ አድርጎ ያዳነንን ጌታ ሁልጊዜ ልናመሰግነው ይገባል:: ለሚለው ግሩም መሠረታዊ የደኅንነት ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ አቀረቡ::

ጊዜው የስቅለት ማታ ነው:: ወንጌላዊው ከቤተሰቡ ጋር ስለበደሉና ኃጢአቱ የሞተለትን ጌታ ኢየሱስን ለማመስገን የኢየሱስን ፊልም ከፍቶ ያያል:: በፊልሙ መጀመሪያ ላይ እየተደሰቱ የቆዩት ቤተሰብ ሁሉ መጨረሻ ላይ ያለ ኃጢአቱ ሥቃይና ሞት የደረሰበትን ጌታ በመስቀል ላይ በምስማር ሲቸነከር እያዩ ፊታቸው በኀዘን ተመታ:: በተለይም የ8 ዓመቷ ልጅ ማልቀስ ጀመረች:: ፊልሙ አልቆ ከተፈጸመ በኋላ አባቷን እንዲህ ስትል ጠየቀች፣ «አባዬ ለምንድን ነው ይሄ ጥሩው ኢየሱስ የሞተው?» አባት፣ «ለእኛ ብሎ ነው የሞተው» አላት:: ቀጠለችና፣ «መቼ ነው የሞተው?» «ከዛሬ 2 ሺህ ዓመት በፊት::» በዚህ ጊዜ የ8 ዓመቷ ልጅ እየገረማት፣ «ታዲያ፣ እንዴት ለእኛ ነው የሞተው ትለኛለህ? እኔ ገና 8 ዓመቴ ነው፣ የት ያውቀኛል?» ብላው አረፈች::

አዎ፣ ዓለም ሳይፈጠር እኛም ሳንፈጠር አወቀን፣ ከአእምሮአችን በላይ በሆነው ዕቅዱም ለዘላለም አዳነን:: በእውነት የአምላካችን የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን:: አሜን!

ግጥምጥም:- ከቶ እንደ ምን ብዬ እንዴት ላመስግንህ፣
ከሞት ስላዳንከኝ በበጎ ፈቃድህ::

| |
|---|
| ዘፍጥ. 3:15 |
| ኤፌ. 2:14-15 |

# ጊወርጊስ ወይስ ዮሐንስ?

የቃል ጥናት ጥቅስ፡- «ኢየሱስም እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።» (ዮሐ. 14፡6)

የስዕለት ልጅ ከመሆኗ የተነሣ አባትና እናቷ ሁልጊዜ የሚመለከቷት በጉጉት፥ የሚከታተሏትም በጥንቃቄና በስስት ነው። ለዚህም ነው ካደገችም በኋላ እንኳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስትገባ አድርሶ የሚመልስ ጠባቂ (body guard) የቀጠሩላት። እርሱም ሁልጊዜ የ15 ዓመቷን ልጅ እንደ መዋዕለ ሕጻናት ተማሪዎች ትምህርት ቤት አድርሶ መመለስን ተያያዘው። አንድ ቀን ግን ይህ ጠባቂ ታመመና ሥራውን አጓደለ። ቤተሰቦቿም ከጎረቤት ካሉት የዕድሜና የጾታ ተመሳሳይነት ካላቸው ተማሪዎች ጋር ትምህርት ቤት እንድትሄድ መክረው እያይዘው ሸኟት። ለካ የጎረቤት ተማሪዎች አማኞች ነበሩና ከትምህርት ቤት እንደ ወጡ ጸሎት ቤት ይዘዋት ሄዱ። እዚያም ሄዳ ወንጌልን ሰማች። ከሰማይ ሰማያት የወረደው፥ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በቀራኒዮ መስቀል ላይ የሞተውና ሞትንም አሸንፎ የተነሣው እርሱ ክርስቶስ ኢየሱስ ላመኑበት ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንደሚሰጥ፥ ነፍስንም ከገሃነመ እሳት እንደሚያድን ሰማች። በመጨረሻም ሰባኪው ጥሪ ሲያደርግ ተነሣችና አመነች (ጌታን ተቀበለች)። ደስም ብሏት ወደ ቤቷ ስትሄድ መሽቶ ደረሰች። ቤተሰቦቿም ተጨንቀው ነበርና እጅግ ተቆጥተው ጠበቋት። ስትመጣም በቁጣ፥ «የት፥ ሄደሽ ነው ያመሸሽው?» አሏት። እርሷም፥ «ቤተ ክርስቲያን» አለች። ጎሽ አሉና፥ «ለመሆኑ የትኛው ቤተ ክርስቲያን ነው የሄድሽው? ጊዮርጊስ ወይስ ዮሐንስ?» እርሷም፥ «አይ፥ አማኞች ቤተ ክርስቲያን ነው» አለች። በዚህ ጊዜ በጣም ደንግጠው፥ «ጴንጤዎች ጋ?» በማለት ጮኸው አማተቡና፥ «ለመሆኑ፥ ምን አድርገሽ መጣሽ ታዲያ?» አሏት። እርሷም፥ «ኢየሱስን ተቀብዬ መጣሁ» አለች። በዚህ ጊዜ በቁጣ ቃል ድምጻቸውን ከፍ አድርገው፥ «በይ ቀጥ ብለሽ ሂጂና ይህንን የተቀበልሺውን ኢየሱስ መልሽላቸው» አሏት። እርሷም፥ በነጋታው ለመመለስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደችና ለወንጌላዊው፥ «ትናንትና የሰጠኸኝ ኢየሱስን ቤተሰቦቼ ስላልተቀበሉት እንድታወጣና እንድትወስደው ነው የመጣሁት» አለችው። ወንጌላዊውም እንባ በዓይኖቹ እየተንቆረዘዘ የልጅቷን የዋህነት አይቶ እንዲህ አላት። «ኢየሱስን ለማስወጣት ነው የመጣሽው?» አላት። «አዎን» አለች። «እንደዚህ ከሆነ ነፍስሽ ይወጣል፥ ኢየሱስ ነፍስ ነው» አላት። እርሷም ደነገጠችና ሁሉንም ትታ ወደ ቤተሰቦቿ ተመለሰች። እነርሱም፥ «አስወጥተሽ መጣሽ ወይ?» ባሏት ጊዜ፥ «አላስወጣሁም። ምክንያቱም ወንጌላዊው ኢየሱስን ካስወጣሽ ነፍስሽም አብሮ ይወጣል» አለኝ አለቻቸው። በዚህ ጊዜ አባትና እናት የስዕለት ልጃቸውን ሞት በመፍራት አሰብ አደረጉና፥ «ነፍስሽስ ከሚወጣ አጥብቀሽ ያዢው» አሏት።

አዎ፥ ወገኖቼ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት እንጂ ሃይማኖት አይደለም። ነፍሳችንን ከገሃነም እሳት የሚያድንና ከሞት ወደ ሕይወት የሚያሸጋግር ብቸኛ አምላክ ነውና በእርሱ ታማምነን አሁኑኑ ከዘላለም ሞት እንድንድን ጌታ ይርዳን። አሜን!

ግጥምጥም፡- ነፍሴን ለማዳን ነፍሱን የገደለው፥
የናዝሬቱ ኢየሱስ እርሱ ጌታዬ ነው።

የሐዋ. 4፡12
ዮሐ. 5፡24
ዕብ. 10፡39

# የፋሲካው በግ

ሕዝቡ በየዓመቱ የሚደረገውን የፋሲካ የሳምንት ኮንፍራንስ በጣም ስለሚወደውና ስለሚባረክበትም ትልቁ ቤተ ክርስቲያን የሞላው ከተቀጠረው የኮንፍራንስ ሰዓት በፊት ነው። ሰባኪውም ለዚህ ግጥም ብሎ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ለሚጠባበቀው ሕዝብ እንዲህ እያሉ መልእክታቸውን ቀጠሉ። «ዛሬ ስለ እውነተኛውና ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት የሰውን ልጅ ለማሻገር ራሱን ለመታረድ አሳልፎ ስለ ሰጠው የፋሲካው በግ (ኢየሱስ ክርስቶስ) እናገራለሁ። እርሱ ብቻውን የሰውን ልጆች ኃጢአት ተሸክሞ፥ ብቻውን ሞቶ፥ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። በእርሱ ብቻ ያመነ ይድናል። ሥጋውም ቢሞት እንኳ ነፍሱ ወደ ገነት ትገባለች። ምክንያቱም የፋሲካው በግ እርሱ ደሙን አፍስሶ ኃጢአታችንን በደሙ አንጽቶልናልና። ዛሬ የሰው ልጆች ሆይ፥ በማን ነው የታመናችሁት? ራሳቸውን ስለ እናንተ ብለው ባልሰጡና ባልሞቱላችሁ አማልእክትና ሰማዕታት ለምን ትታመናላችሁ? የነፍሳችሁ ጠበቃ ክርስቶስ ነውና በእርሱ ብቻ ታመኑ። ከፋሲካው በግ ውጭ አዳኝ የለምና ሰይጣን እንዳያታልላችሁ።» ለሚለው ስብከታቸው የሚከተለውን ምሳሌ አስረግጠው ተናገሩ።

በፋሲካ ሰሞን አንድ ሰው ከቤተሰቡ ጋር በዓሉን በደስታና በፌሽታ ለመዋል እንደተለመደው በግ ለመግዛት ወደ ገበያ ሄዱ። መርጠው አማርጠው በዓይናቸው የሞላውን በሚችሉት ዋጋ ገዙና በረጅም ገመድ የበጉን አንገት አስረው እየሳቡ በደስታ ወደ ቤታቸው መሄድ ጀመሩ። በመንገድም ሆነው፥ «አሁን ቤቴ ሄጄ ይህንን በግ አርድና ከቤተሰቤ ጋር ስፈልግ ጥብስ፥ ስፈልግ ዱለት፥ ስፈልግ ቀይ ወጥ እያማረጥኩኝ በመብላት ስደሰት እውላለሁ» እያሉ ይመኛሉ። በየመንገዱ የሚያልፈው ሰው ሁሉ ግን ሰውዬውን እያዩ ይስቃሉ፥ ግማሹም ይገረማል። ግማሹም፥ «ሰውዬው ምን ነካው? ይላል። ለካስ እንደዚያ ለብዙ ነገር የተመኙት ከቤተሰቤ ጋር ስደሰትበት እውላለሁ ያሉት የፋሲካው በግ ከገመዱ ሾልኮ አምልጧል። ለካ ሰውዬው ባዶ ገመድ ነበር የሚጎትቱት– ባዶ ገመድና ባዶ ምኞት።

እኛስ አንባቢ ሆይ፥ የታመነውንና እውነተኛውን የፋሲካ በግ ክርስቶስን ይዘናል ወይስ እንደ ሰውዬው ባዶ እምነት ይሆን ይዘን የምንገሰግሰው? ከሰማይ ሰማያት የወረደውን፥ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ላይ ስለ ሁላችን ኃጢአት የሞተውንና የተነሣውን የፋሲካውን በግ ታምነን ለመንግሥቱ እንድንበቃ መንፈስ ቅዱስ ይርዳን። አሜን።

ግጥምጥም:- ከሞት የሚያድንህ ክርስቶስ ብቻ ነው፥
ከእርሱ ሌላ ሁሉም የከንቱ ከንቱ ነው።

| |
|---|
| ዮሐ. 4:25–26<br>ቲቶ 2:11–13 |

# ይሉኝታ ይገድላል

የቃል ጥናት ጥቅስ፦ «ኑኃሚን ከአርስቀም ጋር... ምራትዋ ሩት ተመለሱ።» (ሩት 1:22)

ሰባኪው፣ «ዛሬ የምሰብከው በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ስለ መመለስ ነው። ወገኖች፣ እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው። በቃሉም፣ «ብትመለሱ እመልሳችኋለሁ።» ብሏልና ዛሬ ያለን ክርስቲያኖች በተለያየ ኃጢአት ውስጥ የወደቅን ብንኖር እንመለስ። ሕዝቡ ሁሉ የሚያውቀው ኃጢአት የሠራን በሕዝቡ ፊት ንስሐ ገብተን እንመለስ። እግዚአብሔርና እኛ ብቻ የምናውቀው ኃጢአት የሠራን በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ ገብተን እንመለስ። ይሉኝታና ፍርሃት ሸብቦን ንስሐ ሳንገባ ከነኃጢአታችን ወደ ሲዖል አንውረድ። ከቃሉ እንደምናየው ኑኃሚን ባዶዋን ተመለሰች ጌታ ግን ባዶነቷን ሞላ። በምሬት ነው የተመለሰችው፣ ጌታ ግን ምሬቷን ወደ ደስታ ለወጠ። በመመለስ ትርፍ እንጂ ኪሳራ የለም። ከኑኃሚን መመለስ ውስጥ ሩት ተገኘች። በመመለስ እራሳችንንና ሌሎችንም እናድናለንና ዛሬውኑ እንመለስ። ንስሐ ገብቶ በመመለስ የሚገኘውን ትርፍ ደስታ፣ እረፍትና ሕይወት ሰይጣን ስለሚያውቀው እንዲህ እያለ ያጨልምብናል፣ <ጓደኞችህ ምን ይሉሃል? ሕዝቡ ሁሉ ያጠቋቁምብሃል፣ እግዚአብሔርም አይቀበልህም።> ነገር ግን እግዚአብሔር መሐሪ፣ ሕዝቡም ተቀባይ ነውና ተመለሱ። አለበለዚያ ከነኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ።» ለሚለው አስደናቂና ግሩም ለሆነ ስብከታቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

ሁለቱም በአንድ የመዘምራን ቡድን ውስጥ የሚያገለግሉ ወጣቶች ነበሩ። በአገልግሎታቸው ብቻ ሳይሆን በሥራቸውም በአንድ ላይ ሆነው በንግድ ሥራ ነበር የሚተዳደሩት። ጊዜ እየረዘመ ሲሄድ ቤተ ክርስቲያን መሄዱንም ሆነ ማገልገሉን እየቀነሱ መጥተው መጨረሻ ላይ ከነአካቴው ሁሉንም ትተው ንግዳቸውን ብቻ ቀጠሉ። ያለ እግዚአብሔር በራስ ጥረት መሳካት አይገጥምምና ንግዱንም ከሠሩ። ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ብዙ ጣሩ፣ ግን አልሆነም። በመጨረሻም አንደኛ ው የእግዚአብሔር መንፈስ ወቅሶት መመለስ እንዳለበት ወስኖ ለጓደኛ ው ቢነግረው እምቢ አለ። «የድሮ የመዘምራን ቡድን ጓደኞቻችን ምን ይሉናል? የሕዝቡ ዓይን ይበላናል። ይህንን ሁሉ አድርገን እግዚአብሔር የሚቀበለን አይመስለኝም።» ጓደኛው ግን ይህን ሁሉ ሳይሰማ ወደ አምላኩ ተመልሶ ንስሐ ገባና ከነፍሱ አዳኝ ጋር ታረቀ።

በዚህ ሁኔታ ደስ ብሎት እየተመላለሰ እያለ አንድ ቀን እንደዚሁ የንግድ ዕቃ ለማምጣት ከጓደኛው ጋር ወደ ክፍለ ሀገር ሲሄድ የመኪና አደጋ ይደርስና ሁለቱም ሳይመለሱ እስከወዲያኛው አንቀላፉ::

አዎ፣ ወገኖቼ፣ ከዚህ ታሪካዊ ምሳሌ የምንረዳው የመዳን ቀንና ንስሐ የምግባት ቀን ዛሬ ነው፣ ነገ ምን እንደምንሆን አናውቅም:: ንስሐ አድራሻን ይቀይራል:: አንዱ ወጣት ንስሐ ገብቶ ወደ መንግሥተ ሰማይ ሲሄድ፣ ሌላው ደግሞ ይሉኝታን ፈርቶ ንስሐ ሳይገባ ወደ ገሃነም እሳት ሄዷል:: ይሉኝታ ይገድላልና ዛሬውኑ ንስሐ እንድንገባ ጌታ ይደግፈን::

**ግጥምጥም፦ ንስሐ ገብቼ ልታረቅ ከአምላኬ፣**

**ምሥጢሩ ገብቶኛል እንዲህ መታወኬ::**

| ምሳ. 28:13 |
|---|
| ኢሳ. 1:18-20 |

## ክፍል 10

## ለእግዚአብሔር ስለ መስጠትና መስጠት

# ኮርሽምሽምሽምሽም

የቃል ጥናት ጥቅስ፣ «...በዚህ ቸር ሥራ ደግሞ ትረፉ።» (2ኛ ቆሮ. 8:7)።

ሰባኪው፡ አጽንኦት ሰጥተው የሚናገሩት ስለ መስጠት ነበር። «ዛሬ ለመስጠት አቅም ያጣነው መጀመሪያ ቀድመን ራሳችንን፣ ትዳራችንን፣ ሥራችንንና በአጠቃላይ ሕይወታችንን ስላልሰጠን ነው። የተሰጠ ሰው ለመስጠት ጉልበት ይኖረዋል። የምንሰጠው ደግሞ ሲተርፈን ብቻ። ከጉድለታችንም ነው። ልክ፣ «የድህነታቸው ጥልቅነት የልግስነታቸውን ባለጠግነት አብዝቶአል።» (2ኛ ቆሮ. 8:2) እንደተባለው የእግዚአብሔር ቃል ልናደርግ ይገባል ፕሮግራም ውስጥ የገባን ነገር ወይም አንድ ነገር ሊፈጸምበት የታቀደን ገንዘብ መስጠት ከባድ ቢመስልም ግን እግዚአብሔር የበለጠ አዘጋጅቷልና ፕሮግራሙን እንኳ ትተን ለእርሱ ልንሰጠው ይገባል።» እያሉ ለተሰበሰበው ሕዝብ መናገራቸውን ይህንን ምሳሌ አስከትለው ቀጠሉ።

አንድ ቀን ከቤተሰብ ጋር ቤት አብረን ጊዜ እያሳለፍን ሳለ የመጨረሻዋ ልጅ አንድ ሥራ ሠርታ፣ «ምን ላርግልሽ?» ስላት፣ ከረሜላ ገዝተህ ካልሸለምከኝ ስላለች ሁለት ደስታ ከረሜላ ገዛሁላትና መብላት ጀመረች። አንደኛውን ጨርሳ ሁለተኛውን አፍዋ ውስጥ እንዳስገባች የልጄ አፍ ውስጥ የገባውን ከረሜላ መብላት ደስ ስላለኝ እንድትሰጠኝ ጠየቅኋት፣ እርሷም ግንባሯን እያኮሳተረች እንደማትሰጠኝ መለሰችልኝ። እኔም እንድትሰጠኝ፣ «እኔ አይደለሁ እንዴ የሰጠሁሽ? እባክሽ ስጭኝ» ብዬ መለመኔን ቀጠልኩ። በዚህ መሃል አንድ ድምጽ ከአፏ ውስጥ ሰማሁ። ለካ ከረሜላውን ኩርሽምሽምሽምሽም አድርጋ እንደማትሰጠኝ የመጨረሻውን መርዶ እያሰማችኝ ነበር።»

አዎ፣ ፕሮግራም ውስጥ የገባውን ነገር ለአባቷ ለመስጠት ይህች ልጅ የተቸገረችው ስስት እና ራስን አለመስጠት ስላጠቃትና የነገሩም ጣፋጭነት ስለአጓጓት ነው። እኛስ እንደዚህች ሕፃን ነን ወይስ አባቴ የበለጠ የጣፈጠ ነገር ይሰጠኛል ብለን በመጨከን የምንሰጥ ነን? ስስታችንን እና ስሜታችንን ገትተን ፕሮግራም ውስጥ ያስገባነውንም ነገር እንኳ ለጠየቀን አምላካችን በደስታ እንድንሰጥ እግዚአብሔር ይርዳን።

ግጥምጥም፡- ለቸሩ እግዚአብሔር ሥራ ሠርቼ፣
እኖራለሁ እንጂ ሳልኖር ተከፍቼ።

2ኛ ቆሮ. 8:8-11
ፊልጵ. 4:19

# ኢንቨስተሩ!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ለዘሪ ዘርን ለመብላትም እንጀራን በብዙ የሚሰጥ እርሱም የምትዘሩትን ዘር ይሰጣችኋል ያበረክትላችሁማል፣ የጽድቃችሁንም ፍሬ ያሳድጋል» (2ኛ ቆሮ. 9:10)

«ሁሉ ከእርሱ ነው:: ከእኛ የሆነ ምን አለ? ወደዚህስ ዓለም ስንመጣ ምን ይዘን መጥተናልና» በዕለቱ የሰባኪው ዋና የመልእክታቸው ክፍል ነበር:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ባዘጋጀችው ዓመታዊ የገንዘብ ማሰባሰቢያ /Fundraising/ ፕሮግራም ላይ ሰባኪው ቀጠሉ:: «ሁሉን የሰጠን እግዚአብሔር ነው:: ሁሉንም መልሰን ለእርሱ ልንሰጠው ይገባል:: ለጌታ ሰጥቶ የከሰረ የለምና የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር፣ የቄሳርን ለቄሳር ስጡ:: የእግዚአብሔርን ገንዘብ አትስረቁ፤ አስራቱን፣ መባውን፣ በኩራቱን ወደ ጎተራው አስገቡ:: አምላኬ እንዲሰጠን፣ እንዲባርከን ጸልየን ከሰጠን በኋላ ለእርሱ ለመስጠት አንሰስት:: ጋብቻችን ሁሉ የእግዚአብሔር ነው:: በዚህ ምድር ላይ ሀብታም የለም፣ ባለአደራ እንጂ! ሀብቱማ የእግዚአብሔር ነው:: እኛ ሰዎች የባለሀብቱ ሀብት ጠባቂና አንቀሳቃሽ ባለአደራዎች ነን:: ባለሀብቱም (ኢንቨስተሩ) እግዚአብሔር አባታችን ነውና ለአባታችን የአባታችንን ሀብት ለመስጠት መሳሳት የአደራነትን አገልግሎት አለመወጣት ነው::» ሰባኪው ይህንን ትምህርታቸውን ለማጠናከር ቀጣዩን ምሳሌ አስከትለው ተናገሩ::

«አንዲት ልጅ ትምህርቷን ከጨረሰች በኋላ ሥራ ፈትታ ለብዙ ዓመታት ቁጭ አለች:: ወጣ ብላ ሥራ ለመፈለግ በጣም ፈሪና ዐይናፋር ከመሆኗ የተነሣ፣ ይህንን ችግሯን የተረዱ ቤተሰቦቿ የወደፊት ሕይወቷ ስለአሳሰባቸው አባቷ ከአንድ የግል ድርጅት ጋር ተነጋገሩና ሥራ አስገቧት:: ይኸውም በየወሩ ደመወዟን እርሳቸው ሊከፍሉ፣ ድርጅቱ ሠራተኛ እንደሚፈልግ ገልጾ በማስታወቂያ በማወዳደር እንዲቀጥራትና በየወሩም የአባቷን ገንዘብ እየተቀበለ እንዲከፍላት እርሷ ሳታውቅ በምሥጢር ይህንን ተነጋገሩ:: እናም አባቷ የሥራ ማስታወቂያ እንደወጣና እዚያም ድርጅት ሄዳ እንድትወዳደር ጠቆሟትና ሄዳ ማመልከቻዋን አስገባች:: እንዳለፈችም ይነገራትና ሥራዋን ትጀምራለች:: ሥራ በማግኘትዋም ከቤተሰቧ ጋር ደስታዋን ትገልጻለች:: የሁለት ወራት ደመወዟን ከበላችም በኋላ አባቷ

በሦስተኛው ወር፣ "እስከ አሁን አየሁሽ፣ ምንም የደስ ደስ አልጋበዝሽኝም፣ እስቲ በዚህኛው ወር ደመወዝሽ ወጣ እንበልና ጋብዥኝ ሲሏት፣ እንዲህ ብላ መለሰች፡፡ "አይ አባዬ፣ ለጸጉሬ ቅባት፣ ለልብሴና ለሌሎችም ጉጣጉጦች አይበቃኝምና ልጋብዝህ አልችልም፡፡ ይቅርታ!" ብላቸው አረፈች፡፡ በገዛ ገንዘባቸው፡፡»

አዎ፣ ወገኖቼ እግዚአብሔር እንዲሁ ነው፡፡ ይሰጠንና፣ "እስቲ ከአሥሩ አንዱን እጅ ለእኔ ስጠኝ" ሲለን፣ አይ፣ ለዚህ ለዚያ ለማይበቃኝ አልሰጥህም ብለን በገዛ ገንዘቡ እንከለክለዋለን፡፡ ምንኛ ምስኪኖች ነን፡፡ እስቲ ተመልከቱ የዚህች ልጅ አባት ለምትሠራበት ድርጅት ገንዘብ መስጠት ቢያቆሙ ምን ይውጣት ይሆን? እኛም እንደዚሁ ነን፡፡ ወገኖቼ፣ ለዘሪ ዘርን የሚሰጠው እግዚአብሔር እንደዘራ እንዲሰጥ ነውና ለእርሱ ካለን ሁሉ በላይ በደስታ እንድንሰጠው ጌታ ይርዳን፡፡ አሜን፡፡

2ኛ ቆሮ. 9:6፣7
ሮሜ 11:36
ሚልክ. 3:7-12

ግጥምጥም፡- የእኛ ለእኛ እኮ ነው ብለን የምንለው፣
ምን ኖሮን ነው ከቶ ይዘን የመጣነው፡፡

# የፈረንጅ ላም

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ስጡ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፣ የተጨቈነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል::» (ሉቃስ 6:38)

መጋቢው፣ «የክርስቲያኖች ኑሮ የማያድገው ለምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ ስለማንሰጥ ነው የሚል ነው:: ዛሬ ኑሮአችን የተትረፈረፈ መሆን ሲገባው፣ የቤተሰባችንና የአገራችን ኑሮ ከእጅ ወደአፍ ሆኖ ያለው ለምንድን ነው? ብንል ስለማንሰጥ ነው:: ወገኖች፣ ለእግዚአብሔር የተሰሰተ ኃብት በረከት የለውምና እንስጥ፣ ለድሆች እናካፍል:: ለድሃ የሚያካፍል አይደኸይም፣ ለድሃ የሚሰጥ ለእግዚአብሔር እንዳበደረ ነው የሚቆጠረውና ራሳችን ለራሳችን ብቻ እናከማች:: ከእግዚአብሔር ጋር እናከማች:: ብልጥ ልጅ በአባቱ ኪስ ያጠራቅማል እንደሚባለው፣ በአባታችን በእግዚአብሔር ጎተራ እናጠራቅም:: ያን ጊዜ በረከት ይኖራል::» ለሚለው ትምህርታቸው መጋቢው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ::

አንድ ልጅ የፈረንጅ ላም በ5 ሺህ ብር ለመግዛት አስቦ 50 ሳንቲም በአባቱ ኪስ ማስቀመጥ ጀመረ:: የሚያገኘውን ሳንቲም ሁሉ እያስቀመጠ በስድስት ወር ውስጥ አምስት ብር ደረሰ:: ታዲያ በዚህ ሁሉ በነጋ በጠባው ልጁ አባቱን፣ «የፈረንጅ ላም ለመግዛት ብሬ አልሞላም ወይ?» እያለ ይጨቀጭቃል:: ዓመት ሲሆነው ብሩ እንኳን 5 ሺህ ብር ሊሞላ አሥርም ብር አልሞላም:: ይህ ትንሽ ልጅ ግን የፈረንጅ ላም የመግዛት ጉጉቱ ስለጨመረ በነጋ በጠባው አባቱን፣ «አልሞላም ወይ?» እያለ መነዝዙን ቀጠለ:: በዚህ ጊዜ አባቱ የልጁ ንዝነዛ ስለበዛበት፣ ከዚህ ሁሉ እኔ ብገዛለት ይሻላል ብሎ 5 ሺህ ብሩን አውጥቶ ገዛለት::

አዎ፣ የእኛ አይሞላምና ከእግዚአብሔር ጋር እናጠራቅም:: ያን ጊዜ እግዚአብሔር የልባችንን መሻት ይሞላል:: የተትረፈረፈውንና የተጨቆነውን መስፈሪያ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም እናየዋለን:: ቤታችንም አገራችንም ተባርካ ለሌላውም ዓለም የምንተርፍ ሰዎች እንሆናለን::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ለድሃ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል::» (ምሳሌ 19:17)

ግጥምጥም:- እንዴ ምክንያት ለካ ለዚህ ድህነቴ፣
አለመስጠት ኖሯል ወይኔ ስስቴ::

(2ኛ ቆሮ. 8:1-2)

# ዲቪ ቢወጣልኝ!

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እርስዋም ለባሪያህ ወንድ ልጅ ብትሰጠኝ ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ:: ምላጭም በራሱ ላይ አይደርስም ብላ ስዕለት ተሳለች::»

ቄሱ በቤተ ክርስቲያናቸው ሰንበትን ምክንያት አድርገው ለተሰበሰቡት ምእመናን ሁሉ የዕለቱን መልእክታቸውን ለማቅረብ ዝግጅታቸውን አጠናቅቀው የፊት ወንበር ይዘዋል:: የዕለቱም ፕሮግራም መሪ የያዛቸውን ከመልእክት በፊት ያሉትን የዕለቱን ፕሮግራሞች ካጠናቀቀ በኋላ ቄሱን ጋበዛቸው፣ እርሳቸውም መልእክታቸውን ቀጠሉ:: «በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ከጊዜው ጋር በብዙ ሁኔታቸው እየተለዋወጥን ጌታን እያሳዘንን ያለን ይመስለኛል:: ይህንን ልል የቻልኩበት አንዱ ምክንያት ለምሳሌ፣ በአፋችን ለእግዚአብሔር የተናገርነውን ስዕለት በተግባር ስንፈጽም ብዙ አይታይም:: ወገኖች፣ ባንሳል ይሻለናል:: ስንቶች እንሆን፣ "ሥራ ብትሰጠኝ የመጀመሪያ ደመወዜን ላንተ እሰጣለሁ::" ብለን ሥራ አግኝተን ያልነውን ለመፈጸም የተቸገርን:: ስንቶች እንሆን፣ "ማኅጸኔን ብትከፍትልኝ የምወልደውን ልጅ ለአንተ አገልጋይ እንዲሆን እሰጣለሁ::" ብለን እንደ ሐና ነገር ግን ልጆቻችንን እንደሚገባ ካለማሳደጋችን የተነሣ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆናቸው ቀርቶ የሰይጣን አገልጋዮች የሆኑብን:: ስንቶች እንሆን፣ "ዲቪ ቢወጣልኝ / ወይም በተለያየ ዕድል /ከአገር ውጭ ብወጣና በዚያም የመኖሪያ ፈቃድ አግኝቼ ብኖር በኢትዮጵያ አገሬ አንድ ቤተ ክርስቲያን እተክላለሁ የተወሰኑ አገልጋዮችንም ቀለብ እችላለሁ::" ብለን ከተጸለየልንና ሁሉም ተሳክቶ ከተመቻቸን በኋላ እንደዚህ ብለን ስዕለት መሳላችንን ጭራሽ የምንረሳና ትዝ የማይለን:: ቅዱሳን እግዚአብሔር ከልጆቹ አፍ የወጣውን ስዕለት ይፈልገዋልና ፈጽሞ እግዚአብሔርን ማታለል አይቻልም::» ለሚለው መልእክታቸው ይህንን ቀጣይ ምሳሌ ተጠቀሙ::

አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ስዕለት ተሳለ፣ «እግዚአብሔር ሆይ፣ ከዚህ በኋላ ከማገኘው ሁሉ ግማሹን ለአንተ እሰጣለሁ:: 100 ብር ብትሰጠኝ ግማሹ ያንተ ነው፣ አምሰት መቶ ባገኝ ግማሹ ያንተ ነው፤ 1 ሺህ ባገኝ ግማሹ ያንተ ነው::» መቼም እግዚአብሔር ቸር ነውና ይህን ስዕለት ተስሎ ጨርሶ በመንገድ ላይ ሲሄድ ጭር ያለ አካባቢ 50 ብር ያገኛል፤ በዚህ ጊዜ የተሳለው ትዝ አለውና እንዲህ አለ፣ «እግዚአብሔር እንደማልሰጥህ አውቀህ የራስህን ድርሻ ወስደህ የእኔን ስለላክልኝ አመሰግንሃለሁ::»

አዎ፣ የብዙዎቻችን ስዕለት ውጤቱ ከዚህ ሰውዬ ብዙ የተሻለ አይመስልምና ለጌታ የገባነውን ቃል ኪዳን /ስዕለት/ እንፈጽም:: አንዳንዶች፣ «ስዕለት የብሉይ ኪዳን ነው እንጂ የአዲስ ኪዳን አይደለም:: ክርስቲያን አይሳልም» ይላሉ:: ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት አይደለምና እንመለስ:: የተሳልነውንም እንድንፈጽም ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ከአፌ የወጣውን የከንፈሬን ፍሬ::
ስዕለቴን ልፈጽም ሳያልፍ ዘመኔ::

መሳ. 11:29-40
ዘፍጥ. 20:20-22
መክ. 5:4-5

# ኑሮ ጨምሯል

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እናንተ፣ ይህ ሕዝብ ሁሉ፣ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ::» (ሚልክ. 3:9)

ሰባኪው፣ ለእግዚአብሔር ላለመስጠት ብዙ ምክንያቶችንና ዘዴዎችን መጥቀስ የለብንም:: የእግዚአብሔር ቃል የሚለው ስጡ ነው:: ለእኔ ስጥታችሁ ፈትኑኝ ነው ያለው:: እኛ ሳንሰጥ እግዚአብሔርን፣ "ለምን በረከት አጣሁ? ሲሳይ ከድንኳኔ ጠፋ?» ብለን መፈታተንና ማማረር የለብንም:: ሰይጣንና የአሁኑ ዘመን ለእግዚአብሔር እንድንሰጥ አይፈቅዱም:: የሰይጣንንም ምክንያት ማስተናገድ የለብንም:: ሰይጣን ኑሮ ጨምሯልና ዛሬ ተወው ነገ ትሰጣለህ እያለ ያታልለናል:: ሁሉም ነገር ቢጨምር የሚያኖረን የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ጨመረ መርሳት የለብንም:: ቃሉ እንደሚል፣ «መኖሪያህ እግዚአብሔር ነው፤ የዘላለምም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው::» ይህንን መታመን አለብን:: ለእግዚአብሔር ላለመስጠት ድህነት እንኳ ምክንያት አይሆንም:: ያቺ ድሃ መበለት ሁለት ዲናር ሰጥታ ከሃብታሞቹ በላይ አብልጣ ሰጠች ተብሎላታልና:: ሦስት ነገሮችን እግዚአብሔር በደስታ እንድንሰጠው ይጠብቅብናል:- ራሳችንን፣ ያለንን እና ጊዜያችንን:: ለእግዚአብሔር ላለመስጠት ምንም ዓይነት ምክንያት ተቀባይነት አይኖረውም::» ለሚለው ጠንካራ አሳዳጊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከታችው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ::

«ሦስት አማኞች አንድ ቀን ለእግዚአብሔር ገንዘባቸውን እንዴት እንደሚሰጡ ቁጭ ብለው መነጋገር ጀመሩ:: አንደኛው ተነሣና፣ "እኔ ገንዘቤን ለእግዚአብሔር የምሰጠው ደመወዜን እንደተቀበልኩ አንድ ቦታ እቆምና በዙሪያዬ ሰፊ ክብ መሥመር አከባለሁ:: ገንዘቤን ወደ ላይ እወረውራለሁ:: ከክቡ ውስጥ የወደቀው የእኔ ነው፤ ከክቡ ውጭ የወደቀው የእግዚአብሔር ነው" አለ:: ሁለተኛው አማኝ ተነሣና፣ "እኔ ግን ውጭ የወደቀው ለእኔ ነው፣ ውስጥ የገባው የእግዚአብሔር ነው አለ:: ሦስተኛው አማኝ ደግሞ እንዲህ አለ፣ "የእኔ ከእናንተ ትንሽ ይለያል:: በዙሪያዬ የክብ መሥመር አላከብም:: ነገር ግን ያለኝን ገንዘብ በሙሉ ወደ ላይ እወረውራለሁ:: የእኔ የሆነው ወደ እኔ ይመለሳል፤ እግዚአብሔር ደግሞ የራሱን በዚያው ወስዶ ያስቀራል" አለ::

እነዚህ ሰዎች ጤንነት፣ ሰላምና ችሎታ ችሮ ገንዘብ ለሰጣቸው አምላክ ለመስጠት ሁሉም ፈቃደኞች አይደሉም:: እንዲያውም ልብንና ኩላሊትን የሚያውቀውንና የሚመረምረውን ጌታ ሲያታልሉት ይታያሉ:: እኛስ? ለእግዚአብሔር መስጠት ትርፍ እንጂ ኪሣራ የለውም፣ ማግኘት እንጂ ማጣት የለውም:: ይህንን ተረድተን ያለ ምንም ስበካ በደስታ እንድንሰጠው ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- መቀበል በመስጠት መሆኑን አውቃለሁ፣
ለሚሰጠኝ ጌታ መልሼ እሰጣለሁ::

| |
|---|
| ማር. 12:42 |
| ሉቃ. 6:38 |

# እንደ አንበጣዎች ነን

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እኛም በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን...» (ዘኁል. 13:33)

ሰባኪው:- «እኛ ክርስቲያኖች በእውነትና በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት በመታመን በንጹሕ ሕሊና መሄድ እንጂ ላይሆን በሚችል ሥጋ በፈጠረው ስሜታዊ ግምት መሄድ የለብንም:: በእግዚአብሔር እውነት ላይ እንጂ በሥጋዊነት ግምታዊ አስተሳሰብ ላይ መታመስ የለብንም:: ለምሳሌ፣ ሁለት ሰዎች በግቢው ውስጥ ወይም በመንገድ ዳር ቆመው እያወሩ በሩቅ ብናይ ሥጋችን የሚለን፣ "ስለ አንተ ነው የሚያወሩት፣ እያሙህ ወይም እያሴሩብህ ነው::" ይህ የተዛባ ግምት ነው:: ቤተ ክርስቲያን ስለ አንድ ነገር በጉባኤ ላይ ማስታወቂያ ስትናገር፣ "እኔን ለመንካት ወይም ከአገልግሎትና ከቤተ ክርስቲያን ለማባረር ነው" ማለት የለብንም:: በእርግጥ የሠራነው ኃጢአት ካለና መንፈስ ቅዱስ ከወቀሰን ንስሐ እንግባ:: አለበለዚያ በአገር ሰላም ራሳችንን አናስጨንቅ:: እስራኤላውያን፣ "በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን" አሉ:: የተሳሳተ ግምት የተሳሳተ አመለካከትን ይወልዳል:: እነርሱ በእግዚአብሔር ክብር የተፈጠሩ ሰዎች ናቸው እንጂ አንበጣዎች አይደሉም:: ስለዚህም ተጐዱ፣ በአፋቸው በምድረ በዳ እንሞታለን እንዳሉት እንደ አንበጣ በየበረሃው ሞተው ቀሩ:: የተሳሳተ ግምት ይጐዳል::» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

በማገለግልበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አዲስ የተጠመቁ 40 አማኞች የጌታን እራት እንዲወስዱ የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት እያስፈጸምኩ ነው:: ሁሉም አማኞች በአንድ እጃቸው ደሙን የሚወክለውን ወይኑን ይዘዋል:: በሌላ እጃቸው ደግሞ ሥጋውን የሚወክለውን ኅብስቱን ይዘዋል:: እኔም ሳይገባቸው እንዳይወስዱ የሚናዘዙት ኃጢአት ካለም እንዲናዘዙ በጸሎት ሆነን እያስተማርኩ ነው:: በዓይኔ ቀና ብዬ ሁሉንም ስመለከት አስገራሚ ነገር አየሁ:: እንደዚያ ቀን አደብ ገዝታ የማታውቀው የአምስት ዓመቷ ትንሿ ልጄ ከተጠማቂዎቹ በስተመጨረሻ ላይ እጆቿን አጣምራ በሥነ ሥርዓት ቁጭ ብላ አየኋት:: በመጨረሻም፣ ሁሉም የጌታን እራት የሚወስዱበት ጊዜው ደረሰና በአንድ ላይ እንዲወስዱ አዘዝኩኝ፣ ሁሉም ወሰዱ:: አመስግነን ከጨረስኩ በኋላ ያቺ በሥነ ሥርዓት ተቀምጣ የነበረችው ልጄ

ከመቀመጫዋ ተነሥታ ፊቷን አኰሳትራ ወደ እኔ መጣችና፣ «አባዬ፣ ኩኪሱ እኔ ጋ ሳይደርስ ለምን አለቀ?» ብላ አለቀሰች።

አዎ፣ ወገኖቼ፣ ይህች ልጅ የጌታን ራት እንደ ሠርግ ኩኪስ በመቁጠር በተሳሳተ ግምት ተጐዳች። በከንቱ እምባዋን አፈሰሰች። እርሷ የገመተችው፣ "አባቴ የብስኩቱ አዳይ ነው፣ እኔም የእርሱ ልጅ ነኝ፣ እንደ ፈለግሁ እጠግባለሁ" ብላ ነበር። ነገር ግን አልሆነም። በእኛም ሕይወት እንዲሁ ነው። አባቴ እግዚአብሔር ነው፤ እኔም ልጁ ነኝ ብለን ያልሆነ ግምት ገምተን ነገር ግን ሳይሆን ቀርቶ የተጐዳን እንኖር ይሆን? እግዚአብሔር ከገመትነውና ከምናስበው በላይ ማድረግ የሚችል ነውና ትክክል ካልሆነ ሥጋዊ ግምታችን ወጥተን እምነታችን በእርሱ የእውነት ተስፋና ቃሉ ላይ ብቻ እንዲመሠረት ጌታ ይርዳን። አሜን።

ግጥምጥም፡- ያልሆነውን ግምት በሥጋ እየገመትኩ፣
ጌታ በሌለበት በምድረ በዳ አለቅኩ።

| |
|---|
| ዘኁል. 14:36-38 |
| ፊልጵ. 2:3 |

# ችግሬ ክሶኝ ተከሰከሰ!

የቃል ጥናት ጥቅስ- «ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።» (ዮሐ. 14:14)

ሰባኪው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲህ እያሉ ያስተምራሉ። «ወገኖቼ፣ እምነት የሌለው ሰው ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርንም እራሱንም ደስ ማሰኘትና ከሚመጣው ቁጣ ማምለጥ አይችልም። የክርስትና ሕይወት የተመሠረተው በእምነት ላይ ነው። ምንም ከባድና አስቸጋሪ ነገር በሕይወታችን ይግጠመን በእግዚአብሔር ታምነን ለእርሱ ካስረከብነው እንደ ቃሉ ይፈታዋል፣ ያስተካክለዋል። ለእርሱ የሚሳነው ነገር የለም። የእኛን እምነት የሚፈታተኑ ጉዳዮች እንኳን ቢኖሩ ለእግዚአብሔር ምኑም አይደሉምና ለእርሱ እናሳይ። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ያለጥርጣሬ በእርሱ ሁሉን ቻይነት የሚታመን ልብ ነው።» ለዚህም ግሩም የሆነ ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተናገሩ።

«አንድ መጋቢ በስብከት ተራው ቆሞ ስለ እምነት እንዲህ እያለ ይሰብካል። "የሰናፍንጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ተነቅለህ ወደ ባሕር ሂድ ብትሉት ይሆናል።" በዚህ ጊዜ በጉባኤው መካከል ቁጭ ብለው ይሰሙ የነበሩ አንዲት አሮጊት፣ "ይህ ማለት ካመንኩ በእኔ የሰናፍንጭ መሬት ላይ ያለው ትልቅ ቋጥኝ/ተራራ ድንጋይ/ ይናዳል ማለት ነው" ብለው አመኑ። ስብከቱም እንዳበቃ ወደ ኋላ ቀሩና መጋቢውን አግኝተው፣ "ዛሬ እግዚአብሔር የተናገረው እኔን ነው። ስለ እምነት ቅድም ስትሰብክ ትልቁ ተራራ ይናዳል ብለሃል። እኔም አምናለሁ። አንተም ጸልይልኝ። በተለይ የሰናፍጭ መሬቴ ላይ ያለው ተራራ እንዲናድ" ቢሉት። "አይ፣ እኔ ግን የሰበኩት እርሱን ሳይሆን፣ በሕይወታችን ላይ ያሉ የተለያዩ ተራራዎችን ነው" ብሎ መንፈሳዊ ቢያደርግባቸውም፣ "እኔ አምናለሁ፣ የእኔን የሰናፍጭ መሬት ተራራ ነው ጌታ ያለው" አሉት። መጋቢውም፣ "እንደ እምነትዎ ያድርግልዎት" ብሎ ሸኛቸው። እርሳቸውም በእምነት ጸሎታቸውን ቀጠሉ። ጌታም ጸሎታቸውን ሰማ። የአውራ ጎዳና መንገድ ሥራ ትልቅ መንገድ ለአገሪቱ ሲሠራ መንገዱ የሚያልፈው በሴትየዋ የሰናፍጭ መሬት አካባቢ በመሆኑ፣ ባለሙያዎቹ ያ ትልቅ ቋጥኝ ድንጋይ ተከስክሶ ለመንገድ ሥራቸው

እንደሚሆን አሰቡና ሴትዮዋን ጠይቀው ገዝተው በዶዘር በማንሣት የሰናፍጭ መሬቱን የተስተካከለ ሜዳ አደረጉት:: በዚህ ጊዜ ሴትየዋ እግዚአብሔር የየዋህነት የእምነት ጸሎታቸውን እንደ መለሰ ስላዩ እንዲህ አሉ፣ "እስከ ዛሬ ብዙ ሰናፍጭ እንዳለ መሬት የተዋጋኝ ችግሬ ክሶኝ ተከሰከሰ፤ አሜን::"»

በእርግጥ ለሚታመኑበት አምላክ እንዲህ ያደርጋል:: ዛሬም ያለ ጥርጣሬና ማመንታት ነገራችንን ሁሉ ለጌታ ብንሰጠው ያስቸገረንን ችግር አስቸግሮ መልሶ እኛን እንዲጠቅመን ወይም ለዘላለም ከነመታሰቢያው እንዲወገድ ያደርገዋል:: እምነት ውኃን ይከፍላል፣ በውኃ ላይ ያስኬዳል:: ጥርጣሬ ግን ያሰምጣል:: በጥርጣሬ ተሞልተን በዚህ ዓለም ሰምጠን እንዳንቀር እግዚአብሔር እምነትን ያብዛልን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ተራራን የሚንድ ሰጥቶህ ጌታ እምነት፣
የትኛው ተራራ ሊቆም በአንተ ፊት::

| |
|---|
| ዘፍጥ. 18:14 |
| ዘካር. 4:7 |

## እናቴ ጆሮዬን በላችው

ሰባኪው፣ «ዛሬ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ በራሳችን ድካም፣ ጥረትና ጥበብ ነገሮችን ለማሳካት ወይ የምንፈልገውን ለማግኘት እንደማንችል ከሕይወቴ ምሳሌ ጋር እያዛመድኩ እነግራችኋለሁ:: የእግዚአብሔር የአምላካችን ቃል እንደሚል፣ 'ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የበላ ተድላንስ የቀመሰ ማን ነው?' ይላልና:: ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንም ነገር ሊሆን አይችልም፣ የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ምንም ሊያግደው አይችልም:: አንዳንድ ጊዜ የምንፈልገውን ነገር ለማግኘት እንድንችል በራሳችን ጥረት እንድንሄድ ሰይጣን ያታልለናል:: ግን የጌታ እጅ ከሌለበት አይሆንም:: ከሆነም በጌታ ቸርነትና ፈቃድ እንጂ የተጠቀምነው ጎዳና ሰምሮ ወይም የግል ጥረታችን ታክሎበት አይደለም::»

«ትዝ ይለኛል አባቴ የነገረኝ፣ እናቴ በሕፃንነቴ እንዴት ጆሮዬን እንደ በላች:: የእኔ ታላላቆች ሦስቱም በተከታታይ ስለ ሞቱ ልጅ አልባ መሆኑ ያሳሰበው አባቴ ወደ ጠንቋይ ቤት ሄደና ጠየቀ:: ጠንቋዩም፣ 'የሞቱት ወንዶች ናቸውና ቀጥሎ የሚወለደው ልጅ ወንድ ከሆነ እንደ ተወለደ ወዲያው ሰው ባልተጠቀመበት በስለታም ምላጭ የግራ ጆሮውን ጫፍ እናቱ ሳታይ ቁረጥና በእንጀራ ጠቅልለህ ለእናቱ አብላት:: መዋጥዋን ካረጋገጥህ በኋላ «ልጅሽን በላሽው» በላት:: ያኔ በጣም ስለምትደነግጥ እነዚያን ሦስቱን ወንዶች ልጆች የገደለው በሽታ በምትደነግጥ ጊዜ ወጥቶ ይሄዳል' ይለዋል:: ልጅ ለማግኘት የፈለገውም አባቴ ልክ ጠንቋዩ እንዳለው ከእናቴ ማኅፀን እንደ ወጣሁ ወዲያው ጆሮዬን ቆርጦ ለእናቴ አበላት:: ይህ ብቻም አይደለም የሞቱት ታላላቆቼ ወንዶች ስለነበሩ ይህኛው ልጃችንም ወንድ መሆኑን ካወቀ ይገድልብናል ብለው በሴት ስም እየጠሩ፣ የሴት ልብስ እያለበሱ 10 ዓመት እስኪሆነኝ ድረስ ለመደበቅ ሞከሩ፤ እና እኔም ያደግኩት በዚህ ዘዴ መሰላቸው:: ነገር ግን ካደግኩ በኋላ አባቴም በእኔ ምስክርነት ወንጌልን ሰምቶ ጌታን ተቀብሎ ከተረዳ በኋላ የሚያድን፣ ልጅን የሚሰጥና የሚያሳድግ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑ ገብቶት እንደሆነ ለመፈተን፣ የመጀመሪያ ልጄን ስወልድ፣ 'ጆሮውን ልቁረጥ ወይ?' ብዬ ስጠይቀው፣ 'ተወኝ ልጄ፣ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ እንጂ የእኛ አይደለምና:: ባለፈው

በአንተ በልጄ ላይ ያደረግኩትን እግዚአብሔር ይቅር ብሎ የዘላለም ሕይወት ስለሰጠኝ አመሰግነዋለሁ» አለኝ።»

አዎ፣ ልጅን በመስጠት የሚባርክና የሚያሳድግ፣ መካኒቱን የልጆች እናት የሚያደርግ፣ የልብን ፈቃድና ፍላጎት እንደ በጎ ፈቃዱ የሚያደርግ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነውና በእርሱ እንታመን። ጠንቋይ ለራሱ አያውቅምና ገንዘባችንን አንጨርስ፤ እግዚአብሔር ብቻ አዋቂ ነው። እርሱ ይሰጣል፣ እርሱም ያሳድጋል። አሜን።

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና!» (ፊልጵ. 2:13)

ግጥምጥም:- ልቡና ልግዛና ላቁም ኪሣራዬን፣
ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንም ነገር ላይሆን።

1ኛ. ዮሐ. 5:14

# መርፌ የራሱን ቀዳዳ አይሰፋም

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ::» (ፊልጵ. 4:6)::

ሰባኪው: «ብዙ ጊዜ በሕይወታችን የምንጨነቀው እምነት ሲጠፋ፣ በእግዚአብሔር ላይ ያለን መታመን ሲወሰድ ነውና ለዛሬም ለነገም ለዘላለም በእግዚአብሔር ልንታመን ያስፈልጋል:: እግዚአብሔር የዓለም ሁሉ ገገር፣ ሁሉን የሚችልና የሚያኖር አምላክ ነው:: አንዳንድ ጊዜማ በሕይወታችን የሚገርም ነገር ይሆናል:: ለሌሎች ጭንቀት መፍትሔና መንገድ አሳይተን በሁሉን ቻይ ጌታ እንዲታመኑና እንዲያርፉ መክረን እነርሱንም አሳርፈን እኛ ግን አሁንም እንጨነቃለን:: መርፌ የራሱን ቀዳዳ አይሰፋም እንደሚባለው ሲሆንብን እናያለን:: ወገኖቼ፣ እግዚአብሔር እናንተ ከወፎች ትበልጣላችሁ፣ ወፎችን የሚመግብ አምላክ በአምሳሉ የተፈጠርነውን እኛንማ እንዴታ:: ስለዚህ በነገር ሁሉ አትጨነቁ፣ ይልቁንም ጭንቀታችሁን አስታውቁ ይላል ጌታ::» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ::

አንድ ጓደኛዬ አንድ ቀን እንዲህ ብሎ አጫወተኝ: ብዙ ሠራተኞች እኛ ቤት ገብተው ትምህርት አግኝተው ይሄዳሉ:: የአሁኗ ሠራተኛ ግን የተገላቢጦሽ እግዚአብሔር ትምህርት በእርሷ አስተማረን:: ይገርምሃል በምንም ነገር ሁልጊዜ ስትጨነቅ አላያትም፣ ነገረ ሥራዋ ይገርማል:: ባለፈው ሰሞን ያደረገችውን ሁለት ነገር ብቻ ልንገርህ:: ሁላችንም ማታ ቁጭ ብለን ሳለ፣ "እሜቴ፣ ጤፍ አልቋል" ብላ አስታወቀች:: ባለቤቴም፣ "ምን ነው ወሩ ሳይሞላ?" ትላታለች:: "ምን ይደረግ እሜቴ፣ እንደ ጉድ ተበላ" አትላት መሰለህ ዘና ብላ:: ምን ይኸ ብቻ እንደገና በነጋታው ደግሞ እንደዚሁ ሳትጨነቅ ዘና ብላ መጥታ፣ "እሜቴ፣ ቂቤም አልቋል" ትላታለች:: ያለወትሮው ሁሉም ወሩ ሳይደርስ በማለቁ የተገረመችው ባለቤቴ፣ "ዘንድሮስ ጉድ መጣ ትላታለች":: "ምን ይደረግ እሜቴ፣ እንደ ጉድ ተጠጣ" ብላት አረፈችው:: በሁኔታው ተገርመን፣ "ይህች ልጅ ሳትጨነቅ ከማስታወቅ ሌላ ምን ድርሻ ነበረባት:: እኛ እንጨነቅ እንጂ እርሷ ለምን ትጨነቃለች? ከእኛ ጋር ካልተስማማች ከፈለገች ከእኛ ወጥታ ሌላ ቤት ትገባለች፣ ምን ያስጨንቃታል አልንና እኛም እኮ ምን ያስጨንቀናል? አስታውቁኝ ላለው ጌታችን እናስታውቃለን" ብለን ትምህርት ተማርንባት እልሃለሁ::

እውነት ነው፣ የእኛ ኃላፊነት በነገር ሁሉ ያለማቋረምረም ከምስጋና ጋር ማስታወቅ ነው:: ጌታ ችግራችንን ሊያስቸግር፣ ጨለማችንን ሊያበራ፣ ተራራችንን ሊንድና ምድረ በዳችንን ሊያለመልም ታማኝ ነው:: አሜን::

ግጥምጥም:- ጭንቀቴን ሊያስወግድ ካለ ፈጣሪዬ፣
የውስጤን ነግሬው ልረፍ በጌታዬ::

ማቴ. 6:24-34
መዝ. 62:2

# ክፍል 11

## ስለ እግዚአብሔር ቃል

## የጨረቃ ቤት

ሰባኪው ለቤተ ክርስቲያናቸው ምእመናን ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን የዕለቱን መልእክት እንዲህ እያሉ ማስተማር ጀመሩ:: «ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላክ ከሰው ልጆች ጋር የሚገናኘው በቃሉ ነው፤ ቃሉን ሲናገር ያሳርፋል፣ ይመራል፣ ይመልሳል፣ ይፈውሳል:: ቃሉ ኃይል አለው:: ስለዚህ እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምሯችሁን ሰዎች በጥንቃቄ በማስተዋል ስሙ፣ ሰምታችሁ የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ሰሚዎች ብቻ አትሁኑ፣ ወይም በአንድ ጆሮ ሰምታችሁ በሌላኛው ጆሮአችሁ አታፍስሱ:: ደግሞ ልንገራችሁ ሰይጣን ዲያብሎስ የተዘራውን ዘር ለመልቀም ሁልጊዜ አይተኛምና ንቁ አስተውሉም:: የሰማነውን እውነተኛውን ቃል አጥፍቶ ያልሰማነውን ያሰማናልና ተጠንቀቁ::» በማለት በራሳቸው ቤት የገጠማቸውን ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ::

አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ:: ሁልጊዜ ማታ ማታ ከቤተሰቤ ጋር የቤተሰብ ጸሎት አድርገን ስለምንተኛ ቃሉን ከቤተሰቤ ጋር እንማር ነበር:: በዕለቱም፣ «ይህ ቤት የብርሃን ቤት ነው» በሚል ርእስ ቃሉን አስተምር ነበር:: ልጆቼም ባለቤቴም ሁሉም በደስታ ይሰሙ ነበር:: እኔም በዚህ ቤት ውስጥ የጨለማ ሥራ የሆኑትን ክፋትን፣ ተንኰልን፣ ምቀኝነትን፣ ስድብን፣ መራርነትን፣ ሐሜትን፣ ንዴትን፣ ቁጣን፣ ግብዝነትን ሁሉ አስወግደን ልንመላለስ ይገባል:: ምክንያቱም ይህ ቤት የብርሃን ቤት ነው እያልኩ ማስተማር ጀመርኩ:: ታዲያ በመካከል ሁሉን ስመለከት አንዷ ልጄ በሥጋዋ እንጂ በአሳቧ እዚያ እንዳልነበረች በሁኔታዋ ስለተረዳሁ ስሟን ጠቅሼ፣ «ይህ ቤት የምን ቤት ነው?» ብዬ ጠየቅኋት፣ እርሷም ከሄደችበት በአሳብ በመባነን በድንገት፣ «የጨረቃ ቤት ነው» አለችኝ:: በዚያን ሰሞን በአካባቢውና በቴሌቪዥን የሰማችው ይህ የጨረቃ ቤት ጉዳይ ትዝ ብሏት::

አንባቢ ሆይ፣ ሰይጣን ከእግዚአብሔር የሰማኸውን ቃል ወስዶ ከዓለም የሆነውን ያሰማሃልና አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ:: የእግዚአብሔር ቃል ሲነገር በሙሉ ልብ ሰምተን በሙሉ ልብ እንድንተገብር ጌታ ይርዳን ::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ::»

ግጥምጥም:- በቃሉ እንዳትኖር ወጥቷል የሚነጥቅ፣
ክርስቲያን ወገኔ አእምሮህን ጠብቅ::

ማቴ. 13:14
ኤፌ. 4:31

# የሌባ ዓይነ ደረቅ

ሰባኪው፣ «እግዚአብሔር ሊደርስብን ያለውን ነገር እንድንጠነቀቅ አስቀድሞ በቃሉ በባሪያዎቹ በኩል ይናገራል፤ ያንን ሰምቶና አስተውሎ እንደ ጌታ ፈቃድ ያልሆነውን መተው፣ የጌታን ፈቃድ ደግሞ መፈጸም መልካም ነው:: ቃሉም እንዲህ ይላል:: "አሁንም:- ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን በዚያም ዓመት እንኖራለን እንነግድማለን እናተርፍማለን የምትሉ እናንተ ተመልከቱ፣ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና::" (ያዕ. 4:13):: አዎ፣ ወገኖች፣ መሄድ፣ መነገድና ማትረፍ የሚቻለው ጌታ ሲፈቅድና ምሪትም ሲሰጥ ብቻ ነው:: በፈቃዳችን ፈቃዱን ጥለን ብንሄድ ግን በማትረፍ ፈንታ ኪሳራ፣ በዚያች ከተማ በመኖር ፈንታ ሞት ነው የሚጠብቀንና ፈቃዱን እንወቅ» ለሚለው መሠረታዊ የክርስትና ትምህርታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ::

የአንድ ሰውን ቤት በሌሊት እዘርፋለሁ ብሎ በር ሰብሮ ለመግባት የሞከረ አንድ ሌባ ነበረ:: ታዲያ የቤቱ ባለቤት ሁልጊዜ ቤቱን ነቅቶ የሚጠብቅ ነበርና በዚያ ሌሊት ሌባው በር ለመስበር ሲጎረጉር ሰምቶ ጦሩን ይዞ ከበሩ ሥር ሆኖ ይጠባበቅ ነበር:: ሌባውም ከብዙ ትግል በኋላ እንዳሰበው ለመፈጸም በሩን ሰብሮ እንደ ገባ ድንገት ሳያስበው የቤቱ ባለቤት በያዘው ጦር ሆዱን በኃይል ይወጋዋል:: በዚህ ጊዜ ሌባው ያሰበው ቀርቶ ያላሰበው ስለደረሰበት በጣም ተናድዶ ሆዱን በእጁ ይዞ ለባለቤቱ እንዲህ አለው፣ «በጦር የወጋኸኝ መስሎሃል እንጂ፣ አልወጋኸኝም» አለ:: የሌባ ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ እንደተባለው፤ በዚህ ጊዜ ባለቤቱ በደንብ እንደ ወጋው ያውቃልና እንዲህ ብሎ መለሰለት፣ «አሁን ሂድ፣ ውጤቱን በኋላ ታገኘዋለህ» አለው::

አንባቢ ሆይ፣ እግዚአብሔር በቃሉና በመንፈስ የሚመራንን ትተን በእኛ ፈቃድና ስሜት ብንጓዝ የከፋ ሁኔታ ይገጥመናልና እንመለስ:: ውጤቱም እንደዚህ ሌባ የኋላ የኋላ የሚያጠፋ ይሆናልና ለሥራችንም ሆነ ለትዳራችን፣ ለንግዳችንም ሆነ ለመኖሪያችን እንደ እግዚአብሔር አምላካችን ፈቃድና እንደ ቃሉ፣ እንደ መንፈስ ቅዱስም ምሪት እንድንኖር ቀሪ ዘመናችንን ጌታ ይባርክ:: አሜን::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል» (ያዕ. 4:15)

ግጥምጥም:- በፈቃዴ ሄጄ አልተሳካምና፣

ጌታ ያለው ይሁን ከእንግዲህ በኋላ::

ኤፌ. 5:17
የሐዋ. 4:19

# እኔም ዜሮ ነኝ!

አንድ ቀን ወደ ክፍለ ሀገር ለአገልግሎት እየሄድን ነበር፡፡ አውቶቡሱ ግጥም ብሎ ሞልቷል፡፡ ከአዲስ አበባ ከተማ የተወሰኑ ኪሎ ሜትሮች ከተጓዝን በኋላ ግማሹ ተረጋግቶ የሚሄድበትን ያስባል፣ ግማሹ ከጐኑ ካለው ሰው ጋር ያወራል፡፡ በዚህ መሐል ሾፌሩ ድምፁን ከፍ አድርገው ዘፈን ከፈቱ፡፡ የሚገርም ዘፈን ነበር! እንደዚህ ያለ ዘፈን ከዚህ ቀደም ሰምቼ አላውቅም፣ እስካሁንም ሌላ አልሰማሁም፡፡ እንደዚህ ይላል፣ «ይገርማል ዘንድሮ ይደንቃል ዘንድሮ፣ ሁሉም ዜሮ ዜሮ፣ ሁሉም ዜሮ ዜሮ»፡፡ በዚህ ጊዜ ከአጠገቤ የተቀመጡት አንድ ሰው ከረባታቸውን እየነካኩ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው፣ «ሾፌር የዘፈኑን ድምፅ ከፍ አድርገው፣ እኔም ዜሮ ነኝ» አሉ፡፡ ወዲያው የጌታ መንፈስ፣ «አንተ ግን ዜሮ አይደለህም» አለኝ፡፡

«አዎ፣ እኛ ክርስቲያኖች በእውነት ይህንን ከልባችን ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ሰማይና ምድርን የፈጠረ ጌታ በእኛ ውስጥ ሳይንቀን አድሯልና ራሳችንን ከሚጠፋው ዓለም ጋር እያወዳደርን መናቅ የለብንም፡፡ ምንም እንኳ ዛሬ ብዙ ሀብት፣ ገንዘብ፣ ጥሪት ወይም ስም፣ ዝናና ውበት የሌለን ብንመስልም፣ ከዚህ ሁሉ በላይ የሆነና የከበረ ጌታ ግን በእኛ ውስጥ ስላለ የከበርን ነንና ከሚጠፋው ባሻገር የማይጠፋውን እንመልከት፡፡ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሐዋርያት ጴጥሮስና ዮሐንስ ይህንን በሐዋ. *ሥራ* 3፡6-7 ሲያረጋግጡልን፣ "ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው፡፡ በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቁርጭምጭምቱ ጸና፣ ወደ ላይ ዘሎም ቆመ፡፡" አዎ፣ ለዚህ ሽባ ሰው ብርና ወርቅ ቢሰጡት ኖሮ ቁርጭምጭሚቱ ሊጸናና ሊፈወስ፣ ዘሎም ሊቆምና ሊመላለስ ባልቻለም ነበር፡፡ እንግዲህ በውስጣችን ያለው ኃይል ከብርና ከወርቅ፣ ከስምና ከዝና እጅግ የበለጠ ነውና ይልቅ በሙሉ ልብ ተነሥተን እንጠቀምበት፡፡ ክርስቶስ ያለው ሰው ጐደሎ ሳይሆን ሙሉ ነው፡፡ ዓለም እንደ ትንሽና ምንም እንደሌለው አድርጋ እንደምትንቀው ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ ነው፡፡»

*የቃል ጥናት ጥቅስ* «... ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፣ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፣ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ፡፡» (ኢሳ. 66፡2)፡፡

አዎ፣ ቅዱሳን ሆይ፣ በውስጣችን የእግዚአብሔር መንፈስ ስላለ እኛ ዜሮ አይደለንም፣ ወይም የቀን ጨለማ የወረሰን በባዶነት የተሞላን አይደለንም፡፡ በመሆኑም፣ ራሳችንን በቅድስና ይዘን ግራ ወደገባቸውና «ሁሉ አለን፣ ምንም አያስፈልገንም» ብለው ነገር ግን በዜሮ ሕይወት ወደሚመላለሱት ሄደን ሙሉውን ወንጌል ማሳየትና መናገር እንድንችል ጌታ ይርዳን፡፡

ግጥምጥም፡- ምንም እንደሌለህ ራስህን ሳትንቅ፣
ከሙሉው ጌታ ጋር አንተነትህን አጣብቅ፡፡

| |
|---|
| ዘፍጥ. 39፡9<br>1ኛ ቆሮ. 3፡16-17 |

# ኢየሱስ ሳሎን ቤት ነው ያለው

ልጅቷ መለስተኛ መዋዕለ ሕፃናት ትምህርት ቤት ትማራለች:: ቤተሰቦቿ ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ ቢሆንባቸውም፣ በመጠን እየኖሩ ልጃቸውን ገና ከልጅነቷ ትምህርት ለማስተማር ወስነዋል:: ልጅቷ ታዲያ የቤተሰቧ ኑሮ ዝቅተኛነት ስለማይገባት በትምህርት ቤት ሌሎች ልጆች ሲበሉና ሲለብሱ ያየችውን ሁሉ ለራሷም በመመኘት ከትምህርት ቤት መልስ ሁልጊዜ ማታ ማታ፣ «ይህንን ግዙልኝ፣ ይህንን ምግብ ሥሩልኝ» እያለች ከአቅማቸው ጋር የማይሄደውን ሁሉ ታዝዛለች:: አባትና እናት ልጃቸው ገና በጨቅላ አዕምሮዋ እንዳትጎዳ በማሰብ አንዳንድ ከገቢ ምንጫቸው ጋር የማይመጣጠን ነገር ሁሉ ያደርጉላታል:: አንድ ቀን ያላት ጫማ ሳያልቅ የሃብታም ልጆች በውድ ዋጋ የተገዛ ጫማ አድርገው ስላየች ብቻ እንዲገዛላት እንደተለመደው ማታ ለአባቷ ጥያቄዋን አቀረበች:: አባትም ከአቅማቸው በላይ እንደሆነ በመግለጽ «ለአባባ ኢየሱስ እንንገረው፣ እርሱ ይገዛልሻልና ነይ እንጸልይ» ብለው አንገታቸውን ሲደፉ አቋረጠችና፣ «ታዲያ፣ መኝታ ቤት ነው የምንጸልየው? አይደለም::» አለች:: «ለምን?» አሏት አባቷ:: «ኢየሱስ ያለው እኮ መኝታ ቤት ሳይሆን ሳሎን ቤት ነውና እዚያ እንሂድ» ብላ እጃቸውን እየጎተተች ሳሎን ቤት ወደተሰቀለው በተለምዶ ኢየሱስ ተብሎ ወደሚባለው ሥዕል ይዛቸው ሄደች:: አባቷም መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር ሁሉ ቦታ መገኘቱን እንዳታውቅ ባደረገው ሥዕልና ይህንንም ሥዕል በውድ ዋጋ ገዝተው ቤታቸው በማምጣታቸው እየተናደዱ እንዲገባት፣ «ኢየሱስ ሳሎን ቤት ብቻ ሳይሆን በሁሉም ቦታ ይገኛል:: እንግዲህ እንዳልሽው ኢየሱስ ጫማ እንዲገዛልሽ ነይ እንጸልይ» አሏት:: በድጋሚ እርሷም ትንንሽ ጣቶቿን ወደ ሥዕሉ እየጠቆመች፣ «ይኸኛው ኢየሱስማ ጫማ ሊገዛልኝ አይችልም:: ተመልከት አባባ፣ ለራሱም እንኳ ቆንጆ ጫማ አላደረገም» ብላቸው አረፈች::

አዎ፣ ወገኖቼ፣ የእኛ አምላክ በግርማውና በክብሩ ሰማይና ምድርን የሞላ፣ ቦታና ጊዜ የማይወስነው ጌታ ነው እንጂ በፍሬም (በፎቶ ማስቀመጫ) ውስጥ ተወስኖ የተቀመጠ አይደለምና ይህንን ጣዖት እናስወግድ:: በየቤቶቻችን የሰቀልናቸው ሥዕሎች እኛን የፈጠረው አምላክ ወኪሎች ሳይሆኑ የተፈጣሪው የእጅ ሥራ የሆኑ ጣዖቶች ናቸውና ለራሳችንና ለቀሪው ትውልድ እንጠንቀቅ::

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል::» (ዮሐ. 4:24)

ግጥምጥም:- ለምን ታመልካለህ ለአንተ የማይበጀውን፣
ፈጣሪህን ትተህ የተፈጠረውን::

ዘፀ. 20:3-4
ኢሳ. 44:9-17

# በኤፌሶን ይገኙዎታለሁ

*«ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፣ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ» (ኤፌ. 5:33)*

ቄሱ ሁለቱን የጋብቻ ቃል ኪዳን ፈጻሚዎች በፊታቸው አቁመው ወደ እነርሱ እየተመለከቱ፣ «ዛሬ እናንተን በእግዚአብሔርና በዚህ ጉባኤ ፊት ቃል እንድትገቡ ከመጠየቁ በፊት፣ የምትገቡትን ቃል ወደፊት በኑሮአችሁ እንደምትፈጽሙትና እንደገባችሁት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንደምትኖሩ ካረጋገጣችሁልኝ በኋላ ነው አሉአቸው።» እነርሱም በአንድ ላይ፣ «በጌታ ጸጋ ዛሬ በምንገባው የጌታ ቃል ኪዳን መሠረት እንኖራለን» አሉአቸው። ቄሱ ባርከዋቸው፣ «ይህን ያልኩበት ምክንያት ዛሬ ሰዎች መድረክ ላይ በቅዱሱ እግዚአብሔርና በቅዱሳኖች መካከል የፈጸሙትን ቃል ኪዳን ነገ በትዳራቸው ውስጥ ለመተግበር ሲቸገሩ ስለማይ ነው» ብለው ይህንን በተግባር የተገለጸ ምሳሌ አስከትለው ለተጋቢዎቹና ለጉባኤው ተናገሩ።

«ልክ እንደ ዛሬው እንደ እናንተ ከዛሬ 25 ዓመት በፊት የተጋቡ ባልና ሚስት ነበሩ። ሙሉ ደስታ ግን በትዳራቸው አይታይም። አንዱም የሚያጋጫቸው ባልየው ለቤተሰቡ ጊዜ አለመስጠቱ ነው። አንድ ቀን ያለወትሮው ባል በጊዜ ወደ ቤቱ መምጣቱ ሚስቱን አስደስቷት ወደ ፊት አነሣቸዋለሁ የምትላቸውን አጀንዳዎች ሁሉ እያነሣች ሲነጋገሩ፣ አንዳንዱ አጀንዳ ጠንካራ ነበርና ከጭቅጭቅ አልፈው ባልን ዱላ እንዲመዙ አደረጋቸው። ስለሆነም ለመማታት ባል ዱላቸውን መዝዘው በሚስታቸው ላይ ሊያሳርፉ ሲሉ፣ ሚስት የዛሬ 25 ዓመት በሠርጋቸው ላይ የገቡትን ቃል ኪዳንና ከኤፌሶን የተሰበከውን ቃል ጮክ ብለው ማስታወስ ጀመሩ። እንዲህ እያሉ፣ "እረ በኤፌሶን ይገኙዎታለሁ! እረ በኤፌሶን ይገኙዎታለሁ!" ባል ግን የገቡትን ቃል ኪዳን ረስተውና ቃሉን ተላልፈው ሚስታቸውን ደበደቡ። ወገኖቼ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጋብቻ ማለት በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራ፣ የሥጋ ሥራ የተደፈነበት ማለት ነውና ሁላችንም በዚህ መሠረት ትዳራችንን እንድንመራ ፈጣሪ ያግዘን» ብለው ቃል ኪዳን ማስፈጸማቸውን ቀጠሉ።

አዎ፣ አንባቢ ሆይ፣ አንተስ እንደ እግዚአብሔር ቃል በፍቅርና በመስማማት የክርስቶስ መልካም ምስክር ሆነህ ትዳርህን እየመራህ ነው? በእግዚአብሔር መንፈስ የተጀመረ ፍቅር በእግዚአብሔር መንፈስ እየታደሰ ይሄዳል። እንደገባነው ቃል ኪዳንና በእጃችን እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ሕይወታችንንና ትዳራችንን እንድንመራ ጌታ ይርዳን። አሜን።

ግጥምጥም:- ቃሉን ሰምተህ በቃሉ ኑር፣
በራስህ ድካም አምላክን አታማር።

| |
|---|
| ፊልጵ. 2:1-5 |
| ኤፌ. 6:10-13 |

## በውሻ የተበላው ስብከት

**የቃል ጥናት ጥቅስ፦** «ቃሉን ስበክ፣ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና::» (2ኛ ጢሞ. 4:2)

መጋቢው በቤተ ክርስቲያናቸው የአገልጋዮች ኅብረት ቀን እንደዚህ እያሉ ሰባኪዎቹን ማስተማርና መምከር ጀመሩ:: «እናንተ ሰባኪዎች፣ በጊዜውም አለጊዜውም ቃሉን ለመስበክ የተዘጋጃችሁ መሆን አለባችሁ:: ሁልጊዜ የምታስተምሩት የእግዚአብሔርን ቃል ቢሆንም እንኳ፣ ቃሉ የሚለውን በትክክል ማለታችሁን እርግጠኛ ሁኑ:: እንዲሁም ቃሉ የሚለውን ለሕዝቡ ለማቅረብ የተመረጠ የስብከት አቀራረብ ዘዴ ተጠቀሙ:: ረጅም ሰዓትና ረጅም ነጥቦች/ አሳቦች/ ይዛችሁ ለመስበክ ብትሞክሩ፣ የሰው አእምሮ ውስን ነውና ሁሉንም መልእክታችሁን ማስተላለፍ አትችሉም:: የእግዚአብሔርንም ሕዝብ አድክማችሁ ጊዜውን በከንቱ ትጨርሳላችሁ:: ለዚህም ተጠያቂዎች ናችሁ:: ስለዚህ ስሙኝ ምክሬ በ45 ደቂቃ የስብከት ጊዜ ከ3 ወይም ከ4 ነጥቦች በላይ ማስተማር አትችሉም የሚል ነው:: ሰዎች ነጥቦች ሲበዙ የመጀመሪያውን እየረሱ ስለሚሄዱ ተጠንቀቁ፣ ጊዜም አይበቃኝም ብላችሁ ምንም ለሕዝቡ ፈውስ የሚሆንና ተጨባጭ የሆነ ትምህርት ሳትሰጡ ሕዝቡን በስሜት ብቻ በአየር ላይ አውጥታችሁ እንዳትለቁ ተጠንቀቁ:: ለዚህ ሁሉ መጸለይ፣ ማንበብና የስብከት ዘዴዎችን ሁሉ ማወቅና መጠቀም አለባችሁ:: አለበለዚያ በእግዚአብሔርም ሆነ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት አግኝታችሁ ከመወደድ ይልቅ ትሰለቻላችሁ፣ ትጠላላችሁም::» ይህንንም አስመልክተው መጋቢው ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ::

ውጭ አገር በረጅም ስብከቱ የተነሣ ሰዎች የማይቀበሉት አንድ መጋቢ ነበር:: እና ሁልጊዜ በሰበከ ቁጥር ከ12 ነጥቦች በታች ተጠቅሞ አያውቅም:: በዚህም ሕዝቡ ሰልችቶታል:: ተደጋግሞም ተነገረው፣ ሊያስተካክል አልቻለም:: አንድ ቀን ግን አዲስ ክስተት ሆነ:: እንደተለመደው መጋቢው ሊሰብክ ቆሞ ሳለ እንዲህ ብሎ በኀዘን ቃል ተናገረ፣ «ዛሬ በፊታችሁ በጣም አዝኜ ነው የቆምኩት:: ለስብከቴ ከተዘጋጀኋቸው 12 ነጥቦች ውስጥ 9 ነጥቦቼን ውሻዬ በልታብኛለች:: ስለዚህ 3ቱን ብቻ ተመልክተን በጊዜ እንጨርሳለን» ከማለቱ አዳራሹ በሙሉ በደስታ ጭብጨባውን አስተጋባ:: መጋቢውም በሦስቱ ነጥቦች ብቻ ሰብኮ ጉባኤውን በጊዜ አሰናበተ:: መጨረሻ ላይም አንድ ከሌላ

ቤተ ክርስቲያን የመጣ እንግዳ ክርስቲያን ሰውዬ ወደ መጋቢው ሄደና፣ «የእርስዎ ውሻ ባደረገችው ተደስቻለሁ:: የእኔም ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንደዚሁ ከ12 ነጥቦች በታች አይሰብክምና የእርስዎ ውሻ ቡችላ ካላት ቢሰጡኝና ይገፉለት ብሄድ ግሩም ነው» ብሎ ጠየቃቸው::

አዎ፣ አገልጋዮች ሆይ ሕዝቡን፣ ጸጋውንና መድረኩን የሰጠን እግዚአብሔር ነውና እርሱን አስደስተን ሕዝቡንም በሚገባው መጠን አስተምረን የታማኝ ባሪያን ሽልማት ለመቀበል እንዘጋጅ:: በዚህም ሩጫችንን እንድንጨርስ ጌታ ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- የእግዚአብሔርን እውነት በግልጽ ተናገር፣

ዋጋ ታገኛለህ በላይኛው አገር::

2ኛ ቆሮ. 6:1-7
2ኛ ጢሞ. 4:5

# ለካስ ለበጎ ነው!

**የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» (ሮሜ 8:28)**

ሰባኪው፣ «ለእኛ እግዚአብሔርን ለምንወድ ሰዎች የሚደርስብንንና የደረሰብንን ነገር ሁሉ ብንመረምረው ለበጎ ነው፤ ለጥቅማችን ነው:: ወንጌል የበለጠ እንዲሰፋ እግዚአብሔር የከበረ ሥራውን በሕይወታችን ለመግለጽ ነው እንጂ እኛን ስለ ጠላን ወይም ለክፉ ነገር ከመጀመሪያው የተመደብን ሆነን አይደለም:: ወገኖቼ፣ እግዚአብሔር ከማዕበሉ ባሻገር ሰላም አለው፣ ከኀዘን ባሻገር ደስታ አለው:: ከለቅሶ ባሻገር ሳቅ አለውና እንታገሥ:: በራሳቸው በጎ ያልሆኑትን ነገሮች እግዚአብሔር ለበጎ ይለውጣቸዋል:: ወይም ዛሬ ችግሬና መስቀሌ ብለን የምንጠራቸው ነገሮች ሁሉ እኛን ለመሥራት እግዚአብሔር የላከልን ወዳጆቻችን ሊሆኑ ይችላሉ:: ስለዚህ ስንገፋ ደስ ይበለን፣ እግዚአብሔር አብሮን አለ:: ዛሬ እየደረሰብን ያለው ጉዳይ ባይገባንም እንኳ እንጽና፣ ነገ ለፈውስ ለደስታና ለደኅንነት ሆኖ እናገኘዋለን::» ለሚለው ስብከታቸው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ::

«አንድ በሚደርስበት ነገር ሁሉ ለበጎ ነው ማለት የተለማመደ አማኝ ወደ ሩቅ ሀገር ለመሄድ የተሳፈረበት አውቶቡስ በረሃ ላይ ይበላሽና ይቆማል:: እርሱም ቶሎ መሄድ ስላለበት ወደ መንገዱ ወጣ ብሎ ሌሎች መኪናዎችን ይጠብቃል፣ ለትብብር እጁን ሲዘረጋ አንድ ትንሽ መኪና ይቆምለታል:: ከፍቶ ይገባና ካመሰገነ በኋላ፣ "አየህ፣ ይህ አውቶቡስ የተበላሸው ለበጎ ነው:: እኔ በጊዜ እንድደርስ ይህችን ትንሽና ፈጣን መኪና አዘጋጀልኝ" ይለዋል:: አባባሉ ያልገባው አማኝ ያልሆነው ሰውዬም ዝም ብሎት መንዳቱን ቀጠለ:: ትንሽ እንደ ተጓዙ የመኪናው ጎማ ፈነዳና ቆሙ:: በብዙ ድካም ጎማ ተቀይሮ ለመሄድ ሲገቡ፣ አሁንም፣ "አየህ፣ ጎማው የፈነዳው ለበጎ ነው:: እኛም መኪናዋም እንድናርፍ ነው" ብሎ ሊያጽናናው ቢሞክር፣ አሁንም ሾፌሩ በውስጡ ከመጀመሪያው ይልቅ ተቆጣ:: በበረሃው ብዙ ረጅም ርቀት እየተጓዙ እያለ ድንገት መኪናዋ ትበላሽና ትቆማለች:: ሾፌሩም እርሱም ወርደው ኮፈን ተከፍቶ ሾፌሩ መካኒክም ስለሆነ ይሠራትና የሞተሩን ክዳን ወርውሮ ኮፈኑን ሲዘጋ ሳያውቅ አውራ ጣቱ ላይ ይጥለውና የሾፌሩ አውራ ጣት ይቆረጣል:: በዚህ ጊዜ እየጮኸ ሳለ አማኙ፣ "ይህም ቢሆን ለበጎ ነው" ይለዋል:: በዚህ ጊዜ ሾፌሩ በጣም ስለ

ተበሳጨ ያንን አማኝ በረሃ ውስጥ ትቶ መኪናውን ይዞ በረረ:: ብዙም ፈቅ ሳይል ሽፍቶች ያገኙታል:: ያለውንም ከዘረፉ በኋላ ለአመጣላቸው አምላክ መሥዋዕት እንዲሆን ሊያርዱት ሲመካከሩ አውራ ጣቱ በደም ተጨመላልቆ ያዩታል:: በዚህ ጊዜ፣ "አይ፣ ለአምላካችንማ አካለ ጎዶሎ መሥዋዕት አናቀርብም" ብለው ይለቁታል:: በዚህ ጊዜ ያስተውልና ወደ ኋላ ተመልሶ እዚያ አማኝ ጋ ይደርስና አውራ ጣቴ የተቆረጠው ለካስ ለበጎ ነው፣ አንተንም እዚህ ትቼ መሄዴ ይህም ለበጎ ነው:: ብትሄድ ኖሮ ታርደህ ነበር ይለዋል::»

አዎ፣ ወገኖቼ፣ በሕይወታችን እግዚአብሔር አውቋቸው የሚፈጸሙት ነገሮች ሁሉ ለጊዜው ቢያስጨኹን፣ ቢያደሙንና ባይመቹንም ነገር ግን ነገ ለበጎ ሆነው ይጠቅሙናልና እንታገሥ:: ይህንንም እንድናስተውልና እንድንኖርበት እግዚአብሔር ይርዳን:: አሜን::

ግጥምጥም:- የጊዜው መከራ ቢጎረብጠኝም፣
ነገር ሁሉ በጎ መሆኑን አልስትም::

| |
|---|
| ዘፍጥ. 50:20 |
| ዮሐ. 9:1-3 |
| ፊልጵ. 1:12-14 |

# ሚስቴ ሞገሴ ናት!

**የቃል ጥናት ጥቅስ:** ***«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነው...» (ዕብ. 4:12)***

ሰባኪው፣ «ይህ ምድር ሁኔታዎች የሚፈራረቁበት ምድር ነው። ደስታ እንዳለ ሁሉ ኃዘንም አለ፤ ጥጋብ እንዳለ ሁሉ ረሃብ አለ፤ ነጻነት እንዳለ ሁሉ ባርነት አለ፤ ማግኘት እንዳለ ሁሉ ማጣትም አለ። ታዲያ በዚህ ሁሉ ክብርን ለጌታ እየሰጠን እንድንኖር የሚያደርገን የእግዚአብሔር ቃል ነው። የእግዚአብሔር ቃል ከላይ በገለጽኳቸው ሁኔታዎች ሁሉ መጽናኛችን ነው። ልብ በሉ፣ በእነዚህ እና በሌሎችም ሁኔታዎች ሁሉ ስታልፉ ቃሉን ለእናንተ የሚያመጣውን መንፈስ ቅዱስን ስሙ፣ ንቁዎችም ሁኑ። እግዚአብሔር ልጆቹን በቃሉና በመንፈሱ ያጽናናል። ሰይጣን የእኛን ደስታ ስለማይወድ፣ ደስታችንንና ሰላማችንን ለመውሰድ ጥቃቅን ችግሮችን ሁሉ አጉልቶ ያሳየናል። በዚያን ጊዜ የጠላትን ልብ ልንረታ የምንችለው፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ልባችንና አእምሮአችን የሚያመጣውን ቃሉን በንቃት ተቀብለን በእምነት ስንወነጭፍ ነው» ለሚለው መልእክታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

«ሁላችንም እንደምናውቀው የሰርግ ቀን፣ የደስታና የፌሽታ ቀን ነው። ለእኔ ግን የእግዚአብሔር ቃል በመንፈሱ አማካይነት እስኪመጣልኝ ድረስ አልነበረም። የምሬን ተበሳጭቼ ነበር። የተበሳጨሁበትንም ምክንያት በደንብ ሳውቀው፣ 'በእውነትም ሰይጣን የክርስቲያኖችን ደስታ አይወድም' አልኩኝ፣ ታሪኩ እንዲህ ነው። በሙሽራ መኪና ከሙሽራዬ ጋር እየሄድኩኝ ሳለ፣ ሰርግ በዘመኑ ብርቅ ነበርና ሰዎች ሙሽራይቱን እያዩ ያደንቁ ነበር። ሁሉም በእርሷና በእኔ የመኪና መስኮት በኩል ዝቅ እያሉ፣ እስቲ ሙሽራዋን ልያት፣ እስቲ ሙሽራዋን ልያት' ይላሉ። ይህ አባባል እኔን አበሳጨኝ፤ "አንድም ሰው እንኳ ተሳስቶ፣ እስቲ ሙሽራውን እንየው አይልም እንዴ?" አልኩኝ። ወዲያው የእግዚአብሔር መንፈስ ቃሉን ወደ እኔ አመጣ፣ "ሚስትን ያገኘ በረከትን አገኘ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን ይቀበላል" (ምሳሌ 18:22)። ለካ ይህቺ ከጎኔ የተቀመጠችው ሞገሴ ናት እና በሞገሴ እንዴት እቀናለሁ፤ ሰይጣን እግዚአብሔር ይገሥጽህ፣ እርሷ ሞገሴ ናት አልኩኝ። ከዚያ በኋላ ሰዎች፣ 'እስቲ ሙሽራዋን እንያት' ሲሉ፣ "ሞገሴን እይዋት" እያልኩኝ ማሳየት ጀመርኩ።»

አዎ፣ የእግዚአብሔር ቃል ሲመጣ ይፈውሳል፣ መንፈስ ቅዱስ በጊዜው ላለንበት ሁኔታ የሚያመጣውን ቃል በንቃ መንፈስ ሆነን እንቀበል፤ በእኛ ሆኖ ሥራውንም እንዲሠራ ልባችንን እንክፈት።

| |
|---|
| ዕብ. 4:16 |
| ቲቶ 3:8 |

ግጥምጥም:- በየዕለት ኑሮዬ ችግር ሲያጋጥመኝ፣
እግዚአብሔር በቃሉ ይመጣል ሊያጽናናኝ።

# መሃይሙ አስረኛ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል።» (ዮሐ. 16:8)

«በዚህ ምድር - ላይ ያለነው ለሁለት ነገሮች ነው። አንደኛ፣ እግዚአብሔርን ታምነን እርሱን ብቻ እንድናመልክ። ሁለተኛ፣ በሕይወታችንና በአንደበታችን ለዓለም ወንጌልን ለመመስከር ነው። ይህ በደንብ ከገባን አንዱን ጥለን ሌላውን ብቻ የመያዝ አዝማሚያ አይታይብንም። ዛሬ ለሰዎች ወንጌልን መመስከር ችላ ብለናል። ለምን? ምናልባት የእኔ ምስክርነት ሰዎችን ስለለወጣቸውና ጌታን ስለማይቀበሉ መተው አለብኝ የሚል ከሰይጣንና ከሥጋ የመጣ ተስፋ አስቆራጭ ምክንያት ይሆናል። ወገኖቼ አንድ እውነት ተረዱ። የእኛ ድርሻ መናገር እንጂ የሰውን ልብ መለወጥ አይደለም። ወንጌሉን አብርቶ የሰውን ልብ መለወጥ የሚችል ሕያው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። የእርሱን ወቀሳና ኃይል ማንም ሊቋቋም አይችልም። እስቲ አንድ የተፈጸመ ምሳሌ ልንገራችሁ።» ብለው ሰባኪው ቀጣዩን ምሳሌ ለጉባኤው ተናገሩ።

አንድ አማኝ የታሠረ ዘመዱን ለመጠየቅ ወደ ወኅኒ ቤት ይሄዳል። በዚያውም ለእሥረኞች ለመስጠት ሁለት መጽሐፍ ቅዱሶችን ይዞ ይሄዳል። የሚጠይቀውን ሰው ፖሊሱ እስኪጠራለት ድረስ ወደ አጥሩ ጠጋ ብሎ ከውስጥ ግንብ ሥር ቆም ብለው ላሉ ሁለት እሥረኞች መጽሐፍ ቅዱሶቹን ያወጣና፣ «እነዚህን ለእናንተ ስጦታ ለመስጠት እፈልጋለሁ። ውሰዱና አንብቡ» ሲላቸው፣ አንደኛው፣ "እንቢ" አለ። ጭራሽም፣ "ጴንጤ መሆን አልፈልግም» ብሎ ተናገረ፣ ተቆጣም። ሁለተኛው ደግሞ፣ «ጴንጤ የመሆን ወይም ያለመሆን ጉዳይ ሳይሆን፣ ስጦታ ብሎ ሲሰጠን እንደ አገራችን ባህል አመስግነን ነው መቀበል ያለብን» ብሎ ጓደኛውን በመቆጣት ለራሱ ብቻ፣ «አንዱን መጽሐፍ ቅዱስ ለእኔ ስጠኝ» ብሎ ተቀበለ። በውስጡ ምን እንደሚል ማወቅ ፈለገ። ግን ማንበብ አይችልም። እምቢተኛው ጓደኛው ግን ይችላልና ማታ ለአንተ ሳይሆን ለእኔ አንብብልኝ ብሎት ሰጠው። ይህም ሰው ድንገት የከፈተው 12 ዓመት ደም የፈሰሳትን ሴት ፈውስ ጉዳይ የሚያወሳውን ክፍል ነበርና ለሰውዬው ያነብለት ጀመር። ነገር ግን በንባቡ መሃል ቀና ብሎ አንብብልኝ ያለውን ጓደኛውን ሲያየው ለካስ እንቅልፍ ወስዶታል። በዚህ ጊዜ ይህ ሰው እንዲያነብ ለሚለው

ተኝቷል። እንዳያቆም 12 ዓመት ደም የፈሰሳት ሴት ታሪክ ገርሞታልና መጨረሻው ድረስ አነበበ። ሳያውቀውም እንባው በጉንጩ ላይ ፈሰሰ። ጓደኛውንም ቀስቅሶ፣ «በርግጥም ኢየሱስ ጌታ ነው። አዳኝ ነው።» ብሎ ተናገረ። ሁለቱም የሕይወታቸው ጌታ አድርገው ኢየሱስን አመኑት /ተቀበሉት/።

አዎ፣ የሰውን ልብ ሊለውጥ የሚችለው ሰው ሳይሆን የእግዚአብሔር መንፈስ እና ቃሉ ናቸው። የእኛ ድርሻ መናገር ነው። ጌታ ድርሻውን መወጣት ይችልበታል። ስለዚህ በቤታችን፣ በጎረቤታችን፣ በአካባቢያችንና በሥራ ቦታችን ሁሉ እግዚአብሔር የሰጠንን የተከፈተ በር ሁሉ ተጠቅመን ሰላምና ሕይወት የሚሰጠውንና የታሰሩትን የሚፈታውን ወንጌል እንድንናገር ጌታ ይርዳን።

ግጥምጥም:- በአሉባልታ ወሬ ዓይን ከማወጣ፣
ቃሉን በመመስከር ድርሻዬን ልወጣ።

| |
|---|
| ዮሐ. 16:13 |
| ዕብ. 4:12 |

# ክፍል 12
## ግብዝነት ስለሌለበት እውነት
## ገመድ ሰርቄአለሁ

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል::» (ምሳሌ 28:13)::

የቤተ ክርስቲያኒቱ የንስሐ ፕሮግራም ላይ እንዲሰብኩ የተጋበዙት ቄስ እንዲህ እያሉ ስለ እውነተኛ ንስሐ መስበክ ጀመሩ:: «እውነተኛ ንስሐን እግዚአብሔር ይወዳል፤ በእግዚአብሔር ፊት የሠራችሁትን ሁሉ ምንም ሳትደብቁና ሳታፍሩ ተናዘዙ እንጂ ለሰው ለመናገር እንደምታፍሩ ለእግዚአብሔር ለመናገር አትፈሩ:: ይልቁንም ስለ ኃጢአታችሁ እፈሩና አስወግዱት እንጂ:: በደፈናው፣ "የሰረቅሁትን ነገር ይቅር በለኝ" ከማለት፣ "የሰረቅሁት ይህንን ያህል ብር ነው?" እንበል:: "ስለ ሰረቅሁት እንስሳ ይቅር በለኝ" ከማለት፣ "ትናንት ስለ ሰረቅሁት በግ ይቅር በለኝ" እንበል:: እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ቢያውቀውም እንኳ በፈቃደኝነት ገልጸን በትክክል ንስሐ እንድንገባ ይፈልጋል:: በቃሉም እንዲህ ብሎ ተናግሯል፣ "ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም::" (1ኛ ዮሐ. 1:8)::» ለዚህም ስብከታቸው ቄሱ ቀጣዩን ምሳሌ እንዲህ በማለት አስረግጠው ተናገሩ::

«አንድ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ መጥቶ እንዲህ ሲል ንስሐ ገባ:: 'መጋቢ፣ ስለ ኃጢአቴ የመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ አለብኝ፣ ሕሊናዬ ሊያርፍ አልቻለምና ስለሠራሁት በደል እግዚአብሔር ይቅር እንዲለኝ ጸልይልኝ' አለው:: መጋቢውም ደስ ብሎት፣ 'ይህ ዓይነት አቀራረብ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና መልካም ነው:: ለመሆኑ የሠራኸው ኃጢአት ምንድን ነው?' ይለዋል:: አማኙም፣ 'ገመድ ሰርቄአለሁ' ይለዋል:: ይህንንም ኃጢአት መጋቢው በንስሐ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው ይጸልይለትና ይለያያሉ:: በሌላ ቀንም፣ በሌሎች ቀናትም፣ እየደጋገመ አማኙ ወደ መጋቢው እየመጣ፣ አሁንም 'የሕሊና እረፍት አጥቻለሁ፣ ኃጢአቴ አላሳረፈኝም፤ እባክህ፣ እንደገና ጸልይልኝ' ይለዋል:: ይጸልይለታል፣ ይሄዳል:: እንደገናም በሌላ ጊዜ ይመጣል:: አንድ ቀን መጋቢው እንዲህ ብሎ ጠየቀው፣ "ይህ ብቻ አይመስለኝምና እስቲ ልጠይቅህ፣ በገመዱ ጫፍ ምን ታሥሮ ነበር?" ቢለው፣ "ፍየል ታስሮበት ነበር" አለው::»

አንባቢ ሆይ፣ እግዚአብሔር አይዘበትበትምና ኃጢአትህን ሳትደብቅ የሠራኸውን ሁሉ አሁኑኑ ተናዘዝ:: ተመልሰህም አትድገመው፣ አቅጣጫህን ቀይር፣ ያን ጊዜ ጽድቅህ እንደ ንጋት ብርሃን ይሆናል፣ የሚቋቋምህም የለም:: ኃጢአት እንዳንሠራ፣ ከሠራንም እውነቱን እንድንናዘዝ መንፈስ ቅዱስ ያግዘን:: አሜን::

| |
|---|
| 1ኛ ዮሐ. 1:9-10 |
| ሕዝ. 18:32 |

ግጥምጥም:- በኃጢአት ተወልደህ በኃጢአት ከምትሞት፣
ኃጢአትህን ተናዘህ ግባ ወደ ገነት::

# በወገቡ የተጠመጠመው እባብ

በየመንደሩ እየዞረ በእባብ እያስፈራራ ትኩስ ወተት መጠጣቱን ቋሚ ሥራ አድርጎታል። ዛሬ አንዱ ቤት እንደዚህ ያደርጋል፣ ነገ ደግሞ ሌላ ቤት። ግን ክፉ ልማድ አንድ ቀን ማጥፋቱ አይቀርምና እንደለመደው አንድ ቀን ጠዋት ወደ አንድ መንደር ሄዶ በር ላይ ያገኛትን አንድ ሴት የእባቡን ጭንቅላት ይዞ ወደ እርሷ እያሳየ፣ «ቶሎ ብለሽ ትኩስ ወተት ካላመጣሽ ዛሬ በዚህ እባብ ተነድፈሽ መሞትሽ ነው» አላት። እርሷም፣ "እሺ" ብላ በድንጋጤ እየተርበተበተች ወደ ውስጥ ገባችና ወተት አምጥታ ሰጠች። እርሱም ከጠጣ በኋላ ስትርበተበት ስላያት ሴትዮዋን ለማረጋጋት ፈልጎ፣ "አይዞሽ፣ ምን ያርበተብትሻል? ይህ እባብ እንደሆነ አይናደፍም። ተመልከች" ብሎ በወገቡ የተጠመጠመውን የእባቡን አፍ በአፉ ውስጥ እያስገባ ሲያሳያት ሳያስበው በድንገት እባቡ አፉ ውስጥ በመንደፍ መርዙን ረጭቶ ገደለው።

አዎ፣ ዛሬ ጥቅም ያገኘንበት መስሎን ነገ ሊያጠፉን ያለ ኃጢአት ምን ይሆን? እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፣ «ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፣ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች፣ እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ፣ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እንቢ ብትሉ ግን ብታምፁም፣ ሰይፍ ይበላችኋል፤ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና።» (ኢሳ. 1:18-20)። ለዚህ አምላካችን እሺ ብለን በመታዘዝ፣ ኃጢአታችንንም በመናዘዝና በመተው የምድርንም የሰማይንም በረከት እንድንበላ ጌታ ራሱ በጸጋው ይደግፈን። አሜን።

የቃል ጥናት ጥቅስ: «በደለኞችና ኃጢአተኞች ግን በአንድነት ይሰበራሉ፣ እግዚአብሔርንም የሚተዉ ይጠፋሉ።» (ኢሳ. 1:28)።

ግጥምጥም:- የእባቡን አፍ በአፌ ሕያስተናገድኩኝ፣
ሳላውቀው በድንገት ተቀስፌ አረፍኩኝ።

| |
|---|
| ዮሐ. 8:11<br>1ኛ ዮሐ. 1:9 |

## «ኢብራሂም ሰላም ብሎሃል!»

የቃል ጥናት ጥቅስ:- «ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፣ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን •ተነጋገሩ» (ኤፌ. 4:25)።

በዚህ ጥቅስ ላይ በመመርኮዝ ሰባኪው የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓመታዊ የአንድነት ፕሮግራም ላይ ለተሰበሰበው ምእመን ትምህርታቸውን እንዲህ እያሉ ቀጠሉ። «እውነት ያኮራል፣ ያሳድጋል፣ ያለመልማል። ውሸት ደግሞ በተቃራኒው ያሰድዳል፣ ያዋርዳል። እውነቱ ይህ ሆኖ እያለ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ግን እውነት እየከሳ፣ ውሸት እየወፈረና እየደለበ የመጣ ይመስላል። እግዚአብሔር ግን ጻድቅ ፈራጅ ነውና እውነት ይክሳ እንጂ ያሸንፋል። እናንተ በእውነተኛው የእግዚአብሔር ስም የዳናችሁና የተጠራችሁ ሕዝቦች ሆይ፣ እርስ በርሳችሁ እውነትን ተነጋገሩ፣ ተጫወቱ፤ ውሸትን ከሕይወታችሁ፣ ከቤተ ክርስቲያናችሁ፣ ከቤታችሁ አስወግዱ፤ የእውነት ምንጩ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ስለ እውነት ልጆቹን ያከብራል። የውሸት አባትና ምንጩ ሰይጣን ነው። ሰይጣን ደግሞ ከመጀመሪያ የተዋረደ ስለሆነ ያዋርዳል፤ እርሱን ካዱት» ለሚለው ጠንካራና መሠረታዊ የሆነ ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተናገሩ።

«አንድ በጌታ የምወደው ባልንጀራዬ በልጅነቱ ውሸት እንዴት አድርጎ በሰዎች ፊት እንዳዋረደው ያጫወተኝን ልንገራችሁ። አባቱ ልጆቻቸው በጥሩ ሥነ ምግባር አድገው ሥራቸው ለቤተሰባቸው አልፎም ለአገር እንዲተርፍ፣ ጥሩ ዜጋ እንዲወጣቸው፣ በዋልጌነትና በዋዛ ፈዛዛ ዕድሜያቸውን እንዳያሳልፉ የጠበቀ ቁጥጥር ያደርጉባቸው ነበር። ከዚህ የተነሣ አባታቸውን ይፈራሉ። በተቻለ መጠን የአባታቸውን ፈቃድ ለመፈጸም ይጥራሉ። ሆኖም ሁልጊዜ አይሞላምና አንድ ቀን ይህ ጓደኛዬ ከጓደኞቹ ጋር ውጭ አምሽቶ ዘወትር ከሚገባበት ሰዓት በጣም አሳልፎ መጣ። የቤቱ በር ላይም ቆም ብሎ የአባቱን ነገር አሰላሰለ። "ምን ይሻለኛል? ልግባ አልግባ" እያለ ተጨነቀ። በመግባቱም ቆረጠና በር አንኳኳ። እንደፈራውም በሩን ከውስጥ የከፈቱት እኚያ በጣም የሚፈራቸው አባቱ ነበሩ። ፊት ለፊት ተፋጠጡ። ከዚያም የሚለው ግራ ቢገባው በተንተባተበ አንደበት ድንገት በአፉ የመጡለትን የአጎቱን ስም ጠራና፣ "ኢብራሂም ሰላም ብሎሃል፤ አሁን በቀጥታ ከእርሳቸው ጋር ቆይቼ ነው የመጣሁት" ሲል

እጃቸውን በአፋቸው ይዘው፣ ስለ እርሱም አፍረውለት በሩን ለቀቁለት:: ወደ ውስጥ ሲገባ አጎቱ ኢብራሂም ለካ ቀደም ብለው በጊዜ መጥተው ኖሯልና እቤት አገኛቸው:: ከዚያች ሰዓት ጀምሮ አይናገር አይጋገር አንገቱን በእፍረት አቀርቅሮ አመሸ::»

አዎ፣ ክርስቲያኖች፣ ውሸት ያዋርዳል፣ አንገትም ያስደፋል፣ ያሰቅቃልም:: ስለዚህ ይህን አዋራጅ ኃጢአት አስወግደን በየቀኑ ከባልንጀሮቻችን ጋር፣ ከቤተሰቦቻችን ጋር፣ ከጎረቤቶቻችንና ከመንግሥታችን ጋር እውነትን እንድንነጋገር የእውነት አምላክ ራሱ በእውነቱና በጸጋው ይደግፈን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ውሸትን ተሞልተህ ከምትግደረደር፣

እውነትን ተናግረህ ከመሸበት እደር::

| |
|---|
| ዮሐ. 8:31 |
| ዘፍጥ. 39:11-18 |

# ጾም ጸሎት

የቃል ጥናት ጥቅስ «አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልሃል» (ኤፌ. 5:14)::

ሰባኪው፣ «በዚህ ጨለማ ዓለም ውስጥ ብርሃንና ጨው ሆነን መመላለስ የምንችለው ነቅተን በጸሎት ሕይወታችን ስንተጋ ነው:: ዛሬ ሰይጣን ከተያያዘው የውጊያ ስልቱ አንዱ እንቅልፋምና ሰነፍ ማድረግ ነው:: የጨለማ ሥራው እንዳይገለጥ የብርሃንን ልጆች በእንቅልፍ አዚም ይመታልና አሳቡን ሳንስተው ተግተን ልንጸልይና ልንቃወመው ይገባል:: የእግዚአብሔር ቃል እንደሚል፣ “እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፣ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች” (ያዕቆብ 5:16):: እርግጥ ነው የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ ኃይለኛን ነገር ታደርጋለች:: ይህንን የተረዳ ሰይጣን በሥራዋ ሥራው እንዳይፈርስበት የጸሎት ትጋታችንን ለማስጣል በጌታ ፊት ተንበርክከን ከመጸለይ ይልቅ ቆመን እንድንጣላ በዘዴ ሥራ ሰጥቶናልና ነቅተን ልንቃወመው ያስፈልጋል:: እስቲ ከዚህ መልእክቴ ጋር የሚሄድ አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ» ብለው ሰባኪው ቀጣዩን ምሳሌ ተናገሩ::

«ቤተ ክርስቲያኒቱ ባወጀችው መሠረት ዕለቱ የጾምና ጸሎት ቀን ነው:: ሁሉም በዚያ ቀን ከእህል ውኃ ተቆጥቦ ስለ ግል ሕይወቱ፣ ስለ ቤተሰቡ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያኑና ስለ አገሩ በእግዚአብሔር ፊት ያነባል:: በርእስ ተከፋፍሎ በተሰጣቸው መሠረት በየተራ ሰዎች ፕሮግራሙን በጸሎት መምራት ቀጥለዋል:: የቻለ በተንበረከከበት ቆይቶ፤ ያልቻለ ደግሞ እየቆመ ለዕለቱ የተያዘው ሰዓት ሲደርስ ሁሉም በአንድ ላይ ጸልዮ ከጨረሰ በኋላ ፕሮግራሙ አልቆ ሁሉም በየቤቱ ሄደ:: አንዲት ሴት ለካ ጠዋት እንንበርከክ በተባለ ጊዜ የተንበረከከች ፕሮግራሙም ካለቀ በኋላ እንቅልፍ ወስዷት ኖራልና ሳትነቃ ቀረች:: እንቅልፏን ጨርሳ ከተንበረከከችበት ወንበር ስትነሣ ማንም ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የለም:: በዚህ ጊዜ ባደረገችው ነገር ተደናግጣና አፍራ “ሰይጣን፣ ብተኛም በአባቴ ቤት ነው የተኛሁት፣ ደስ አይበልህ” አለች::»

ወገኖቼ፣ በእግዚአብሔር ቤት ሆነን ከተኛን በዓለም ያሉትን ማን ይታደጋቸው? ሰይጣን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ደስ የሚለው በዓለም ሆነን ስንተኛ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቤት ሆነን ስንተኛ ነውና እንንቃ:: ጌታም በቃሉ ያለን፣ «ስለምን ትተኛላችሁ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሥታችሁ ጸልዩ»:: (ሉቃ. 22:46):: በቀረው ዘመናችንም ጌታ የሚተጋ የጸሎት ሕይወትን ያፍስስልን:: አሜን::

ግጥምጥም:- ሕይወቱ እየሞተ ለምን እተኛለሁ፣
ከእንግዲህስ ይብቃኝ ደጁን እጠናለሁ::

ሉቃ. 22:45

# *የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት*

*«እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደፊት ለምንም አይጠቅምም።»*

*(ማቴዎስ 5:13)*

## የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት /የጨመማአ/ ለምን አስፈለገ?

በዚህ ዥንጉርጉር ዓለም ውስጥ ብዙ መፍትሄና ቀና መንገድ የሚጠይቁ ብዙ ዥንጉርጉር ችግሮች መኖራቸው አሌ የማይባል ሐቅ ነው። በተለይም ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ስንመለስ ይህ ጉዳይ በጣም ጎልቶ ይታያል። አያሌዎች ለተለያዩ ችግሮቻቸው ምክር በመጠየቅና መልካም የሆነ ምላሽ አግኝተው የሚሄዱበትን ሲፈልጉ እንደ ልብ አያገኙም። ጥቂቶች ብቻ በጥቂት አማካሪዎች በሚድኸው የማማከር አገልግሎት ምክር አግኝተው ይሄዳሉ። የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎትም የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ሰዎችን ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል በምክር ለማቅናትና ለመደገፍ በእግዚአብሔር ምሪት የተጀመረ የአገልግሎት ክፍል ነው። /1ኛ ጢሞ. 3:16/

## የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር ኣገልግሎት /የጨመማአ/ እንዴት ተጀመረ?

በምክሩ ግሩም የሆነው ጌታ እግዚአብሔር ይህንን አገልግሎት እንድንጀምር በእኔ እና በባለቤቴ ልብ ራእዩን ሲያመጣ ብዙ ጊዜ በፊቱ የቆይታ ጸሎት አድርገናል፤ ራእዩም ከእርሱ መሆኑን ስናረጋግጥ ሰፊና ትልቅ በሆነው የማማከር አገልግሎት በእርሱ ጸጋ ተደግፈን ጌታ ህዝቡን ለማቅናትና ለመፈወስ በሚሠራበት ዘመን እኛም ከእርሱ ጋር አጠቃላይ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የምክር አገልግሎት በመስጠት አብረን ለመሥራት ወሰንን። በዚህም መሠረት የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት በ1994 ዓ.ም በነሐሴ ወር ተጀመረ። /ማቴ. 5:13/

## የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት /የጨመማአ/ ግብ ምንድን ነው?.

የጨመማአ ግብ ሰዎች ሁሉ በኀዘንም ሆነ በደስታ ጊዜ ዓይኖቻቸውን ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር ላይ ሳያነሡ እንደ እርሱ አሳብ እንዲሄዱና ጌታ በክርስቶስ በኩል ያዘጋጀውን ዘላለማዊ የድኅነት መንግሥት እንዲወርሱ ለመርዳት ነው፡፡

## የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት /የጨመማአ/ ዓላማዎች ምንድን ናቸው?.

1. ለሰዎች ሁሉ መልካም ምክር መስጠት፣ ወንጌልን በደብዳቤ መመስከር፣ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄዎቻቸው ምላሽ መስጠት፡፡
2. ለባለትዳሮችና ትዳር ለሚመሠርቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክር መስጠት፡፡
3. አብያተ ክርስትያናትን ለምክር አገልግሎት ለማነሣሣት ትምርትና ሥልጠና መስጠት፡፡
4. መጽሐፍ ቅዱስን በመላላክ መማር ለሚፈልጉ ሁሉ በአድራሻ ማገናኘት፡፡

### የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት /የጨመማአ/ ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

1. በጋብቻ ዙሪያ:-
   ሀ. ላላገቡ ወጣቶች
   - በትዳር ጓደኛ ምርጫ ዙሪያ
   - በእጮኛሞች ቅድስና ዙሪያ
   - ወጣቶች እንዴት ለጋብቻ ይዘጋጃሉ
   - በቅድመ - ኤች አይ ቪ ምርመራ ዙሪያ
   - በሰርግ ዝግጅት ዙሪያ/ ጥሎሽ፣መልስ፣ቅልቅል/
   - ድንግልና፣እርግዝና፣ውርጃ

   ለ. ላገቡ ባለትዳሮች
   - የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት
   - የቤተሰብ ምጣኔ
   - ኤች አይ ቪ /ኤድስና ባልና ሚስት

- ድርብ ጋብቻ
- ዳግም ጋብቻ
- አገልጋይና ቤተሰቡ
- የልጆች አስተዳደግ
- የወሲብ ችግሮች
- ፍቺ
- ቤተሰብና ጎጂ ባህሎች
- የባልና ሚስት ግንኙነት/ ሚና/

2. ከመጽሐፍ ቅዱስ በሚነሡ ጥያቄዎች ዙሪያ/ መጽሐፍ ቅዱስ ስታነቡ ወይም ስትሰሙ ጥያቄ የፈጠረባችሁ ቢኖር/
3. ኤች አይ ቪ /ኤድስን በተመለከተ ከባለሙያዎች ጋር በመመካከር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክር እንሰጣለን::
4. መጽሐፍ ቅዱስን በማስተማርና በመስበክ የሚያገለግሉትን አገልጋዮች ማገልገል:-
   4.1 በጥያቄዎቻቸው መሠረት ለሚያስተምሩት ትምህርት የሚጠቅማቸውን ምሳሌ በመላክ፣
   4.2 በአገርም ውስጥ ሆነ ከአገር ውጪ መጽሐፍ ቅዱስን በመላላክ መማር ለሚፈልጉ ሁሉ ጤናማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ከሚሰጡ ክፍሎች ጋር ማገናኘት::

እንግዲህ ከላይ በጠቀስናቸው አገልግሎቶች ለመገልገል የምትፈልጉ ሁሉ በቀጣዩ አድራሻችን ጥያቄዎቻችሁን ሁሉ ብትልኩልን ይደርሰናል:: እግዚአብሔር ሁላችሁንም ይባርካችሁ!

አድራሻችን:- የምድር ጨው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት
የመ.ሳ.ቁ. 70893
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ:- 349-23-57 (የቤት)
091-140-45-54
ኢ-ሜይል:- sebcm@ethionet.et
ወይም
sebcm2@yahoo.com